የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 59
ADDIS ABABA, 3rd September, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፮/፪ሺ፲፰ የካርበን ገበያ አዋጅ ……..ገጽ ፳ሺ፩፻፸

Content

Proclamation No. 1436/2026

Carbon Market Proclamation.....Page 20170

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፮/፪ሺ፲፰

የካርበን ገበያ አዋጅ

የአየር ንብረት ለውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ አሳሳቢ ጉዳይ በመሆኑና ኢትዮጵያ አየር ንብረት ላይ በሚደገፉ ዘርፎች ላይ ጥገኛ እንደመሆኗ መጠን በከፍተኛ ደረጃ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ በመሆኗ ለዓለም አቀፍ የልቀት ቅነሳ ድጋፍ ማድረግና በአየር ንብረት ላይ አደገኛ ጣልቃ-ገብነትን ማስቀረት የብሔራዊ ጥቅም ጉዳይ በመሆኑ፤

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ የማዕቀፍ ስምምነትንና የፓሪስ ስምምነትን እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ የካርበን ገበያ ማዕቀፎች ያጸደቀች በመሆኑ፤

የካርበን ገበያ አሠራሮች የኢትዮጵያን የዝቅተኛ ልቀት የልማት ስትራቴጂና በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረቱ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅዶችን ለማሳካት፣ ግንዘብ ለማሰባሰብና በዚህም ዘላቂ ልማትን፣ አረንጓዴ የሥራ ዕድሎችንንና የሥነ-ምኅዳር ጥበቃን ለማፋጠን ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ፤

PROCLAMATION No. 1436/2026

CARBON MARKET PROCLAMATION

WHEREAS, climate change is a global concern to which Ethiopia is acutely vulnerable due to its dependence on climate-sensitive sectors, making it in the national interest to support global emission reductions and avoid dangerous climate interference;

WHEREAS, Ethiopia has ratified the United Nations Framework Convention on Climate Change and the Paris Agreement, and other relevant international carbon market frameworks;

WHEREAS, carbon market mechanisms are instrumental to achieving Ethiopia's low emissions development strategy, and its Nationally Determined Contributions (NDCs), mobilizing finance, while catalyzing sustainable development, green jobs, and ecosystem protection;

ኢትዮጵያ በካርበን ገበያ ውስጥ ኢንቬስትመንትን የሚስብና የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ሽግግርን ለማሳለጥ የሚያግዝ የተፎካካሪነት ዐቅሟን ለማሳደግ ፍላጎት ያላት በመሆኑ፤

WHEREAS, Ethiopia wishes to facilitate its competitive advantage in the carbon market that can attract investment and facilitate the transfer of climate-friendly technologies to enhance community resilience;

የካርበን ቅነሳ ተግባራትን ለመቅረጽ፣ ለማጽደቅ እንዲሁም ግልጽ በሆነ የክትትል፣ ሪፖርት የማድረግና የማረጋገጥ ሥርዓት አማካኝነት የቅነሳ ተግባራትንና ውጤቶችን ይሁንታ በመስጠትና በመፍቀድ የገበያ ሀቀኛነትን መደገፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it is necessary to establish standardized procedures for development and the approval of mitigation activities, issuance, and authorization of mitigation activities and mitigation outcomes through a transparent system of monitoring, reporting, and verification to support market integrity;

ኢትዮጵያ፣ ለሕዝቦቿና ለምትገኝበት ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ጠቀሜታ ሲባል በግዛቷ ውስጥ የሚከናወኑትን የካርበን ቅነሳ ተግባራትና ውጤቶችን እንዲሁም ተፈጥሮአዊ የካርበን ማከማቻዎችን በበላይነት የመምራትና የመቆጣጠር ሉዓላዊ መብት ያላት በመሆኑ፤

WHEREAS, Ethiopia asserts its sovereign right to oversee and regulate all mitigation activities and mitigation outcomes and natural carbon sinks within its territory for the benefit of its people and the global climate that they live in;

የካርበን ገበያ ተግባራት የአካባቢ ማኅበረሰቦችን መብቶችን ለመጠበቅ፣ ርትዕን መሠረት ያደረገ የጥቅም ክፍፍልን ለማሳለጥ እንዲሁም የተፈጥሮአዊ ሥነ-ምኅዳሮችን ደኅንነት ለማስጠበቅ እንዲቻል ጠንካራ የአካባቢና የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓቶችን ባከበረ መንገድ መከናወናቸው አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, it is essential that carbon market activities are conducted in accordance with robust environmental and social safeguards to protect the rights of local communities, facilitate the equitable distribution of benefits, and maintain the integrity of natural ecosystems;

በተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ሕጎችና መመሪያዎች ውስጥ ተበታትነው የሚገኙና ከካርበን ገበያ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በአንድ ላይ ማጠቃለል አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, it has become necessary to consolidate carbon market related Proclamation, regulation, rules and directives into one Proclamation;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት እንደሚከተለው ታውጇል።

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የካርበን ገበያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፮/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

፩/ **"ተጨማሪነት"** ማለት በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ግዴታ ሆኖ ያልተቀመጠና በካርበን ክሬዲት ገቢዎች ወይም በአየር ንብረት ፋይናንስ አማካኝነት የተፈጠሩ ማበረታቻዎች ባይኖሩ ኖሮ ሊከሰት የማይችል የቅነሳ ተግባራት ውጤት የሆነ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ቅነሳ፣ ማስወገድ ወይም ማስቀረት ማለት ነው፤

፪/ **"አንቀጽ ፮"** ማለት በፓሪስ ስምምነት ሥር የሚገኝና ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ግቦቿን ለማሳካት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ዓለም አቀፍ ትብብር የምታደርግበት ማዕቀፍ ሲሆን፣ በአባል አገራት የሚመራ የቅነሳ ውጤቶች ዓለም አቀፍ ዝውውርን (አንቀጽ ፮.፪)፣ ዓለም አቀፍ የግብይት ሥርዓትን (አንቀጽ ፮.፬) እና በገበያ ላይ ያልተመሠረቱ የትብብር አሠራሮችን (አንቀጽ ፮.፰) የሚያካትት ሆኖ ዓላማውም የላቀ ተነሳሽነትንና ዘላቂ ልማትን ማሳደግ እንዲሁም አካባቢያዊ ደኅንነትን ማረጋገጥ ነው፤

፫/ **"ማስቀረት"** ማለት የፕሮጀክቱ ተግባር ባይኖር ኖሮ ሊከሰት ይችል የነበረን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት እንዳይከሰት መከላከል ማለት ነው፤

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Carbon Market Proclamation No. 1436/2026."

2. Definition

1/ **"Additionality"** means GHG emission reductions, removals or avoidance from Mitigation Activities that are not required by legal framework and which would not have occurred in the absence of the financial incentive created by Carbon Credit revenues or climate finance;

2/ **"Article 6"** means the rules and requirements of Article 6 of the Paris Agreement through which Ethiopia may voluntarily engage in international cooperation to meet its climate targets, including for member country driven international transfers of Mitigation Outcomes (Article 6.2), for the Paris Agreement crediting mechanism (Article 6.4), and for non-market-based cooperative approaches (Article 6.8), all aimed at fostering higher ambition, sustainable development and environmental integrity;

3/ **"Avoidance"** means the prevention of GHG emissions that would have otherwise occurred in the absence of a Mitigation Activity;

፬/ **"መነሻ"** ማለት አንድ የካርበን ቅነሳ ተግባር በሌለበት ሁኔታ ወስጥ ሊከሰቱ ይችሉ የነበሩ ሁኔታዎችን ሊያሳይ በሚችል የማነጻጸሪያ የቢሆናዊ ሁኔታ ዐውድ ውስጥ የካርበን ቅነሳ ተግባራት በሌለበት ሁኔታ ሊከሰት ይችል የነበረ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ቅነሳ ወይም ማስወገድ አሃዛዊ ማነጻጸሪያ ነው፤

4/ **"Baseline"** means the quantitative reference of the GHG emissions and/or GHG removals that would have occurred in the absence of a Mitigation Activity in the context of a reference scenario that best represents the conditions that are most likely to occur in the absence of such Mitigation Activity;

፭/ **"የካርበን መጠባበቂያ"** ማለት ከተወሰኑ የቅነሳ ውጤቶች የሚውጣጣና ሳይለቀቁ ወይም ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለዚሁ ዓላማ በተለየ ሒሳብ ውስጥ ተለይተው የሚቀመጡ የካርበን ክሬዲቶች ወይም በአንድ የካርበን ስታንዳርድ መሠረት የተቋቋመ ክምችት ሲሆን ከሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት ቅነሳ ግዴታዎች አለመፈጸም ወይም ከልቀት ቅነሳዎች ወይም የመወገድ ሂደቶች ቋሚ አለመሆን ወይም መቀልበስ የሚመነጩ ስጋቶችን በመከላከል የካርበን ግብይቶችን አካባቢያዊ ደኅንነት የሚያረጋግጥ ነው፤

5/ **"Carbon Buffer"** means the reserve of Carbon Credits from certain types of Mitigation Outcomes in a dedicated account that may be withheld from issuance or use, or otherwise established pursuant to a Carbon Standard to safeguard against the risks of non-Permanence or reversal of GHG emission reductions or removals from the Mitigation Outcome, and intended to facilitate a risk adjusted approach to Permanence and environmental integrity;

፮/ **"ካርበን አሰባሳቢ"** ማለት ከተለያዩ የመሬት ባለይዞታዎች ወይም ኩባንያዎች አነስተኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን የመቀነስ፣ የማስወገድ ወይም የማስቀረት ፕሮጀክቶችን በአንድ ላይ በማሰባሰብና ወደ ልዩ ልዩ ፖርትፎሊዮች በማካተት እንደገና ለገዢዎች የሚሸጡበትን መንገድ የሚመራ አካል ነው፤

6/ **"Carbon Aggregator"** means an entity that pools small-scale GHG emission reduction, removal or avoidance projects from multiple landowners or companies, aggregating them into diversified portfolios, and managing their resale to buyers;

፯/ **"የካርበን ጥቅም ማጋራት"** ማለት ለልቀት ቅነሳ ተግባራት አፈጻጸም አስተዋጽኦ ላደረጉ ባለ ድርሻዎች ባለቤትነትን፣ መብቶችን፣ የሚና ድርሻዎችን፣ መዋጮዎችን፣ ወጪዎችንና ኀላፊነቶችን መሠረት በማድረግ ብቁ ሆነው ለተገኙት ከካርበን ክሬዲቶች የሚገኙ የገንዘብ እና ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ትርፎችን ማከፋፈል ነው፤

7/ **"Carbon Benefit Sharing"** means the distribution of financial and non-monetary proceeds from carbon credits among stakeholders who contributed for the implementation of emission-reduction activities, among eligible stakeholders based on their ownership, rights, roles, contributions, costs, and responsibilities;

፰/ **"የካርበን ክሬዲት"** ማለት በአንድ ዕውቅና ባለው የካርበን ስታንዳርድ ወይም የካርበን መዝገብ ወይም በእነዚህ አማካኝነት ከአንድ የቅነሳ ውጤት የሚመነጨዉ ተፈጻሚነት ያላቸውን ደንቦችና መመዘኛዎች መሠረት በማድረግ የሚሰጥና የሚገበይ የምስክር ወረቀት ሲሆን አንድ ሜትሪክ ቶን የካርበን ዳይኦክሳይድ ወይም የካርበን ዳይኦክሳይድ አቻ የሆነን ጋዝ ይወክላል፤

8/ **"Carbon Credit"** means a tradable certificate issued by or through a Carbon Standard or Carbon Registry in accordance with the applicable rules and requirements that results from a Mitigation Outcome and represents one metric tonne of carbon dioxide or carbon dioxide equivalent;

፱/ **"የካርበን ክሬዲት አሠራሮች"** ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የቅነሳ ተግባራት ፈጠራንና ምዝገባን እንዲሁም ከቅነሳ ተግባራት የሚመነጨዉ የካርበን ክሬዲቶችን ማረጋገጥና ለገበያ ማውጣትን የሚገዙ፤ በፓሪስ ስምምነት አንቀጽ ፮.፪ እና አንቀጽ ፮.፬፣ በዓለም አቀፍ የአቪዬሽን የካርበን ማካካሻና ቅነሳ ሥርዓት እንዲሁም በካርበን ስታንዳርድ መሠረት የተቋቋሙ የተቀናጁ የሕግ፣ የቴክኒክ እና የአስተዳደር ሥርዓቶች ናቸው፤

9/ **"Carbon Crediting Mechanisms"** refers to the structured legal, technical, and administrative systems including those established under Article 6.2 and Article 6.4 of the Paris Agreement, CORSIA, or Carbon Standard that govern the creation, registration of Mitigation Activities and the Validation/Verification, and issuance of Carbon Credits from Mitigation Outcomes within Ethiopia;

፲/ **"የካርበን ገበያ"** ማለት የልቀት ውጤቶችና ተጓዳኝ ካርበን ክሬዲቶችና ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የካርበን መብቶች፣ አስገዳጅ የንብረት መብቶችን እንደያዘ አንድ የሀብት መደብ የሚፈጠሩበት፣ የሚገበዩበትና የሚከስሙበት የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የግብይት ሥርዓት ነው፤

10/ **"Carbon Market"** means the domestic and global trading system in which Mitigation Outcomes and associated Carbon Credits and their associated Carbon Rights are created, traded, and retired as an asset class with related enforceable property rights;

፲፩/ **"የካርበን ገበያ አሳላጭ"** ማለት ገዢዎችን፣ ሻጮችንና የካርበን ክሬዲት አከናዋኞችን የሚያገናኝና የካርበን ክሬዲት ግብይቶችን የሚያመቻች ሰው ወይም አካል ነው፤

11/ **"Carbon Market Intermediary"** means a person or entity that acts as an intermediary to connect buyers, sellers, and dealers in Carbon Credits, and facilitates Carbon Credit transactions;

፲፪/ **"የዓለም አቀፍ አቪዬሽን የካርበን ማካካሻ እና ቅነሳ ሥርዓት"** ማለት በዘርፉ ውስጥ የሚደረጉ የልቀት ቅነሳ ጥረቶችን ለማሟላት በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት የተቀረጸና ከዓለም አቀፍ በረራዎች የሚወጡ የካርበን ዳይኦክሳይድ ልቀቶችን ለመቀነስ የሚያገለግል በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ነው፤

12/ **"Carbon Offsetting and Reduction Scheme for International Aviation" or "CORSIA"** means the global market-based mechanism developed by the International Civil Aviation Organization (ICAO) to reduce carbon dioxide emissions from international aviation as a complement to in-sector mitigation efforts;

፲፫/ **"የካርበን መዝገብ"** ማለት በአንድ የካርበን ስታንዳርድ ወይም ሌሎች አስገዳጅ መመዘኛዎች (የካርበን ክሬዲት ግብይትና ማክሰምን ጨምሮ) መሠረት የቅነሳ ተግባራትንና የቅነሳ ውጤቶችን ጠቅላላ ዑደት የሚከታተልና ለእያንዳንዱ የተቀነሰ፣ የተወገደ ወይም እንዲቀር የተደረገ ሜትሪክ ቶን ካርበን ዳይኦክሳይድ ወይም ተመጣጣኝ ጋዝ ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ግልጽነትን የሚያመቻች እንዲሁም ዳግም ቆጠራን የሚከላከል የዲጂታል መድረክ ነው፤

13/ **"Carbon Registry"** means a digital platform that tracks the entire cycle of Mitigation Activities and Mitigation Outcomes in accordance with a Carbon Standard or other mandatory requirements (including the trading and retirement of Carbon Credits) and assigns unique serial numbers to each metric tonne of carbon dioxide equivalent reduced, avoided or removed in order to facilitate transparency and avoid double-counting;

፲፬/ **"የካርበን መብት"** ማለት ከአንድ የቅነሳ ተግባር ጋር ከሚያያዝ የካርበን ክሬዲት የሚመነጭ የማይዳሰስ ሕጋዊ የንብረት መብት ባለቤትነትና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት መብት ሲሆን በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ የካርበን ክሬዲቶችን የመያዝ፣ የማስተላለፍ፣ የባለቤትነት መብት ጥያቄን የማንሳትና የማክሰም መብትን ይጨምራል፤

14/ **"Carbon Right"** means the legal entitlement to the intangible property rights and economic benefits arising from a Carbon Credit associated with a Mitigation Outcome, including the right to hold, transfer, claim, and retire Carbon Credits issued under this Proclamation;

፲፭/ **"የካርበን ስታንዳርድ"** ማለት የቅነሳ ተግባራትንና የቅነሳ ውጤቶችን ለመቅረጽና ለመተግበር የሚያስችል ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለው ስታንዳርድ ነው፤

15/ **"Carbon Standard"** means an internationally recognized standard for the creation and implementation of Mitigation Activities and Mitigation Outcomes;

፲፮/ **"ተመጣጣኝ ማስተካከያ"** ማለት በፓሪስ ስምምነት ውስጥ የሚገኝና የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የኢትዮጵያ የልቀት ቅነሳ ውጤቶች በሌላ ሀገር በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም ለዓለም አቀፍ የቅነሳ ዓላማዎች ሲባል በኢትዮጵያ ብሔራዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ምጥጥኖሽ ላይ እንዲመላከት በይፋ የሚፈቅድበት አስገዳጅ የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት ሲሆን ዓላማውም የካርበን ክሬዲቶች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ውስጥ በድጋሚ አለመቆጠራቸውን ማረጋገጥ ነው፤

16/ **"Corresponding Adjustment"** means the mandatory accounting procedure under the Paris Agreement whereby Mitigation Outcomes in Ethiopia that the DNA expressly authorizes to be used towards another country's NDC or for other international mitigation purposes are reflected in Ethiopia's national GHG emissions balance, in order to ensure that such Carbon Credits are not double-counted toward Ethiopia's NDC;

፲፯/ **"የተሰየመ ብሔራዊ ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ የካርበን ገበያዎችን እንዲያስተዳድርና እንዲያስተባብር በቀዳሚነት የሚሰይመው መንግስታዊ አካል ነው፤

17/ **"Designated National Authority"** or **"DNA"** means a public body assigned by the Government of Ethiopia to serve as the primary national body for the governance and coordination of Carbon Market in Ethiopia

፲፰/ **"አልሚ"** ማለት የአንድን የቅነሳ ተግባር የቴክኒክ ንድፍንና የየዕለት ትግበራን በሚመለከት ከአንድ ሃሳብ አመንጪ ወይም አካል ጋር የሚተባበር ሰው ሲሆን በአብዛኛው ጊዜ ለካርበን ክሬዲቱ ጎላፊ የሆነውን የሀሳብ አመንጪ፣ የፕሮጀክት ባለቤት ወይም አካል በመወከል ወይም አጋር በመሆን የሚሠራ ነው፤

18/ **"Developer"** is a person who collaborates with a Proponent, Project Owner or the entity for the technical design, and day-to-day implementation of the Mitigation Activity, often acting on behalf of or in partnership with the Proponent, the Project Owner or the entity responsible for the Carbon Credit;

፲፱/ **"የልቀት ቅነሳ የግዢ ስምምነት"** ማለት በአንድ የካርበን ገበያ ማዕቀፍ ውስጥ የሚመነጩ ወይም የሚዘዋወሩ የልቀት ቅነሳዎችን ወይም ማስወገዶችን ግዢ እና ሽያጭ የሚገዛ ውል ነው፤

19/ **"Emission Reductions Purchase Agreement" or "ERPA"** means a contract governing the purchase and sale of emission reductions or removals generated or transferred under a carbon market framework;

፳/ **"የአካባቢያዊና የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓቶች"** ማለት የቅነሳ ተግባራት የአካባቢ ማኅበረሰቦችን ወይም ሥነ-ምኅዳሮችን የማይጎዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አስገዳጅ ሥርዓቶች ናቸው፤

20/ **"Environmental and Social Safeguards"** means the mandatory rules ensuring Mitigation Activity do not harm local communities or ecosystems;

፳፩/ **"የሙቀት አማቂ ጋዝ"** ማለት የፀሐይን የሙቀት ጨረር አምቀው የሚይዙ በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ ምክንያት በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ጋዞች ሲሆኑ፣ ካርበን ዳይኦክሳይድን፣ ሜቴንን፣ ናይትረስ ኦክሳይድን እና በፓሪስ ስምምነት ውስጥ የተገለጹ ሌሎች ፍሎሪኔትድ ጋዞችን ያካትታል፤

21/ **"Greenhouse Gas"** or **"GHG"** means those natural and anthropogenic gaseous constituents of the atmosphere that trap thermal radiation, including carbon dioxide, methane, nitrous oxide, and other fluorinated gases identified under the Paris Agreement;

፳፬/ **"በዓለም አቀፍ ደረጃ የተላለፈ የልቀት ቅነሳ ውጤት"** ማለት ተጨባጭ፣ ተጨማሪ እና የተረጋገጠ የሆነና የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ከከባቢ አየር የመቀነሱ፣ ወይም የሙቀት አማቂ ጋዞች ከሌሎች ምንጮች የመወገዱ ወይም የመገደቡ ማረጋገጫ ሲሆን ይህም በካርበን ዳይኦክሳይድ ወይም በካርበን ዳይኦክሳይድ አቻ የሚለካና የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ለሌላ ወገን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅድ ወይም በሌላ ዓለም አቀፍ የቅነሳ ዓላማ ውስጥ እንዲቆጠር የፈቀደው ቅነሳ ወይም መወገድ ነው፤

22/ **"Internationally Transferred Mitigation Outcome" or "ITMO"** means a real, additional and verified reduction in GHG emissions from the atmosphere or removal and avoidance of GHG from other sources, measured in carbon dioxide or carbon dioxide equivalent and which has been authorized by the DNA for use toward an NDC or other international mitigation purposes;

፳፭/ **"መሬትን መሠረት ያደረገ የቅነሳ ተግባር"** ማለት የካርበን ክሬዲቶችን ወይም ገበያ-ነክ ያልሆኑ ጥቅሞችን ለማመንጨት በማሰብ በግብርና፣ በደን ልማት ወይም በሌላ የመሬት አጠቃቀም ውስጥ የሚከናወንና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ለመቀነስ ወይም በአንድ ቦታ ለማከማቸት ያለመ የቅነሳ ተግባር ነው፤

23/ **"Land-based Mitigation Activity"** means any Mitigation Activity in the agriculture, forestry, or other land-use aimed at reducing and/or sequestering GHG emissions to generate Carbon Credits or non-market benefits;

፳፮/ **"ማምለጥ"** ማለት እንደየሁኔታው ከቅነሳ ተግባሩ ዳርቻ ውጪ በሚገኙ ምንጮች አማካኝነት የሚከሰትና ከቅነሳ ተግባሩ አኳያ ሊለካና በቅነሳ ተግባሩ ሊመካኝ የሚችል የተጣራ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ጭማሪ ወይም በቅነሳ ተግባሩ ምክንያት ከቅነሳ ተግባሩ ዳርቻ ውጪ በካርበን በምንጮች ምክንያት የሚከሰት የሙቀት አማቂ ጋዞች መጨመር ወይም በካርበን ማከማቻዎች ውስጥ የተጠራቀመ የካርበን ክምችት መቀነስ ነው፤

24/ **"Leakage"** means the net positive change of GHG emissions by sources which occurs outside the boundary of the Mitigation Activity and which is measurable and attributable to the Mitigation Activity, or the increase in GHG emissions by sources or decrease in carbon stock sequestered in carbon pools which occurs outside the boundary of the Mitigation Activity as a result of the Mitigation Activity, as applicable;

፳፩/ **"የማጽደቅ ደብዳቤ"** ማለት የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የሚሰጠውና አንድን የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ የሚያጸድቅና አንድ ሃሳብ አመንጪ የቅነሳ ተግባሩን በመዝገብ ውስጥ ወደ ማስመዝገብ እንዲያልፍ የሚፈቅድ ይፋዊ ሰነድ ነው፤

25/ **"Letter of Approval"** means a formal document issued by the DNA endorsing a Mitigation Activity Design Document and permitting a Proponent to proceed with registration of the Mitigation Activity by a Registry;

፳፪/ **"የይሁንታ ፈቃድ ደብዳቤ"** ማለት በፓሪስ ስምምነት መሠረት የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮ መሠረት አንድን የትብብር አሠራርና በውስጡ ያሉ አካላትን የሚያጸድቅበት እና/ወይም ከአንድ የቅነሳ ተግባር የመነጩና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሚተላለፉ የቅነሳ ውጤቶች ወደሌላ አገር ወይም አካል እንዲተላለፉ የሚፈቅድበት ይፋዊና ሉዓላዊ ሰነድ ነው፤

26/ **"Letter of Authorization"** means a formal, sovereign document issued under Article 6 of the Paris Agreement by which the DNA approves a Cooperative Approaches, its entities, and/or authorizes the transfer of ITMOs generated by a Mitigation Activity to another country or entity;

፳፫/ **"የተቃውሞ አለመኖር ደብዳቤ"** ማለት የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን፣ በአንድ የቅነሳ ተግባር ሀሳብ አመንጪ የተቀረጸውን የቅነሳ ተግባር የመነሻ ሀሳብ በመገምገም የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ ወደማዘጋጀት እንዲያልፍ የሚሰጠው የመጀመሪያ ደረጃ የማጽደቂያ ሰነድ ነው፤

27/ **"Letter of No Objection"** means is a preliminary approval document issued by the DNA permitting a Proponent to proceed with the development of a Mitigation Activity Design Document;

፳፬/ **"ሚኒስቴር"** ማለት የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ነው፤

28/ **"Ministry"** means is the Ministry of Planning and Development;

፳፭/ **"የቅነሳ ተግባር"** ማለት የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት ለመቀነስ፣ ለማስቀረት ወይም ለማስወገድ የተቀረጸና የቅነሳ ውጤቶችን እንዲሁም ተያያዥ የካርበን ክሬዲቶችን የሚያስገኝ አንድ ልዩ ፕሮጀክት፣ ፕሮግራም ወይም ፖሊሲ ነው፤

29/ **"Mitigation Activity"** means a specific project, program, or policy designed to reduce, avoid, or remove GHG emissions that generate Mitigation Outcomes and the associated carbon credits;

፴፩/ **"የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ"** ማለት በቅነሳ ተግባሩ ላይ ተፈጻሚ በሆኑ ዝርዝር መመሪያዎች መሠረት የሚዘጋጅ፣ የአንድን የካርበን ፕሮጀክት ወይም የካርበን ፕሮግራም ንድፍ፣ አተገባበርና የክትትል ሂደት በዝርዝር የሚገልጽ አጠቃላይ እና ዝርዝር የቴክኒክ ሰነድ ነው፤

30/ **"Mitigation Activity Design Document" or "MADD"** means a comprehensive and detailed technical document that sets out in detail the design, implementation, and monitoring of a Carbon Project or Carbon Program, as applicable, in accordance with the specific rules and requirements of the applicable Mitigation Activity;

፴፪/ **"የቅነሳ ተግባር መነሻ ኃሳብ"** ማለት የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለመቀነስ፣ ለማስቀረት ወይም ለማስወገድ ስለታቀደበት ፕሮጀክትና ከፕሮጀክቱ መንጭተው በካርበን ገበያዎች ላይ ሊሻሻጡ ስለሚችሉ የተረጋገጡ የካርበን ክሬዲቶች የመጀመሪያ ደረጃ ማብራሪያ የሚሰጥ አጭር ሰነድ ነው፤

31/ **"Mitigation Activity Idea Note" or "(MAIN)"** means a concise document that provides a preliminary description of an initiative designed to reduce, avoid, or remove GHG emissions, resulting in certified carbon credits that can be traded in Carbon Markets;

፴፫/ **"የቅነሳ ውጤት"** ማለት (፩) በተቀመጡ ድንጋጌዎችና መመዘኛዎች መሠረት የተለካ፣ ክትትል የተደረገበት፣ ሪፖርት የተደረገና የተረጋገጠ እንዲሁም (፪) ትክክለኛ፣ ተጨማሪ እና እንደየሁኔታው ደግሞ ቋሚ መሆኑ በገለልተኛ አካል የተረጋገጠ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መቀነስ፣ የሙቀት አማቂ ጋዞች ወደ ማከማቻዎች የመወገዳቸው መጠን መጨመር ወይም የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ማስቀረት ነው፤

32/ **"Mitigation Outcome"** means the independently Verified reduction of GHG emissions, enhancement of GHG emission removals in sinks, or avoidance of GHG emissions, that is (i) measured, monitored, reported, and Verified in accordance with stipulated rules and requirements and (ii) real, additional, and, if applicable, Permanent;

፴፬/ **"በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ"** በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፬ ሥር የተቀመጠውን ትርጓሜ ይይዛል፤

33/ **"Nationally Determined Contribution" or "NDC"** has the meaning given to it in Article 4 of the Paris Agreement;

፴፬/ **"መሬትን መሠረት ያላደረገ ፕሮጀክት"** ማለት የየብስ ሥነ-ምሕዳርሮችን ከማስተዳደር ወይም ከማጎልበት ውጭ በሆኑ ቴክኖሎጂያዊ ወይም ኢንዱስትሪያዊ ጣልቃ ገብ እርምጃዎች አማካኝነት የመሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለመቀነስ ወይም ለማስቀረት የሚተገበር ማንኛውም የቅነሳ ውጤት ነው፤

34/ **"Non-Land-based Mitigation Activity"** means any Mitigation Outcome implemented through technological or industrial interventions designed to reduce or avoid GHG emissions through means other than the management or enhancement of terrestrial ecosystems;

፴፭/ **"በመካሄድ ላይ ያሉ የካርበን ቅነሳ ተግባራት"** ማለት ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ትግበራ የጀመሩ የቅነሳ ተግባራት ናቸው፤

35/ **"Ongoing Carbon Mitigation Activities"** means those Mitigation Activities that have started implementation before the enactment of this Proclamation;

፴፮/ **"ወገን"** ማለት በካርበን ክሬዲቶች ግብይት፣ ፈጠራ ወይም ማክሰም ውስጥ የሚሳተፍ ገዢ ወይም ሻጭ ነው፤

36/ **"Party"** means any entity buyer, or seller involved in the transaction, creation, or retirement of carbon credits;

፴፯/ **"ቋሚነት"** ማለት [የጸደቀውን] የቅነሳ ተግባር በሚመለከቱ ድንጋጌዎችና መመዘኛዎች ላይ በተቀመጠው ጊዜ መሠረት የመሙቀት አማቂ ጋዞች ከከባቢው አየር ተቀንሰው፣ ሳይለቀቁ ወይም ተወግደው የሚቆዩበት ረዥም የጊዜ ቆይታ ሲሆን "ቋሚነት" ከዚሁ ጋር ተዛማጅ የሆነ ትርጉም ይኖረዋል፤

37/ **"Permanence"** means the long term duration of the reduction, avoidance and sequestration of GHG emissions from the atmosphere for the period stipulated by the rules and requirements of the [approved] Mitigation Activity, and "**Permanence**" shall have a corresponding meaning;

፴፰/ **"የፕሮጀክት ባለቤት"** ማለት የቅነሳ ተግባሩ የሚከናወንበትና የካርበን መብቶቹ የሚመነጩበት መሬት፣ ሀብት ወይም ንብረት ሕጋዊ የባለቤትነት፣ የኪራይ ወይም ሌላ የባለቤትነት መብት ያለው ሰው ነው፤

38/ **"Project Owner"** is a person that holds the legal title, lease, or other proprietary rights to the land, resource, or asset where the Mitigation Activity is implemented and from which the Carbon Rights originate;

፴፱/ **"የሀሳብ አመንጪ"** ማለት በተቀመጡት ደንቦችና መመዘኛዎች መሠረት ለቅነሳ ተግባሩ ኀላፊ የሆነና ከተገዢነት፣ ሪፖርት ከማድረግ፣ ከተግባቦትና ከተሰየመው ባለሥልጣንና መዝገብ ጋር የሚኖር መስተጋብርን በሚመለከት በቀዳሚነት ኀላፊ የሆነ አካል ወይም አካላት ነው/ናቸው፤

39/ **"Proponent"** is the primary entity or entities responsible for the Mitigation Activity and all compliance, reporting, and communication and engagement with the DNA and Registry in accordance with the stipulated rules and requirements;

፵/ **"ቅነሳ"** ማለት ከአንድ ልዩ ምንጭ የሚለቀቁ ሙቀት አማቂ ጋዞች ከተቀመጠ የንጽረት መነሻ አንጻር ሊለካ በሚችል መጠን መቀነሳቸው ነው፤

40/ **"Reduction"** means the measurable decrease of GHG emissions from a specific source relative to an established Baseline;

፵፩/ **"መዝጋቢ"** ማለት የካርበን መዝገቡ ኀላፊ ነው፤

41/ **"Registrar"** means the registrar of the Carbon Registry;

፵፪/ **"ማስወገድ"** ማለት የሙቀት አማቂ ጋዞች ከከባቢ አየሩ ውስጥ ባዮሎጂካዊ ወይም ቴክኒካዊ የሆነ መወገድና በአንድ ባዮሎጂካዊ ወይም ጂኦሎጂካዊ የካርበን ማከማቻ ውስጥ በቋሚነት መጠራቀም ማለት ነው፤

42/ **"Removal"** means the biological or technical removal of GHG emissions from the atmosphere and Permanent sequestration in a biological or geological carbon sink;

፵፫/ **"መክሰም"** ማለት የአንድ የካርበን ክሬዲት ወደፊት ሊሸጥ፣ ሊገበይ ወይም ሊተላለፍ እንዳይችል ሆኖ በቋሚነትና በማይቀለበስ ሁኔታ ከገዘውውር መውጣት ነው፤

43/ **"Retirement"** means the permanent and irreversible removal of a Carbon Credit from circulation so that it can no longer be sold, traded, or transferred;

፵፬/ **"ቅልበሳ"** ማለት በቅነሳ ተግባሩ ላይ በተደረገ ለውጥ ምክንያት የቅነሳው ውጤት ከሆነ የካርበን ክሬዲት ላይ የሙቀት አማቂ ጋዞች ተመልሰው ወደ ከባቢ አየር መለቀቃቸው ነው፤

44/ **"Reversal"** means the release of the GHG emissions from a Mitigation Outcome that is a Carbon Credit back into the atmosphere due to change in the Mitigation Activity;

፵፭/ **"መሰረዝ"** ማለት በሀሳብ አመንጪው ወይም በፕሮጀክቱ ባለቤት ማጭበርበር ወይም የሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት የአንድ የካርበን ክሬዲት፣ የቅነሳ ውጤት ወይም የቅነሳ ተግባር መሰረዝ ነው፤

45/ **"Revocation"** means the revocation of a Carbon Credit, a Mitigation Outcome, or a Mitigation Activity due to fraud or malfeasance of the Proponent or the Project Owner;

፵፮/ **"ማረጋገጥ"** ማለት አንድ ገምጋሚና አረጋጋጭ አካል የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት ቅነሳ ትክክለኛ፣ ተጨባጭ፣ ተጨማሪ፣ ግልጽና ለተዘረጉ ስታንዳርዶች ተገዢ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያከናውነው ገለልተኛ የሦስተኛ ወገን ምዘና ነው፤

46/ **"Verification"** means an independent third-party assessment of GHG assertions by a Validation and Verification Body (VVB) to verify that reported emission reductions or removals are accurate, real, additional, transparent, and compliant with established standards;

፵፯/ **"በፈቃደኛነት ላይ የሚመሠረት የካርበን ገበያ"** ማለት አካላት በፈቃደኛነት ላይ ተመሥርተው የካርበን ክሬዲቶችን የሚፈጥሩበትን የሚገበያዩበት ገበያ ነው፤

47/ **"Voluntary Carbon Market"** means the market in which entities voluntarily create and transact in Carbon Credits;

፵፰/ **"ገምጋሚና አረጋጋጭ አካል"** ማለት አንድ የካርበን ስታንዳርድ ዕውቅና የተሰጠው ገለልተኛና ዓለም አቀፍ ገምጋሚና አረጋጋጭ አካል ነው፤

48/ **"Validation and Verification Body" or "VVB"** means the independent, internationally accredited validation and verification body that is accredited by a Carbon Standard;

፵፱/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ሰው ነው፤

49/ **"Person"** means any natural or juridical person;

፶/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ የሴትንም ጾታ ይጨምራል።

50/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ፡-

፩/ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በሚከናወኑ የቅነሳ ተግባራት በሙሉ፤

፪/ በፓሪስ ስምምነት አንቀጽ ፮ በፈቃደኛነት ላይ በተመሠረተው የካርበን ገበያ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ሌሎች የቅነሳ ተግባራትን በሚያካትቱ ወይም በቅነሳ ተግባራት ላይ ተጽዕኖ በሚኖራቸው የካርበን ግብይት አሠራሮች፣ የቅነሳ ውጤቶች ወይም የካርበን ክሬዲቶች፤

3. Scope of Application

This Proclamation shall apply to:

1/ All Mitigation Activities undertaken within the territory of Ethiopia;

2/ Article 6 of the Paris Agreement, the Voluntary Carbon Market, and other Carbon Crediting Mechanisms that involve or affect Mitigation Activities, Mitigation Outcomes, or Carbon Credits in Ethiopia;

፫/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑ ወይም ዝውውራቸው፣ አጠቃቀማቸው ወይም መክሰማቸው የሚከናወነው በየትኛውም ሥፍራ ቢሆን በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ በሚኖራቸውና የካርበን ክሬዲቶችን ወይም የቅነሳ ውጤቶችን በሚያካትቱ ግብይቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

3/ All transactions involving Carbon Credits or Mitigation Outcomes in, from or affecting Ethiopia, regardless of the jurisdiction where the transfer, use, or retirement occurs.

፬. ዓላማዎች

4. Objectives

የዚህ አዋጅ ዓላማዎች

The objectives of this Proclamation are to:

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከናወኑ የቅነሳ ተግባራት ትግበራ የሚሆን አጠቃላይ የሕግ ማዕቀፍ መዘርጋት፤

1/ Establish a comprehensive legal framework for implementation of all Mitigation Activities in Ethiopia;

፪/ ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በሚያስችልና ከኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ጋር በተጣጣመ መንገድ የኢትዮጵያን አጠቃላይ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ዒላማዎችና የዝቅተኛ ልቀት የልማት ስትራቴጂዎችን መደገፍ፤

2/ Create incentives and implement initiatives and Mitigation Activities to support the overall GHG emission targets, and low emissions development strategy of Ethiopia in a manner that promotes sustainable development and is consistent with Ethiopia's NDC;

፫/ በኢትዮጵያ ውስጥ የካርበን ገበያ ማቋቋም እንዲሁም ከኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ጋር በሚጣጣም መልኩ በሚከናወን የካርበን ክሬዲቶች ግብይት አማካኝነት የአየር ንብረት ፋይናንስና ኢንቬስትመንትን ማመቻቸት ናቸው።

3/ Establish a Carbon Market in Ethiopia in order to facilitate climate finance and investment through the trading of Carbon Credits in a manner that is consistent with Ethiopia's NDC.

፭. መርሆች

5. Principles

ይህ አዋጅ በፓሪስ ስምምነት መርሆችና በሚከተሉት ፍላጎቶች መነሻነት የሚመራ ይሆናል፦

This Proclamation shall be guided by the principles of the Paris Agreement and the intent to:

፩/ ተጨማሪነት፤

1/ Additionality;

፪/ ዳግም ቆጠራን ማስቀረት፤

2/ Avoiding double counting;

፫/ አካባቢያዊ ደኅንነት፤

3/ Environmental integrity;

፬/ አካታችነት፤

4/ Inclusivity;

፭/ የአካባቢያዊና የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓቶች፤

5/ Environmental and social safeguards;

፮/ ፍትሐዊና ርቱዕ የጥቅም መጋራት፤ እና

6/ Fair and equitable benefit-sharing; and

፯/ ተጠያቂነትና ግልጽነት፡፡

ክፍል ሁለት

የቅነሳ ተግባራት የሚመሩባቸው ሥነ-ሥርዓቶች

፮. የቅነሳ ተግባር ማመልከቻ

፩/ ማንኛውም የቅነሳ ተግባር በኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ወይም የጸና ሆኖ የካርበን ክሬዲቶችን ጨምሮ ማንኛውንም የቅነሳ ውጤት የሚያስገኘው በተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የጸደቀ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በመመዝገብ የተቃውሞ አለመኖር ደብዳቤ እንዲሁም የቅነሳ ተግባር የማጽደቅ ደብዳቤ ሳያገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የቅነሳ ተግባር ማከናወን አይፈቀድለትም፡፡

፫/ አንድ በቅነሳ ተግባር ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ያለው ሀሳብ አመንጪ በቅነሳ ተግባሩ ላይ ተቃውሞ አለመኖሩን የሚጠይቅበት ማመልከቻ የመጀመሪያ ክፍል የሚሆነውን የቅነሳ ተግባር የመነሻ ሰነድ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በተደነገገው ቅርጽ መሠረት በማዘጋጀት የተቀመጠውን የአስተዳደር ክፍያ መክፈሉን ከሚያስረዳ ሰነድ ጋር አብሮ ማስገባት አለበት፡፡

፬/ ሀሳብ አመንጪው መንግስታዊ ያልሆነ አካል ሲሆን የቅነሳ ተግባር የመነሻ ሀሳብ ሰነዱ አግባብነት ካለው የኢትዮጵያ የዘርፍ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ወይም ኤጀንሲ ከሚሰጥና የታሰበው የቅነሳ ተግባር ከአገሪቱ የዘርፍ ፖሊሲዎችና ዕቅዶች ጋር የሚጣጣም መሆኑን ከሚያረጋግጥ የዘርድ የድጋፍ ደብዳቤ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት፡፡

7/ Accountability and transparency.

PART TWO

PROCEDURES FOR DEVELOPING MITIGATION ACTIVITY

6. Application for a Mitigation Activity

1/ No Mitigation Activity in Ethiopia is legal or valid, and may generate any form of Mitigation Outcome including Carbon Credits unless and until it is approved by the DNA.

2/ No person shall undertake a Mitigation Activity in Ethiopia without being registered by the DNA and receiving a Letter of No Objection and a Letter of Approval of the Mitigation Activity issued by the DNA.

3/ A Proponent intending to engage in a Mitigation Activity shall submit a Mitigation Activity Idea Note (MAIN) forming the first part of an application seeking No Objection of the Mitigation Activity to the DNA in the prescribed form, together with evidence of payment of the prescribed administrative fee.

4/ Where the Proponent is a non-state entity, the submission of the MAIN shall be accompanied by a letter of sectoral support issued by the relevant Ethiopian sectoral ministry or agency confirming alignment of the proposed Mitigation Activity with Ethiopia's sectoral policies and plans.

፭/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን፣ አንድ የተሟላ የቅነሳ ተግባር የመነሻ ሀሳብ ሰነድና የመጀመሪያ ደረጃ ማመልከቻ በደረሰው በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን በመመርመር፡-

ሀ) የመነሻ ሀሳብ ሰነዱ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ውስጥ ያሉ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ከሆነ የተቃውሞ አለመኖር ደብዳቤ መስጠት፤ ወይም

ለ) የቅነሳ ተግባር የመጀመሪያ ማመልከቻው ውድቅ መሆኑን የመነሻ ሀሳቡን በማጣቀስ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ያደረጉትን ዝርዝር ምክንያቶች በመጥቀስ ለሃሳብ አመንጪው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ The DNA shall, within 30 (Thirty) days of receiving a complete MAIN and preliminary application, review the MAIN and:

a) issue a Letter of No Objection for the Mitigation Activity, where MAIN demonstrates that the Mitigation Activity meets the requirements for a Mitigation Activity set out in a guideline to be issued by the DNA; or

b) notify the Proponent in writing of the refusal of the preliminary application for approval of the Mitigation Activity, providing detailed reasons for such a decision with reference to the MAIN.

፮/ የሀሳብ አመንጪው ማመልከቻ ለአንድ የቅነሳ ተግባር የሚጠየቁት የብቁነት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማሳየት እንዲሁም የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣውና በየጊዜው በሚያሻሽለው መመሪያ ውስጥ በተቀመጠው ቅጽና ይዘት መሠረት መቅረብ አለበት፡፡

6/ The Proponent's application shall demonstrate that the eligibility criteria for a Mitigation Activity have been met and be in the form and substance in the guideline to be issued by the DNA, and updated from time to time;

፯/ መሬትን መሠረት ያደረጉ የቅነሳ ተግባራትን ያቀደው ሀሳብ አመንጪ ከመነሻ ሀሳቡ ጋር ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የመሬት መጠቀም መብትን የሚያሳይ ሰነድ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

7/ The Proponent shall, demonstrate that the Proponent of Land-based Mitigation Activities submit the Project Owner's valid land use rights document to accompany with the MAIN, issued by the competent authority, to the DNA.

፰/ የሀሳብ አመንጪው የቅነሳ ተግባሩ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያስቀምጠውና በየጊዜው በሚያሻሽለው ቅጽ መሠረት መመዘኛዎችን እንደሚያሟላ ማሳየት አለበት፡፡

8/ The Proponent shall demonstrate that the Mitigation Activity shall fulfill the elements in the form to be issued by the DNA, and updated from time to time.

፯. <u>የቅነሳ ተግባራት መጽደቅ</u>

፩/ ሀሳብ አመንጪው የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣውና በየጊዜው በሚያሻሽለው መመሪያ መሠረት ዝርዝር የቅነሳ ተግባራት የንድፍ ሰነድ አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ ሀሳብ አመንጪው የተቃውሞ አለመኖር ደብዳቤ በተሰጠው በ፮ (ስድስት) ወራት ውስጥ ዝርዝር የቅነሳ ተግባራት የንድፍ ሰነድ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት።

፫/ ሀሳብ አመንጪው የተቃውሞ አለመኖር ደብዳቤው በወጣ በስድስት (፮) ወራት ውስጥ ዝርዝር የቅነሳ ተግባራት የንድፍ ሰነድ ማቅረብ ካልቻለ የዘገየበትን ምክንያቶች በመጥቀስ ከ፮ (ስድስት) ወራት የማይበልጥ የጊዜ ማራዘሚያ እንዲሰጠው ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

፬/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ሀሳብ አመንጪው ያቀረባቸውን ምክንያቶች ከተቀበለ የጊዜ ማራዘሚያው ከተፈቀደበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠርና ከ፮ (ስድስት) ወራት ለማይበልጥ ጊዜ የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ የማቅረቢያ ቀን ገደቡን ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

፭/ የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው ወይም የቅነሳ ተግባሩ እንዲመዘገብ በታሰበበት የካርበን ስታንዳርድ ሥር በሚገኝና ተፈጻሚነት በሚኖረው መመሪያ ውስጥ በሚገኙ ሥነ-ዘዴዎች፣ ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች መሠረት መዘጋጀት አለበት፡፡

7. <u>Approval of Mitigation Activities</u>

1/ The Proponent shall complete a detailed Mitigation Activity Design Document (MADD) in accordance with the guideline to be issued by the DNA, and updated from time to time.

2/ The Proponent shall, within 6 (Six) months of the date of the Letter of No Objection, submit the detailed MADD to the DNA.

3/ If the Proponent is unable to submit the detailed MADD on or before the date that is six (6) months after the date of the Letter of No Objection, it may request the DNA for an extension of not more than 6 (Six) months, by stating the reasons for the delay.

4/ Where the DNA accepts the reasons stated by the Proponent, it may grant the extension of the deadline for the MADD for a period not more than 6 (Six) months from the date that the extension is granted.

5/ The MADD shall be prepared in accordance with the methodologies, rules, and procedures of the applicable guidance of the DNA or Carbon Standard under which the Mitigation Activity seeks registration.

፮/ የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱ የሚቀርብበት ቅጽና ይዘት እንዲሁም አብረው መቅረብ የሚኖርባቸው ሰነዶች የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

6/ The form and substance of, and documents that accompany, the MADD shall be set out in the guideline to be issued by the DNA.

፯/ የሀሳብ አመንጪው በራሱ ወጪ የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱን ተፈጻሚነት ባለው የካርበን ስታንዳርድና ሥነ-ዘዴ ውስጥ በሚገኙ መመዘኛዎች መሠረት ብቁ በሆነ ገምጋሚና አረጋጋጭ አካል ማስገምገም አለበት፤

7/ The Proponent shall, at its own cost and expense, have the MADD validated by a qualified VVB consistent with the requirements of the applicable Carbon Standard and methodology.

፰/ የሀሳብ አመንጪው በገምጋሚና አረጋጋጭ አካል የተረጋገጠውን የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፤

8/ The Proponent shall submit the VVB validated MADD to the DNA.

፱/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በገምጋሚና አረጋጋጭ አካል የተረጋገጠውን የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ የተቀመጠው መስፈርት መሟላቱን ለመፈተሽ በዚህ አዋጅ ለሚቋቋመው የኢትዮጵያ የበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

9/ The DNA shall forward the VVB validated MADD to the Ethiopia's Inter-Sectoral Carbon Market Committee, established by this Proclamation, for fulfilment of the stipulated requirements check.

፲/ የበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴው የተረጋገጠው የቅነሳ ተግባራት የንድፍ ሰነዱ በደረሰው በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ መርምሮ የሰነዱን መጽደቅና ግምገማ በሚመለከት ምክረ-ሐሳቦቹን ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡

10/ The Inter-Sectoral Carbon Market Committee shall within thirty (30) days of receipt of the validated MADD shall review and submit its recommendation on the approval and the registration of the validated MADD to the DNA.

፲፩/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴው ሪፖርትና ምክረ-ሀሳቦች በደረሱት በ፲፭ (አሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ፡-

11/ The DNA shall, within 15 (Fifteen) days of the receipt of the report and recommendations of the Inter-Sectoral Carbon Market Committee:

ሀ) ሰነዱን በማጽደቅና የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለሀሳብ አመንጪው የማጽደቅና የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤ ይሰጣል፣ ወይም

ለ) ምክንያቶቹን በጽሑፍ በመዘርዘር የቅነሳ ተግባሩን ያግዳል ወይም ውድቅ ያደርጋል።

፲፪/ በተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የጸደቀ የቅነሳ ተግባር በኢትዮጵያ የካርበን መዝገብ ውስጥ መመዝገብ አለበት።

፲፫/ ሁሉም የቅነሳ ተግባራት ተጨባጭ አሉታዊ አካባቢያዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖዎችን በሚከላከል፣ በሚቀንስ ወይም በሚያለዝብ እንዲሁም ለአካባቢ ማኅበረሰቦችና ተፈጥሮአዊ ከባቢው አዎንታዊ የቅነሳ ውጤቶችን በሚያጎለብት መንገድ መነደፍና መተግበር አለባቸው።

፲፬/ የሀሳብ አመንጪዎች እንደ አካባቢያዊ ደኅንነትና ማኅበራዊ ርትዕ ላሉ የአካባቢያዊና ማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓት መርሆችና የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ለሚያደርገው መደበኛ ቁጥጥር ተገዢ መሆን አለባቸው።

፰. <u>የቅነሳ ተግባራት ትግበራ</u>

፩/ አንድ የሀሳብ አመንጪ የማጽደቅና የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤ በተሰጠው በስድስት (፮) ወራት ውስጥ የቅነሳ ተግባሩን ተጨባጭ ትግበራ መጀመር አለበት።

a) approve and issue a Letter of Approval and Registration of the Mitigation Activity to the Proponent upon payment of the administrative fees; or

b) suspend or reject the Mitigation Activity, setting out the reasons in writing.

12/ A Mitigation Activity that is approved by the DNA shall be registered in the Ethiopia Carbon Registry.

13/ All Mitigation Activities shall be designed and implemented in a manner that prevents, minimizes, and mitigates materially adverse environmental and social impacts, and enhances positive Mitigation Outcomes for local communities and the natural environment.

14/ Proponents shall comply with the pillars of the Environmental and Social Safeguards such as environmental integrity and social equity and they shall be subject to regular oversight by the Environmental Protection Authority.

8. <u>Implementation of Mitigation Activities</u>

1/ A Proponent shall commence the physical implementation of the Mitigation Activity within 6 (Six) months from the date of the Letter of Approval and Registration.

፪/ ሀሳብ አመንጪው የቅነሳ ተግባሩን በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መተግበር መጀመር ካልቻለ፦

ሀ) ሳይጀምር እንዲቆይ ያደረገውን ተገቢ ምክንያት በመግለጽ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ለአንድ ጊዜ ብቻ ቀነ-ገደቡን ከስድስት (፮) ወራት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያራዝምለት ማመልከቻ ማቅረብ፤ ወይም

ለ) ከታሰበው የቅነሳ ተግባር መውጣቱን ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ Where a Proponent is unable to commence implementation of the Mitigation Activity within the period stipulated in Sub-Article (1), the Proponent may:

a) apply to the DNA for a one-time extension of no more than 6 (Six) months, providing a valid justification for the delay; or

b) notify the DNA in writing of its withdrawal from the Mitigation Activity.

፫/ በዚህ አንቀጽ ውስጥ በተቀመጡት የጊዜ ገደቦች ውስጥ ትግበራን አለመጀመር የማጽደቅና የምዝገባ ማረጋገጥ ደብዳቤ መሰረዝንና የቅነሳ ተግባሩን ከካርበን መዝገብ መወገድን ያስከትላል፡፡

3/ Failure to commence implementation within the periods specified in this Article shall result in the automatic cancellation of the Letter of Approval and Registration and the removal of the Mitigation Activity from the Carbon Registry.

፬/ የሀሳቢ አመንጪዎች፣ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በሕግ የተሰጧቸውን የመሬት ባለይዞታነት መብቶችን ማክበር አለባቸው፡፡ ማንኛውም የቅነሳ ተግባር አስቀድሞ የተዘጋጀ፣ ግልጽና በጋራ ስምምነት የተደረገበት የመልሶ መስፈርና የካሳ ዕቅድ ሳይኖር ሰዎችን ያለፈቃዳቸው ከቀዬያቸው ወይም ከመተዳደሪያቸው ማፈናቀል የለበትም፡፡

4/ Proponents shall respect the statutory land tenure rights of local communities and no Mitigation Activity shall result in the involuntary physical or economic displacement of persons without a prior, transparent, and mutually agreed-upon resettlement and compensation plan.

፫/ እያንዳንዱ የቅነሳ ተግባር፣ በቅነሳ ተግባሩ አካባቢያዊና ማኅበራዊ አፈጻጸም ተጽዕኖ የደረሰባቸው ሰዎች ቅሬታዎቻቸውንና አቤቱታዎቻቸውን የሚያቀርቡበትና መፍትሔ የሚያገኙበት ተደራሽ፣ ግልጽና ገለልተኛ የሆነ የቅሬታ አፈታት አሠራር ያለው ወይም እንደዚህ ዓይነት አሠራር ባለው የካርበን ስታንዳርድ የሚገዛ መሆን አለበት፡፡

5/ Each Mitigation Activity shall have, or be subject to a Carbon Standard that has, an accessible, transparent, and independent grievance mechanism to receive and facilitate the resolution of concerns and complaints raised by persons affected by the Mitigation Activity's environmental and social performance.

፬/ በዚህ አንቀጽ ሥር የተቀመጡትን የአካባቢያዊና ማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓቶች አለማክበር፣ የማጽደቅና የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤና የይሁንታ ፈቃድ ደብዳቤ መሰረዝን እንዲሁም ከቅነሳ ተግባሩ ጋር ከሚያያዙ የቅነሳ ውጤቶች የሚመነጩ የካርበን ክሬዲቶች መታገድን ወይም ወደፊት መሰረዝን ሊያስከትል ይችላል፡፡

6/ Failure to adhere to the Environmental and Social Safeguards outlined in this Article may result in the suspension or revocation of the Mitigation Activity's Letter of Approval and Registration, Letter of Authorization, and the suspension or future cancellation of Carbon Credit issuances from Mitigation Outcomes associated with the Mitigation Activity.

፱. ክትትል፣ ሪፖርት ማድረግና ማረጋገጥ

9. Monitoring, Reporting and Verification

፩/ የሀሳብ አመንጪው ሁሉም የተመዘገቡ የቅነሳ ተግባራት በጸደቀው የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ፣ መጀመሪያ በተገባው የፈቃድ ቃልና ሁኔታዎች፣ ተፈጻሚነት ባለው የካርበን ስታንዳርድ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መመዘኛዎች መሠረት መተግበራቸውን ለማረጋገጥ መደበኛ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

1/ All registered Mitigation Activities shall be regularly monitored by the Proponent in order to ensure that they are implemented in accordance with the approved MADD, the terms and conditions of the initial approval, the applicable Carbon Standard, and the requirements of this Proclamation.

፪/ የሀሳብ አመንጪዎች የቅነሳ ተግባራቱን አፈጻጸምና የቅነሳ ውጤቶችን እንዲሁም ማንኛውንም ከመጀመሪያው የንድፍ ሰነድ ዕቅድ ውጪ የተፈጸሙ ተግባራትን የሚዘረዝሩ ዓመታዊ የክትትል ሪፖርቶችን ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ማቅረብ አለባቸው፡፡

2/ Proponents are required to submit annual monitoring reports detailing the performance and Mitigation Outcomes of the Mitigation Activity and any deviations from the original plan to the DNA.

፫/ የሀሳብ አመንጪው ከተመዘገበው የቅነሳ ተግባር ለሚገኙ የቅነሳ ውጤቶች የካርበን ክሬዲቶች ከመሰጠታቸው በፊት በገምጋሚና አረጋጋጭ አካል መረጋገጥ አለባቸው፡፡

3/ The Proponent shall cause the Mitigation Outcomes resulting from the registered Mitigation Activity to be successfully Verified by a VVB before any Carbon Credits may be issued.

፬/ የሀሳብ አመንጪው፡-

4/ The Proponent shall:

ሀ) ገምጋሚና አረጋጋጩ አካል ያለ ምንም ገደብ የቅነሳ ተግባሩንና የትግበራ ቦታውን እንዲጎበኝና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች፣ የክትትል መመዝገቢያዎችና አግባብነት ያላቸውን የሒሳብ መዛግብት ያለምንም ገደብ እንዲያገኝ መፍቀድ፤

a) provide the VVB with unrestricted access to the Mitigation Activity, the site and all relevant data, monitoring logs, and relevant financial records;

ለ) የክትትል ሪፖርቱ በቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድና ተፈጻሚነት ባለው የካርበን ስታንዳርድ ውስጥ ለተቀመጡ ስታንዳርዶችና አሠራሮች በጥብቅ ተገዢ መሆኑን ማረጋገጥ፤

b) ensure that the monitoring report aligns strictly with the standards and methods set out in the MADD and the applicable Carbon Standard;

ሐ) በተመዘገበው የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ ውስጥ ከተቀመጠው ውጪ የተፈጸሙ ተግባራትን በማረጋገጫ ሪፖርቱ ውስጥ በግልጽ ማመልከት አለበት፡፡

c) expressly set out any deviations from the registered MADD in the Verification Report.

፭/ ገምጋሚውና አረጋጋጩ አካል፡-

5/ The VVB shall:

ሀ) ማንኛውንም እና ሁሉንም ሪፖርት የተደረጉ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳንና ማስወገድን ጨምሮ ከቅነሳ ተግባሩ ጋር የሚያያዙ የቅነሳ ውጤቶችን በአሃዛዊና ጥራታዊ መለኪያዎች በገለልተኛነት መገምገም፤

a) conduct an independent assessment of the quantified and qualitative Mitigation Outcomes associated with the Mitigation Activity including any and all reported GHG emission reductions and removals;

ለ) የተቀነሱ ወይም የተወገዱ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት ትክክለኛ መጠን የሚያረጋግጥ አዎንታዊ የማረጋገጥ መግለጫ የያዘ የማረጋገጫ ሪፖርት ማውጣት፤ እና

b) issue a Verification Report with a positive Verification statement confirming the exact quantity of GHG emission reductions and removals; and

ሐ) ገምጋሚውና አረጋጋጩ አካል የማረጋገጥ ሥራውን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታወቁ ስታንዳርዶች እንዲሁም በቅነሳ ተግባሩ ላይ ተፈጻሚነት ባላቸው ደንቦችና መመዘኛዎች መሠረት ለማከናወን ብቁ መሆኑንና በሀሳብ አመንጪውና በራሱ መካከል የጥቅም ግጭት እንደሌለ ማረጋገጥ አለበት፡፡

c) expressly confirm that the VVB is qualified to do the Verification in accordance with internationally recognized standard and the applicable rules and requirements of the Mitigation Activity, and that no conflict of interest exists between the VVB and the Proponent.

፮/ ገምጋሚውና አረጋጋጩ አካል ሪፖርት የተደረጉት የቅነሳ ተግባራትና የቅነሳ ውጤቶች ለቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱና ለማንኛውም ተፈጻሚነት ላለው የካርበን ስታንዳርድ መመዘኛ ተገዢ እንዲሆኑ የሚያስችሉ አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃ ጥያቄዎችን ለሀሳብ አመንጪው ሊያቀርብለት ይችላል፡፡ ሀሳብ አመንጪው በገምጋሚና አረጋጋጩ አካል በሚቀርቡት የማስተካከያ እርምጃ ጥያቄዎች ውስጥ ተለይተው የተቀመጡ ጉደለቶችን ወይም ተደጋጋሚ ልዩነቶችን የማያርም ከሆነ የቅነሳ ውጤቶቹ ሊረጋገጡም ሆነ ከቅነሳ ውጤቶቹ ጋር የሚያያዙ የወደፊት የካርበን ክሬዲቶች ሊሰጡ አይችሉም፡፡ ተደጋጋሚና የማይስተካከሉ ጉድለቶች ወይም ከዕቅድ ውጪ የሆኑ ትግበራዎች በተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የካርበን ክሬዲት መሰጠት ዕገዳን፣ የቅነሳ ተግባር ምዝገባ መሰረዝን ወይም የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት የሚያስከትሉ ይሆናል፡፡

6/ The VVB may provide the Proponent with required corrective action requests in order to Verify that the reported Mitigation Activity and Mitigation Outcomes comply with the MADD and any applicable Carbon Standard requirements. If the Proponent fails to remedy defects or persistent deviations identified by the VVB as part of the corrective action requests, the Mitigation Outcomes cannot be Verified and further Carbon Credits associated with the Mitigation Outcomes cannot be issued. Persistent and unremedied defects or deviations may result in the DNA suspending Carbon Credit issuance, revoking the registration of the Mitigation Activity, or imposing administrative monetary penalties to be prescribed in the Directive to be issued by the DNA.

፲. የካርበን ክሬዲቶችን መፍቀድ

፩/ የሀሳብ አመንጪው፣ የሚከተሉትን የተረጋገጡ የቅነሳ ውጤቶች በሌላ አገር በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረቱ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅዶች ወይም ለሌላ ዓለም አቀፍ የቅነሳ ዓላማ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ እንዲፈቅድለት የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡-

ሀ) ቅነሳዎች፣

ለ) ማስቀረቶች፣

ሐ) ማስወገዶች፡፡

፪/ የሀሳብ አመንጪው የፈቃድ ማመልከቻውን ከገምጋሚና አረጋጋጩ አካል የማረጋገጫ ሪፖርት ጋር ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን፣ የካርበን ክሬዲቶችን ጨምሮ ብቁ ለሆኑ የቅነሳ ውጤቶች የቀረበለትን የፈቃድ ማመልከቻ እንዲሁም ከበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴው የተሰጠ ማንኛውንም ምክረ-ሀሳብ በመመርመር የፈቃድ ደብዳቤ ውሳኔውን የኮሚቴው ምክረ-ሀሳብ በደረሰው በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ከሀሳብ አመንጪው ጥያቄ ሲቀርብለት ከካርበን ክሬዲቶች ለሚመነጩና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚዛወሩ የቅነሳ ውጤቶች የፈቃድ ደብዳቤ በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ሊሰጥ ይችላል፡፡

10. Authorization of Carbon Credits

1/ The Proponent may apply to the DNA to have the following Verified Mitigation Outcomes authorized for use towards another country's NDC or for other international mitigation purposes:

a) Reductions;

b) Avoidance;

c) Removals.

2/ The Proponent shall submit its application for authorization and the VVB's Verification report to the DNA.

3/ The DNA shall consider the Proponent's application for authorization of the qualifying Mitigation Outcomes including Carbon Credits and any recommendations from the Inter-Sectoral Carbon Market Committee, and DNA shall issue its decision on the Letter of Authorization within 30 (Thirty) days from the date of receipt of the Committee's recommendation.

4/ Upon the request of the Proponent, the DNA may issue a letter of Authorization for Internationally Transferred of Mitigation Outcomes (ITMOs) resulting from the Carbon Credits within 30 (Thirty) days.

፫/ እንደ ሀሳብ አመንጪው ፍላጎት ሁሉም የቅነሳ ተግባራት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ስታንዳርዶች፣ በዓለም አቀፍ የካርበን ክሬዲት ስታንዳርዶች ወይም በካርበን ክሬዲት አሠራሮች መሠረት ፈቃድ የማግኘት ዕድል አላቸው፡፡

፬/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለ ሥልጣን ከሀሳብ አመንጪው ጥያቄ ሲቀርብለት በፈቃደኛነት ላይ በተመሠረተ የካርበን ገበያ ላይ በሚገኝ የካርበን ስታንዳርድ ለሚገዙ የቅነሳ ተግባራትና የቅነሳ ውጤቶች የፈቃድ ደብዳቤ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፲፩. <u>የካርበን ክሬዲቶች መቀልበስ</u>

፩/ በአንድ የተመዘገበ የቅነሳ ተግባር ውስጥ የተከማቸ፤ ወይም የተቀነሱ ካርበን ክሬዲቶች መቀልበስ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሀሳብ አመንጪው፡-

ሀ) ስለ ቅልበሳው ባወቀ በ፲፭ (አስራ አምስት) ቀናት ውስጥ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በጽሑፍ ማሳወቅ፤

ለ) የቅልበሳውን ምክንያትና ተጽዕኖ የደረሰባቸውን የካርበን ክሬዲቶች ወሰንና መጠን የሚገልጽ ዝርዝር የቅልበሳ ሪፖርት ማቅረብ፤ እና

ሐ) ቅልበሳው እስኪስተካከል ድረስ ተጽዕኖ ከደረሰበት የቅነሳ ተግባርና ከተያያዥ የቅነሳ ውጤቶች የሚመነጩ የካርበን ክሬዲቶችን ሽያጭ ወይም ዝውውር ማቆም አለበት፡፡

5/ All Mitigation Activities are eligible for authorization under the Ethiopian National Standards, the International Carbon Crediting Standards, or the Carbon Crediting Mechanisms at the discretion of the Proponent.

6/ Upon request by the Proponent, the DNA may issue a Letter of Authorization for a Mitigation Activity and Mitigation Outcomes governed under a Voluntary Carbon Market Carbon Standard.

11. <u>Reversal of Carbon Credits</u>

1/ Where a Reversal of sequestered or reduced Carbon Credits occurs within a registered Mitigation Activity, the Proponent shall:

a) notify the DNA in writing within 15 (Fifteen) days of becoming aware of the Reversal;

b) submit a Reversal report detailing the cause, extent, and quantity of Carbon Credits affected; and

c) cease the sale or transfer of any further Carbon Credits from the affected Mitigation Activity and related Mitigation Outcomes until the Reversal is remediated.

፪/ ቅልበሳው የተከሰተው የሀሳብ አመንጪው ሆነ ብሎ በፈጸመው ወይም መፈጸም ሲኖርበት ባልፈጸመው ድርጊት ወይም በከፍተኛ ቸልተኛነቱ ምክንያት ከሆነ የሀሳብ አመንጪው በ፩፻፹ (አንድ መቶ ሰማንያ) ቀናት ውስጥ፡-

ሀ) በራሱ ሒሳብ ውስጥ ከሚገኙ የጸኑ የካርበን ክሬዲቶች ውስጥ አቻ የሚሆነውን መጠን በማክሰም፤ ወይም

ለ) አቻ የሆነን የካርበን ክሬዲት መጠን ከካርበን መዝገብ ወይም ከሌሎች የጸደቁ መዝገቦች ገዝቶ በማክሰም የተቀለበሱትን ክሬዲቶች መተካት አለበት፡፡

፫/ የሀሳብ አመንጪው፣ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ውስጥ በሚወሰነው መሠረት ከተሰጠው የካርበን ክሬዲት ውስጥ በመቶኛ የሚቀመጥ አቻ መቶኛውን በ በአፈጻጸም ዋስትና፣ በመድን ፖሊሲ ወይም በተቀማጭ ጥሬ ገንዘብ መልክ በማግኘትና በመያዝ በንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር ለተቀመጠው የመተካት ግዴታ ተገዢ መሆን አለበት፡፡

፬/ የሀሳብ አመንጪው ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በመመሪያ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታውን መወጣት ካልቻለ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ይህን ምትክ የካርበን ክሬዲት የመግዛት ዋስትና ተፈጻሚ እንዲሆን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ If the Reversal is caused by the intentional action, inaction, or gross negligence of the Proponent, the Proponent shall, within 180 (One Hundred Eighty) days, replace the Reversed credits by:

a) retiring an equivalent quantity of valid Carbon Credits from the Proponent's own account; or

b) purchasing and retiring equivalent quantity of Carbon Credits from the Carbon Registry or other approved registries.

3/ The Proponent shall comply with the replacement obligations under Sub-Article (2) by obtaining and maintaining a financial guarantee in the form of a performance bond, insurance policy, or cash deposit, equivalent to a percentage of the value of issued Carbon Credits as determined by the directive to be promulgated by the DNA.

4/ The DNA may call upon this guarantee to purchase replacement Carbon Credits if the Proponent fails to fulfill their obligations within the timeframe specified in Sub-Article (2) or the Directive to be stipulated by the DNA;

፭/ ቅልበሳው የተከሰተው ከዐቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ምክንያት ከሆነና የታጣው የካርበን ክሬዲት የተመዘገበ ሆኖ የሀሳብ አመንጪው ሁሉንም የማሳወቂያ ግዴታዎች አክብሮ ከተገኘ የካርበን ክሬዲት ኪሳራው በዚህ አዋጅ፣ በካርበን ስታንደርዶች ወይም በካርበን ገበያ አሠራሮች መሠረት በሚቋቋመው የኢትዮጵያ መጠባበቂያ የካርበን ሒሳብ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

5/ If the Reversal is caused by a force majeure event, the loss of Carbon Credits may be covered by the Ethiopia Carbon Buffer Account established under this Proclamation, Carbon Standards, or Carbon Marketing Mechanisms where the Carbon Credit has been registered and the Proponent has complied with all notification requirements.

፮/ የሀሳብ አመንጪው ማንኛውንም የተቀለበሰ ክሬዲት ካልተካና ያቀረበው የገንዘብ ዋስትና ቅልበሳውን ለመሸፈን በቂ ሆኖ ካልተገኘ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን፡-

6/ Where the Proponent fails to replace any Reversed credits and its financial guarantee is insufficient to cover the loss, the DNA may:

ሀ) የቅነሳ ተግባሩንና የቅነሳ ውጤቶቹን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ፤

a) suspend or revoke the Mitigation Activity and the Mitigation Outcomes;

ለ) በማንኛውም ቀሪና የስጋት ቅነሳ እርምጃ ካልተወሰደበት የተቀለበሰ ክሬዲት የገበያ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮ ሊጥል፤ እና

b) impose an administrative monetary penalty equivalent to the market value of any remaining, unmitigated Reversed credits; and

ሐ) ሀሳብ አመንጪው የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰን ጊዜ በማንኛውም ሌላ የቅነሳ ተግባር ወይም የቅነሳ ውጤት ውስጥ እንዳይሳተፍ ሊከለክል ይችላል፡፡

c) prohibit the Proponent from participating in any other Mitigation Activity or Mitigation Outcome for a period to be defined by the Directive to be promulgated by the DNA.

፲፪. ተመጣጣኝ ማስተካከያዎች

፩/ የካርበን ክሬዲቶችን ጨምሮ የቅነሳ ውጤቶች በፓሪሱ ስምምነት መሠረት ለሌላ አገር በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረቱ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅዶች ወይም ለሌሎች ዓለም አቀፍ የቅነሳ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ፈቃድ ከተሰጠባቸው፣ ኢትዮጵያ እና የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በፓሪሱ ስምምነት ሪፖርት የማድረጊያ ግዴታዎች መሠረት በአስቸኳይ ለተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ የማዕቀፍ ስምምነት ጽሕፈት ቤት በማሳወቅ በፓሪስ ስምምነትና በአንቀጽ ፮ መሠረት በልቀት ሚዛኗ ላይ ተመጣጣኝ ማስተካከያ ማድረግ አለባት፡፡

፪/ ተመጣጣኝ ማስተካካዮች ሊተገበሩ የሚችሉት በኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ከልልና የጊዜ ወሰን ውስጥ ብቻ መሆን አለበት፤

፫/ ተመጣጣኝ ማስተካከዮቹ የእያንዳንዱ እና የሁሉም የግልጽነት ሪፖርቶች፣ የመነሻ ሪፖርት እና በየሁለት ዓመቱ የሚቀርበው ሪፖርት አካል መሆን አለባቸው፡፡

፬/ የተመጣጣኝ ማስተካከያ ፕሮቶኮል ተፈጻሚ የሚደረግባቸው የቅነሳ ወጤቶች የሚፈለጉት የካርበን ክሬዲቶች የተሰጡትና የተፈቀዱት ለሚከተሉት የአጠቃቀም ዓይነቶች ከሆነ ነው፡-

ሀ) ለዓለም አቀፍ አቪዬሽን የካርበን ማካካሻ እና ቅነሳ ሥርዓቱ ወይም ለሌላ በተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ለተፈቀደ ዓለም አቀፍ የቅነሳ ዓላማ ተገዢ ለመሆን፤ እና

12. Corresponding Adjustments

1/ Where Mitigation Outcomes including Carbon Credits are authorized by the DNA for use towards another country's NDC under the Paris Agreement or for other international mitigation purposes, Ethiopia and the DNA shall promptly notify the UNFCCC Secretariat in accordance with the Paris Agreement reporting requirements and apply a Corresponding Adjustment to its emissions balance in accordance with the Paris Agreement and Article 6.

2/ Corresponding Adjustments shall not be applied beyond the scope and timeframe of Ethiopia's applicable NDC cycle.

3/ The Corresponding Adjustments shall be part of each and all transparency reports the initial report, annual report and biennial transparency report.

4/ Mitigation Outcomes that are subject to Corresponding Adjustment (CA) protocol shall only be required when Carbon Credits are issued and authorized for use:

a) for compliance under CORSIA or other international mitigation purpose authorized by the DNA; and

ለ) ለሌላ ወገን በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረቱ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅዶች መሳካት ታስበው ሲሆን ነው፡፡

፭/ የተወሰኑ የካርበን ክሬዲቶች የአገር ውስጥ ብቻ በሚል ሊለዩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ክሬዲቶች በተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የማይፈቀዱና ተመጣጣኝ ማስተካከያ የማይደረግባቸው እንዲሁም ወጪ የማይደረጉ ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ለዓለም አቀፍ የቅነሳ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ናቸው፡፡

፮/ አንድ ተመጣጣኝ ማስተካከያ ተፈጻሚ እንዲሆን ከተደረገ የካርበን መዝገቡ፣ ተመጣጣኝ ማስተካከያው በተደረገ በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ በካርበን ክሬዲቱ ላይ ተመጣጣኝ ማስተካከያ የተደረገበት የሚል ምልክትና መለያ ማድረግ አለበት፡፡

፲፫. ገበያ-ነክ ያልሆነ አሠራር

፩/ በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮.፰ ሥር የተቀመጡት ገበያ-ነክ ያልሆኑ የትብብር አሠራሮች በዚህ አዋጅ ዕውቅና የተሰጣቸውን የገበያ አሠራሮች በሚደግፍ መንገድ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፪/ ገበያ-ነክ ያልሆኑ አሠራሮች የሚከተሉትንና ሌሎች ከዚህ በታች ያልተዘረዘሩ አሠራሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

ሀ) ታዳሽ ኃይል፣ የኃይል ቀልጣፋነትና ዘላቂ የመሬት አጠቃቀም፤

ለ) የቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር፤

ሐ) ዐቅም ግንባታ፣ ትብብራዊ የምርምር ፕሮጀክቶች፣ የዕውቀትና ክሂሎቶችን መጋራት፤

b) toward the achievement of another Party's NDCs.

5/ Certain Carbon Credits may be designated as domestic-only, and shall not be authorized by the DNA, in which case no Corresponding Adjustments shall apply and such Carbon Credits shall not be exported or otherwise used for international mitigation purposes.

6/ In the event that a Corresponding Adjustment is applied, the Carbon Registry shall label and tag the Carbon Credit status as Correspondingly Adjusted within 30 (Thirty) days from the date of Corresponding Adjustment.

13. Non-Market Approach

1/ The cooperative approaches under Article 6.8 of the Paris Agreement through non-market mechanisms shall apply in a manner that complements the market mechanisms recognized in this Proclamation.

2/ The non-market mechanisms may include, but not restricted to:

a) renewable energy, energy efficiency, and sustainable land use;

b) technology development and transfer;

c) capacity building, cooperative research projects, knowledge and skill sharing;

መ) የአየር ንብረት ፋይናንስ እና ውጤትን መሠረት ያደረጉ ክፍያዎች፤

ሠ) የዘርፍ የቅነሳ ፕሮግራሞችና የፖሊሲ ትብብር፡፡

፫/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በፓሪስ ስምምነት አንቀጽ ፮.፰ መሠረት መደበኛ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት የማዕቀፍ ስምምነት ጽህፈት ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

d) climate finance and results based payments;

e) sectoral mitigation programs and policy cooperation.

3/ The DNA shall prepare periodic reports and submit to the UNFCCC in consistence with Article 6.8 of the Paris Agreement.

ክፍል ሦስት

የካርበን ክሬዲት ግብይት

PART THREE

CARBON CREDIT TRADING

፲፬. የቅነሳ ውጤቶችን የሚያስገኝ የቅነሳ ተግባር ባለቤትነት

፩/ የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ለሚመነጩ የካርበን ክሬዲቶች የበላይ ባለቤት ነው፡፡

፪/ አንድ የመሬት ባለ ይዞታ የቅነሳ ተግባር ወይም የቅነሳ ውጤት የባለቤትነት መብቱን ለአንድ ሀሳብ አመንጪ ካስተላለፈ በሁለቱ ወገኖች መካከል የተፈጸመና የካርበን ክሬዲቶቹ ትክክለኛ ባለቤት ማንነትን በግልጽ የሚያሳይ የውል ስምምነት የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱ አካል ሆኖ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡

14. Ownership of Mitigation Activity resulting Mitigation Outcomes

1/ The Government of Ethiopia shall be the supreme owner of carbon credits generated within the territory of Ethiopia.

2/ If a landholder transfers his ownership rights for a Mitigation Activity or Mitigation Outcome to a Proponent, the contractual agreement between the parties that clearly shows who owns the Carbon Credits shall be submitted to the DNA as part of the MADD.

፲፭. የካርበን መብቶች ባለቤትነት

፩/ የካርበን መብቶች ከቅነሳ ተግባሮች የሚመነጩና ልዩትነት ያላቸው መብቶች ስለመሆናቸው ዕውቅና ይሰጣቸዋል፡፡

15. Ownership of Carbon Rights

1/ Carbon Rights shall be recognized as distinct rights arising from Mitigation Activities.

፪/ በውል ላይ ከዚህ በተለየ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር የካርበን ክሬዲቶች የመጀመሪያ ባለቤትነት መብት የሚኖረው የሀሳብ አመንጪው ሲሆን ይህም በሥራ ላይ ባሉ የመሬትና የንብረት መብቶች የሚገዛ ይሆናል፡፡

፫/ በማኅበረሰብ ከሚተዳደሩ ሃብቶች ጋር የሚያያዙ የካርበን መብቶች ባለቤት የሚመለከታቸው ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ማህበራት ይሆናሉ፡፡

፬/ የካርበን መብቶች ምዝገባ በመሬት ላይ ወይም በበታችኛው የአፈር ንጣፍ ሀብቶች ላይ የባለቤትነትን ወይም የመጠቀም መብትን አያጎናጽፍም፡፡

፲፮. <u>የቅነሳ ተግባር የቆይታ ዘመን</u>

፩/ የአንድ የቅነሳ ተግባር የካርበን ክሬዲት የቆይታ ጊዜ የአንድ የቅነሳ ተግባር መጽደቅ በቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱና ተፈጻሚነት ባለው የካርበን ስታንዳርድ መሠረት የሚቀመው የጊዜ ገደብ ሲሆን ይህ የጊዜ ገደብ ለዚህ አዋጅ፣ ለጸደቀው የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድና በዚሁ ሰነድ ውስጥ ለሚካተተው የክትትል ዕቅድ በቀጣይነት ተገዢ በመሆን ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

፪/ የሀሳብ አመንጪው የቅነሳ ተግባር የክሬዲት ማድረጊያ ጊዜን ለማደስ የመጀመሪያው ክሬዲት የማድረጊያ ጊዜ ከማብቃቱ ከ፲፪ (አስራ ሁለት) ወራት አስቀድሞ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የጽሑፍ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡ ዕድሳቱ የሚፈቀደው፡-

2/ Unless otherwise agreed by a contract, the initial ownership of Carbon Credits shall vest in the Proponent, subject to the protection of existing land and property rights.

3/ Carbon Rights associated with community-managed resources shall be vested in the respective associations having legal personality.

4/ The registration of Carbon Rights does not confer ownership or use rights over land or subsoil resources.

16. <u>Duration of Mitigation Activity</u>

1/ The Carbon Crediting period of a Mitigation Activity is the defined timeframe during which an approval of Mitigation Activity is eligible to generate Carbon Credits in accordance with the MADD, the applicable Carbon Standard and contingent upon continued compliance with this Proclamation, the approved MADD, the monitoring plan included in the MADD.

2/ To renew a Mitigation Activity crediting period, the Proponent shall submit a formal request to the DNA at least 12 (Twelve) months prior to the expiry of the first crediting period. Renewal is subject to a satisfactory demonstration to the DNA and Inter-Sectoral Carbon Market Committee that:

ሀ) የቅነሳ ተግባሩ የተጨማሪነት መመዘኛዎችን እያሟላ መቀጠል መቻሉን፤

a) the Mitigation Activity continues to meet the Additionality requirements;

ለ) የቅነሳ ተግባሩ የኦፕሬሽን ስትራቴጂና ዓላማዎች ከመጨረሻው የጸደቀ የኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረቱ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድና አግባብነት ካላቸው የዘርፍ ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን፤

b) the Mitigation Activity's operational strategy and objectives remain aligned with the latest approved Ethiopia NDC and relevant sectoral policies;

ሐ) የቅነሳ ተግባሩ የመነሻ ቢሆናዊ ሁኔታ እና የክትትል ዕቅድ በካርበን ስታንዳርዶች ውስጥ የሚገኙትን ተፈጻሚነት ያሏቸውን የመጨረሻዎቹን ሥነ-ዘዴዎችና ደንቦች መሠረት በማድረግ እንዲዘምኑ የተደረጉና የተረጋገጡ መሆኑን እንዲሁም፤

c) the Mitigation Activity's Baseline scenario and monitoring plan have been updated and validated against the most current applicable methodologies and Regulations set out in Carbon Standards; and

መ) የቅነሳ ተግባሩ ባለፈው ጊዜ ሲተገበርና ክትትል ሲደረግበት የቆየው በቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱ ውስጥ በተቀመጡትና በጸደቁት ዕቅዶች መሠረት መሆኑን ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣንና ለበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴው ማሳየት ሲቻል ብቻ ነው።

d) the Mitigation Activity has been implemented and monitored in accordance with its approved plans set out in the MADD throughout the preceding period.

፫/ የአንድ የቅነሳ ተግባር የተመረጠና የመጨረሻ ክሬዲት ማድረጊያ ወቅት (የተቆረጠ ወይም የታደሰ) ማብቂያ በኋላ የቅነሳ ተግባሩ በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ የካርበን ክሬዲቶችን ለማመንጨት ብቁ መሆኑ ያከትማል።

3/ Upon the final expiry of the chosen maximum Mitigation Activity crediting period, fixed or renewed, the Mitigation Activity shall cease to be eligible to generate new Carbon Credits under this Proclamation.

፬/ የቅነሳ ተግባሩ በተጨባጭ እንቅስቃሴ ማድረግ ሊቀጥል የሚችል ቢሆንም በጸደቀው የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ እንዲሁም ተፈጻሚነት ባላቸው ደንቦችና መመዘኛዎች እንዲሁም የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በቀጣይነት በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ከተሳኩ ማስወገዶች ቋሚነት ወይም ከተሳኩ ቅነሳዎች ዘላቂነት ጋር የሚያያዙ የክትትል፣ ሪፖርት የማድረግና የማረጋገጥ ግዴታዎቹ ቀጣይነት ይኖራቸዋል።

4/ The Mitigation Activity may continue its physical operations, but shall maintain its obligations for Monitoring, Reporting, and Verification related to the Permanence of achieved removals or the sustainability of achieved reductions, as specified in its approved MADD and applicable rules and requirements and subsequent DNA Directives and Guidelines.

፲፯. <u>የካርበን ክሬዲቶችን መመዝገብና መስጠት</u>

17. <u>Registration and Issuance of Carbon Credits</u>

፩/ መዝጋቢው የማረጋገጫ ሪፖርቱን ካጸደቀ በኋላ፦

1/ Upon approval of the Verification report, the Registrar shall:

ሀ) በማረጋገጫ ወቅቱ ውስጥ መቀነስ፣ ማስቀረት ወይም ማስወገድ የሆኑና ከቅነሳ ተግባር የተገኙ የቅነሳ ውጤቶችን ትክክለኛ የቶን መጠን ያረጋግጣል፤

a) certify the exact quantity of tonnes of Mitigation Outcomes that are Reductions, Avoidance or Removals achieved from the Mitigation Activity during the Verification period;

ለ) ዳግሞ ቆጠራን ለመከላከል ለእያንዳንዱ የካርበን ክሬዲት ልዩ ተከታታይ ቁጥር ይሰጣል፤

b) assign a unique serial number to each Carbon Credit to prevent double counting;

ሐ) በካርበን መዝገቡ ውስጥ በሚገኘው የሀሳብ አመንጪው ሒሳብ ውስጥ የካርበን ክሬዲቶቹን ገቢ ያደርጋል።

c) deposit the Carbon Credits into the Proponent's account within the Carbon Registry;

፪/ አንድ የቅነሳ ተግባር በተሳካ ሁኔታ በአንድ ገምጋሚና አረጋጭ አካል ከተረጋገጠ መዝጋቢው የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

2/ Upon successful validation of a Mitigation Activity by a VVB, the Registrar shall issue a Registration Certificate.

፫/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን፡-

ሀ) የማረጋገጫው ሪፖርት ያልተሟላ፣ ወጥነት የጎደለው ወይም ስህተቶች ያሉበት ከሆነ፤

ለ) የሀሳብ አመንጪው ማንኛውንም የአካባቢያዊና ማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓቶችን ከጣሰ፣ ወይም

ሐ) የቅነሳ ተግባሩ ሊቃና የማይችል ቅልበሳ ካጋጠመው ለካርበን ክሬዲቶችን ላይፈቅድ ይችላል፡፡

፬/ አንድ ፕሮጀክት የተመዘገበው የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ባጸደቀውና ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና ባለው የካርበን ስታንዳርድ ሥር ከሆነ፡-

ሀ) የሀሳብ አመንጪው ዓለም አቀፍ ምዝገባ በተሰጠው በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ የማረጋገጫ ሪፖርቱን፣ የዓለም አቀፍ ምዝገባ ማረጋገጫ ሰነዱንና ያገኛቸውን የካርበን ክሬዲቶችን ከሚያሳይ መግለጫ ጋር በማድረግ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ማሳወቅ አለበት፡፡

ለ) የተሰየመው ባለሥልጣን ማሳወቂያው ሲደርሰው የዓለም አቀፍ ክሬዲቱን መሰጠት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በመመርመር የሚያስከለክል ምክንያት ከሌለ የተሰጡትን ክሬዲቶች የዓለም አቀፍ ምዝገባው ትይዩ ምዝገባ እንዲሆን አድርጎ በብሔራዊ የካርበን መዝገቡ ውስጥ አግባብነት ካለው የዓለም አቀፍ የምዝገባ ሒሳብና ተከታታይ ቁጥሮች ጋር በማመሳከር ይመዘግባል፡፡

3/ The DNA may refuse to authorize Carbon Credits if:

a) the Verification Report is incomplete, inconsistent, or contains errors;

b) the Proponent is in breach of any environmental or social safeguard requirements; or

c) the Mitigation Activity has experienced an irremediable reversal.

4/ Where a project is registered under an internationally recognized carbon standard approved by the DNA:

a) the project proponent shall notify the DNA in writing within 30 (Thirty) calendar days of issuance by the international registry, providing the verification report, the international registry issuance confirmation, and a statement of the quantity of credits issued;

b) upon receipt of such notification, the DNA shall review the issuance against the grounds set out in Sub-Article (2) of this Article and, if no grounds for refusal exist, shall record the credits as a mirror entry in the National Carbon Registry, cross-referenced to the relevant international registry account and serial numbers.

፲፰. የካርበን ክሬዲቶች መክሰም

፩/ አንድ የካርበን ክሬዲት ሲከስም፦

ሀ) የተገዥነት ወይም የመዋጮ የመብት ጥያቄን ለማንሳት በፈቃደኛነት ላይ ተመሥርቶ መጠቀምን ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ የአንድን አካልን ልዩ የካርበን አሻራ ማካካሻ ጨምሮ ከካርበን ክሬዲት አጠቃቀም ጋር የሚገናኝ ማንኛውንም ነጠላ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የመብት ጥያቄ ወይም የተገዥነት አጠቃቀም ለመደገፍ፤ ወይም

ለ) አንድን መቀልበስ ተከትሎ የሚመጣ የመተካት ግዴታን ለማሟላት እንዲከስም መደረግ አለበት፡፡

፪/ አንድ የካርበን ክሬዲት በመዝገቡ ውስጥ የከሰመ የሚል ምልክት ከተደረገበት በኋላ አገልግሎት መስጠት እንዳቆመ የሚቆጠር ሲሆን በድጋሚ እንዲንሠራራ ሊደረግ ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ዲጂታል ሀብት ለመፍጠር ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡

፫/ የካርበን ክሬዲቶች ለመክሰም ብቁ የሚሆኑት ከተረጋገጡና በይፋዊ መንገድ በካርበን መዝገቡ ውስጥ እንዲገቡ ከተደረጉ በኋላ ብቻ ነው፡፡

፬/ የካርበን ክሬዲቶች ንክሰም በቅነሳ ተግባሩ ውስን የክሬዲት ማድረጊያ ወቅት ውስጥ የተገደበ ነው፡፡

፭/ ሁሉም የባለፈው ዓመት የማረጋገጫ መመዘኛዎች እስከተሟሉ ድረስ አንድ የሀሳብ አመንጪ የቅነሳ ተግባሩ የክሬዲት ማድረጊያ ወቅት ከመጠናቀቁ በፊት የካርበን ክሬዲቶቹን ቀድሞ የማክሰም መብት አለው፡፡

18. Retirement of Carbon Credits

1/ A Carbon Credit shall be Retired to:

a) Support any singular voluntary claim or compliance use associated with the use of the Carbon Credit including the voluntary use to make a compliance or contribution claim or otherwise offset an entity's specific carbon footprint; or

b) fulfill a replacement obligation following a Reversal.

2/ Once a Carbon Credit is marked as Retired in the Registry, it is considered consumed and cannot be re-activated or otherwise used to create a digital asset.

3/ Carbon Credits are eligible for Retirement only after they have been Verified and officially issued into the Carbon Registry.

4/ The Retirement of Carbon Credits is limited to the specific crediting period of the Mitigation Activity.

5/ A Proponent may choose the early Retirement of Carbon Credits prior to the end of the crediting period of the Mitigation Activity, provided that all Verification requirements for the vintage year have been met;

፮/ የካርበን ክሬዲቶችን ለማክሰም ሀሳብ አመንጪው የሚከስሙትን ክሬዲቶች መጠን፣ ተከታታይ ቁጥር እና፣ እንደ አግባብነቱ ደግሞ የሚሰየመውን ተጠቃሚ የሚጠቅስ የጽሑፍ ማመልከቻ ለመዝጋቢው ማቅረብ አለበት፡፡

6/ To Retire Carbon Credits, the Proponent shall submit to the Registry a formal request specifying the quantity, serial numbers, and, if applicable, the designated beneficiary;

፯/ የማክሰም ሒደቱ የሚጠናቀቀው መዝጋቢው አካል የመክሰም የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ሲሆን ይህም ከካርበን ክሬዲቱ ጋር ለሚያያዝ ጥያቄ ብቸኛው ሕጋዊ ማረጋገጫ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡

7/ Retirement is finalized upon the Registry's issuance of a Retirement Certificate, which shall serve as the sole legal proof of the claim associated with the Carbon Credit.

፰/ ክሬዲቶቹ የተሰጡትና በይዞተታ ሥር የሆኑት የተሰየመው ባለሥልጣን ባጸደቀውና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ባለው መዝገብ ውስጥ ከሆነ፦

8/ Where credits have been issued and are held on an internationally recognized registry approved by the DNA:

ሀ) ማክሰሙ በመዝገቡ ደንቦች መሠረት ሊከናወን የሚችል ሲሆን ይህም ለዚህ አዋጅ ዓላማዎች ትክክለኛ ማክሰም እንደሆነ ይቆጠራል፤

a) retirement may be effected on the international registry in accordance with that registry's rules, and such retirement shall be recognized as valid retirement for the purposes of this Proclamation;

ለ) የፕሮጀክት ሀሳብ አመንጪው ክሬዲቶቹ በከሰሙ በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ከዓለም አቀፍ መዝገቡ የተሰጠውን የመክሰም ማረጋገጫ፣ የከሰሙትን ተከታታይ ቁጥሮች፣ ብዛት፣ የቅነሳውን ተግባር ወይም ውጤት ዓመትና የተሰየመውን ተጠቃሚ በማካተት ለተሰየመው ባለሥልጣን ማሳወቅ አለበት፤

b) the project proponent shall notify the DNA within 30 (Thirty) calendar days of retirement, providing the international registry's retirement confirmation, the retired serial numbers, quantity, vintage year, and designated beneficiary;

ሐ) የተሰየመው ባለሥልጣን የክሬዲቶቹን መክሰም በብሔራዊ የካርበን መዝገብ ውስጥ እንደተመጣጣኝ ምዝገባ አድርጎ ያሰፍረዋል፤ ጥያቄ ሲቀርብለትም ለተጠቃሚው ብሔራዊ የማክሰም ማረጋገጫ ይሰጣል፤

c) the DNA shall record the retirement as a corresponding entry in the National Carbon Registry and, upon request, issue a National Retirement Acknowledgement to the beneficiary;

መ) የአንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ(፯) ድንጋጌ ቢኖርም የዓለም አቀፍ መዝገቡ የመክሰም ማረጋገጫ በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ለሚከስሙ ክሬዲቶች የጸና ሕጋዊ ማረጋገጫ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ብሔራዊ የመክሰም ማረጋገጫው እንደ ደጋፊ ሰነድ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል።

d) notwithstanding Article 17 (7), the international registry's retirement confirmation shall constitute valid legal proof of retirement for credits retired under this sub-article, and the National Retirement Acknowledgement shall serve as supplementary documentation only.

ክፍል አራት
የካርበን ምዝገባ

PART FOUR
CARBON REGISTRY

፲፱. የካርበን ምዝገባ

፩/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የካርበን መዝገብ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ የተሰየመው ባለሥልጣን የብሔራዊ ካርበን መዝገቡ መዝጋቢ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን የመዝገቡን አስተዳደር፣ ደኅንነትና ተአማኒነት በሚመለከት ኀላፊ ይሆናል።

፫/ በተሰየመው ባለሥልጣን የሚተዳደረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የካርበን መዝገብ የሁሉም የካርበን ክሬዲቶች ባለቤትነትን፣ መሰጠትን፣ መከታተያን፣ ማስተላለፍንና መክሰምን ጨምሮ የቅነሳ ተግባራትን፣ የቅነሳ ውጤቶችንና የካርበን ግብይቶችን በሚመለከት የተማከለ የኤሌክትሮኒክ የመረጃ ቋት ሆኖ የሚያገለግል ነው።

፬/ ሁሉም የቅነሳ ተግባራት የሀሳብ አመንጪዎች በቅድሚያ የተሰየመውን ባለሥልጣን የቅነሳ ተግባር የማጽደቅ ደብዳቤ ካገኙ በኋላ የኢትዮጵየ ብሔራዊ የካርበን መዝገብን ወይም የፓሪስ ስምምነት ዓለም አቀፍ መዝገብን (ከሁለቱ አንደኛውን ብቻ) መጠቀም ይችላሉ።

19. Carbon Registry

1/ The Ethiopia National Carbon Registry is hereby established by this Proclamation.

2/ The DNA shall serve as the Registrar of the National Carbon Registry and shall be responsible for its administration, security, and integrity.

3/ The DNA shall maintain the Ethiopia National Carbon Registry to function as the centralized electronic database that records all information on Mitigation Activities, Mitigation Outcomes and trading of Carbon Credits including but not limited to ownership, issuance, tracking, transfer and retirement of all Carbon Credits.

4/ All Proponents of Mitigation Activities can use the Ethiopia National Carbon Registry or Paris Agreement International Registry (but never both) provided that they first must obtain a formal Letter of Approval for the Mitigation Activity from the DNA.

፭/ መዝጋቢው፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የካርበን መዝገቡ ሙሉ ለሙሉ እስኪቀናጅና ሥራ እስኪጀምር ድረስ ጊዜያዊ፣ በአብዛኛውን ጊዜ አፍላይን የሆነና የቅነሳ ተግራትንና የቅነሳ ውጤቶችን ዳታ ለመከታተልና ለማጽደቅ የሚያስችል የመረጃ ቋት ሊጠቀም ይችላል፡፡

፮/ ብሔራዊ የካርበን መዝገቡ ሥራ ከጀመረ በኋላ መዝገብ ያዡ ሥርዓቱ ዕውቅና ከተሰጣቸው ዓለም አቀፍ መዝገቦች ጋር እንደ አግባብነቱ እርስ በርስ ለመናበብና ዳታን ለማቀናጀት የሚያስችል መሆኑን እንዲሁም ከጊዜያዊው የመረጃ ቋት ወደ ብሔራዊ የካርበን መዝገብ የሚደረገውን የሁሉንም ዳታ ፍልሰት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ አለበት።

፯/ የተሰየመው ባለሥልጣን የየዘርፉን የካርበን መዝገቦች ማቋቋም የሚችል ሲሆን እነዚህም ከብሔራዊው የካርበን መዝገብ ጋር የተቀናጁና እርስ በርስ የሚናበቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

5/ The Registrar may use an interim record as a temporary, often offline, database to track Mitigation Activity and Mitigation Outcome data and authorizations before full integration and operation of the Ethiopia National Carbon Registry.

6/ Upon the operationalization of the Ethiopia National Carbon Registry, the Registrar shall take all necessary steps to ensure that the system maintains interoperability and data synchronization with recognized international Carbon Registries, as applicable and the migration of all data from the interim record to the Ethiopia National Carbon Registry.

7/ The DNA may establish sector specific Carbon Registries in an integrated and interoperable manner in order to establish the Ethiopia National Carbon Registry.

፳. <u>የኢትዮጵያ የመጠባበቂያ የካርበን ሒሳብ</u>

፩/ የተሰየመው ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ብሔራዊ የካርበን መዝገብ ውስጥ የኢትዮጵያን የመጠባበቂያ የካርበን ሒሳብ ያቋቁማል፡፡

፪/ የመጠባበቂያ ሒሳቡ ቀዳሚ ዓላማ ከዐቅም በላይ በሆኑ ሁኔታዎች ምክንያት በሚከሰቱ ቅልበሳዎች የሚፈጠሩ ስጋቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል የመድን አሠራር ሆኖ ማገልገል ነው፡፡

20. <u>Ethiopia Carbon Buffer Account</u>

1/ The DNA shall establish the Ethiopia Carbon Buffer Account within the Ethiopia National Carbon Registry.

2/ The primary purpose of the Ethiopia Carbon Buffer Account is to act as an insurance mechanism to manage the risk of force majeure reversals.

፫/ የቅነሳ ተግባሮችን የፋይናንስ አዋጪነት ለማመቻቸትና ድርብ የመድን ሽፋንን ለማስቀረት ወደ ኢትዮጵያ መጠባበቂያ የካርበን ሒሳብ የሚደረጉ አስገዳጅ ብሔራዊ መዋጮዎች ምጣኔ እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡-

ሀ) ዓለም አቀፍ ዕውቅና ላለው የመጠባበቂያ ክምችት በወቅቱ መዋጮ እያደረጉ ላሉ የቅነሳ ተግባራት የካርበን ክሬዲቱን ፪ በመቶ፤

ለ) ለዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ክምችት መዋጮ ለማያደርጉ የቅነሳ ተግባራት የተሰየመው ባለሥልጣን በሚያወጣው የአሠራር መመሪያ መሠረት ለእያንዳንዱ የቅነሳ ተግባር የተቀመጠውን የስጋት ገጽታ መሠረት በማድረግ ከ ፭ እስከ ፲ በመቶ ይሆናል፡፡

3/ To facilitate the financial viability of Mitigation Activities and avoid double-insurance, the mandatory national contribution to the Ethiopia Carbon Buffer shall be set at:

a) 2% of the Carbon Credit for Mitigation Activities that already contribute to an internationally recognized buffer pool;

b) 5 to 10% for Mitigation Activities that do not contribute to an international buffer pool, based on the specific risk profile of the Mitigation Activity to be prescribed in a guideline issued by the DNA.

፬/ በኢትዮጵያ መጠባበቂያ የካርበን ሒሳብ ውስጥ የሚያዙ የካርበን ክሬዲቶች፡-

ሀ) ለግብይት የማይውሉና በስጋት ምዘናው የቆይታ ጊዜ ያለ ተከታታይ ቁጥር የሚያዙ፤

ለ) በተረጋገጡ ከዐቅም በላይ በሆነ ሁኔታዎች ምክንያት በአገር ውስጥ የተከሰቱ ቅልበሳዎችን ለማካካስ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ፤ እና

ሐ) ለግብይት ከሚውሉት የሀሳብ አመንጪው የቅርብ ሀብቶች በሕግ የተከለሉ ይሆናሉ፡፡

4/ Carbon Credits held in the Ethiopia Carbon Buffer Account shall be:

a) held as non-tradable and without a serial number for the duration of the risk-assessment period;

b) used solely to compensate for verified force majeure Reversals within the national territory; and

c) legally ring-fenced from the Proponent's immediate tradable assets;

፭/ የሀሳብ አመንጪው በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ በብሔራዊ መጠባበቂያ የካርበን ሒሳቡ ውስጥ የሚገኙ የካርበን ክሬዲቶች ወደ ግብይት ሒሳባቸው እንዲለቀቁለት ሊጠይቅ ይችላሉ፡-

5/ The Proponent may request the release of Carbon Credits from the Ethiopia Carbon Buffer Account back into their tradable account under the following conditions:

ሀ) የቅነሳ ተግባሩ ቢያንስ ሁለት ተከታታይ የማረጋገጫ ዑደቶችን ያለ ቅልበሳ ክስተት በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቀ፤

ለ) ሀሳብ አመንጪው የቅነሳ ተግባሩን የስጋት ምጣኔ የሚቀንሱ እርምጃዎችን መውሰዱን ካሳየ፤

ሐ) የካርበን ክሬዲቶች የሚለቀቁት በሒደትና እያንዳንዱን ጉዳይ በተናጠል በማመዛዘን ሲሆን የመጠባበቂያ የካርበን ክሬዲቶቹ የመጨረሻ ክፍል የሚለቀቀው የአንድ የቅነሳ ተግባር የክሬዲት ወቅትና የመጨረሻ ማረጋገጫ በተሳካ ሁኔታ ከተጠናቀቁ ብቻ ነው፡፡

፮/ የተሰየመው ባለሥልጣን የኢትዮጵያ መጠባበቂያ የካርበን ሒሳብ በቂ መሆኑን በየሁለት ዓመቱ ይገመግማል፤

፯/ አጠቃላይ ብሔራዊ ክምችቱ ከመላው የአገሪቱ የተሰላ ስጋት ከበለጠ የተሰየመው ባለሥልጣን ቀጣይ ኢንቬስትመንትን ለማበረታታት ሲል ከፍተኛ አፈጻጸም ላላቸው የሀሳብ አመንጪዎች የክሬዲቶች ድርሻን በምጣኔ ሊመልስ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው የአሠራር መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፰/ የኢትዮጵያ መጠባበቂያ የካርበን ሒሳብ በሀቀኝነትና በግልጽነት መርሆች ላይ በመመርኮዝ የሚተዳደር ይሆናል፡፡

a) the Mitigation Activity has successfully completed at least two consecutive Verification cycles without a Reversal event;

b) the Proponent demonstrates improved risk mitigation measures that lower the Mitigation Activity's risk rating;

c) the release of Carbon Credits shall be conducted progressively on a case-by-case basis, with the final portion of the Buffer Carbon Credits being released only upon the successful completion of the Mitigation Activity's credit period and final Verification.

6/ The DNA shall review the adequacy of the Ethiopia Carbon Buffer Account every two years;

7/ Where the total national pool exceeds the calculated risk of the entire country's portfolio, the DNA may return a pro-rata share of credits to all high-performing Proponents to encourage further investment. Details shall be determined by a Directive to be issued by the DNA;

8/ The Ethiopia Carbon Buffer Account shall be managed in accordance with integrity and transparency principles.

ክፍል አምስት

አስተዳደርና ተቋማዊ ማዕቀፍ

፳፩. የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን መቋቋም

፩/ የካርበን ገበያ ተግባራትን የሚያስተባብር፣ የሚደግፍና የሚከታተል የተሰየመ ብሔራዊ ባለሥልጣን ተቋቁሟል፡፡

፪/ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር እንደተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ሆኖ ያገለግላል፡፡

፫/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ለዓለም አቀፍ የካርበን ክሬዲት አሠራሮች፣ የካርበን ስታንዳርዶችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ባላቸው የካርበን ስታንዳርዶች የተሰጡ የገምጋሚና አረጋጋጭ አካል ዕውቅናዎች ዕውቅና ይሰጣል፡፡

፬/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የተሰጠውን ኀላፊነት በውጤታማ መንገድ መወጣት እንዲችል የካርበን ገበያ አሃዶችን ያቋቁማል፡፡

፭/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያከናውናቸው ሥራዎች ሁሉ የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እንዲሁም ገለልተኛነትንና ግልጽነትን ለማረጋገጥ ጠንካራ የውስጥ አሠራሮችን ይዘረጋል፡፡

፳፪. የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነቶች

የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

PART FIVE

GOVERNANCE AND INSTITUTIONAL FRAMEWORK

21. Establishment of the Designated National Authority (DNA)

1/ The DNA is hereby established to coordinate, support, and monitor Carbon Market activities.

2/ The Ministry of Planning and Development shall serve as the DNA.

3/ The DNA shall acknowledge and recognize international Carbon Crediting Mechanisms, Carbon Standards, and VVB accreditations issued by recognized international Carbon Standards.

4/ The DNA shall establish carbon market units to facilitate the effective implementation of the DNA's mandate.

5/ The DNA shall adopt robust internal procedures to prevent conflicts of interest, ensure impartiality, and guarantee transparency across the operations.

22. Powers and Responsibilities of the Designated National Authority

The DNA shall have the following powers and responsibilities. It shall:

፩/ በብሔራዊ የካርበን ክሬዲት ማድረጊያ አሠራሮች፣ በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮ በዓለም አቀፍ አቪዬሽን የካርበን ማካካሻ ሥርዓትና በሌሎች ዓለም አቀፍ የካርበን ገበያ ሥርዓቶች ውስጥ የሚደረጉና ከካርበን ገበያ ትብብሮች ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን በሙሉ መምራትና ማስተባበር፤

1/ Lead and coordinate all matters relating to Carbon Market cooperation under national Carbon Crediting Mechanisms, Article 6 of the Paris Agreement, CORSIA and other international Carbon Market mechanisms;

፪/ የካርበን ገበያ ተግባራት ከኢትዮጵያ የካርበን ገበያ ስትራቴጂ፣ ከዚህ አዋጅና ከአጠቃላይ ብሔራዊ የአየር ንብረት ግቦች ጋር የሚኖራቸውን ስልታዊ መጣጣም መምራትና ማስተባበር፤

2/ Lead and coordinate the strategic alignment of Carbon Market activities with the Ethiopia Carbon Market strategy, this Proclamation and broader national climate goals;

፫/ በፓሪሱ ስምምነትና በስምምነቱ አንቀጽ ፮ መሠረት የሚቀርቡ ዓለም አቀፍ ሪፖርቶችን ዝግጅትና አቅርቦት ማስተባበር፤

3/ Coordinate the preparation and submission of international reports required under the Paris Agreement, and its Article 6;

፬/ የበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴን በሰብሳቢነት መምራት፤

4/ Chair an Inter-Sectoral Carbon Market Committee;

፭/ አግባብነት ካላቸው ዘርፎች ጋር በመመካከር ለቅነሳ ተግባራት የሚሆኑ የብቁነት መስፈርቶችንና የቅነሳ ተግባራት የሚጸድቁበትንና የሚከናወኑበትን ሥነ-ሥርዓት መወሰን፤

5/ Develop in consultation with relevant sectors, an eligibility criteria for Mitigation Activities, and procedures for the approval and operation of Mitigation Activities;

፮/ ስታንዳርዶችን፣ የቅነሳ ተግባራት የብቁነት መስፈርቶችንና የቅነሳ ተግባራት የሚጸቅቁባቸውንና የሚከናወኑባቸውን አሠራሮች ማስከበር፤

6/ Enforce standards, eligibility criteria for Mitigation Activities, and procedures for the review and approval and operation of Mitigation Activities;

፯/ ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተገዢ የማይሆንን የማንኛውንም የቅነሳ ተግባር ዕውቅና ማገድ ወይም መሰረዝ፤

7/ Suspend or revoke the approval of any Mitigation Activity that fails to comply with the provisions of this Proclamation;

፲፰/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የካርበን መዝገብን ማንቀሳቀስና የክትትል፣ ሪፖርት የማድረግና የማረጋገጥ መመዘኛዎችን በበላይነት መቆጣጠር፤

፲፱/ የአገር ውስጥና ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ የካርበን ግብይቶችን በመከታተል ዳግም ቆጠራን መከላከልና የቅነሳ ውጤቶችን አከባቢያዊ ታማኝነት ማረጋገጥ፤

፳/ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች የተቀመጡ አስተዳደራዊ ክፍያዎችንና ከዚህ አዋጅ ተገዢነት ጋር የሚያያዙ አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮዎችን መሰብሰብ፤

፳፩/ ለሚከተሉት ብቸኛ ብሔራዊ ፈቃጅ አካል ሆኖ ማገልገል፡-

ሀ) ለቅነሳ ተግባር የመነሻ ሀሳብ ሰነዶች የተቃውሞ አለመኖር ደብዳቤ፤

ለ) ለቅነሳ ተግባራት የንድፍ ሰነዶች የማጽደቅና የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤ፤

ሐ) ለትብብራዊ አሠራሮችና በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮.፪ እና ፮.፬ መሠረት ለሌሎች አገራት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅዶች እንዲቆጠሩ እንዲሁም ለተፈቀዱ አካላት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚተላለፉ የቅነሳ ውጤቶች እንዲሁም በዓለም አቀፍ አቪዬሽን ወይም በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ የቅነሳ እርምጃ ወይም በሌሎች ዓለም አቀፍ የቅነሳ ተግባራት ላይ ጥቅም ላይ ለሚውሉ የካርበን ክሬዲቶች የይሁንታ ፈቃድ ደብዳቤ፡፡

8/ Operate the Ethiopia National Carbon Registry and the oversight of the Monitoring, reporting, and Verification requirements;

9/ Monitor all domestic and international Carbon Credit transactions relevant to Ethiopia in order to prevent double counting and ensure the environmental integrity of Mitigation Outcomes;

10/ Collect prescribed administrative fees, and administrative monetary penalties related to compliance with this Proclamation;

11/ Serve as the sole national authorizing body for:

a) Letters of No Objection for Mitigation Activity Idea Notes (MAIN);

b) Letters of Approval and Registration for Mitigation Activity Design Documents (MADD);

c) Letters of Authorization for cooperative approaches and Internationally Transferred Mitigation Outcomes (ITMOs) towards other countries NDCs and authorized entities under Article 6.2 and 6.4 of the Paris Agreement, and authorization of Carbon Credits for the use for other international mitigation purposes such as international aviation or voluntary mitigation action.

፲፪/ የካርበን ገበያ ተሳትፎን እና የቅነሳ ተግባራት ልማትን በሚመለከት የአገራዊ ባለ ድርሻዎችን ዐቅም ማሳደግ፤

12/ Build the capacity of national stakeholders regarding Carbon Market participation and Mitigation Activity development;

፲፫/ ሁሉንም የተመዘገቡ የቅነሳ ተግባራት በመደበኛነት በመከታተል በጸደቀው የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድና የመጀመሪያው ፈቃድ ሲሰጥ በተቀመጡት ቃሎችና ሁኔታዎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ መመዘኛዎች መሠረት መከናወናቸውን መፈተሽ፤

13/ The DNA shall conduct regular monitoring of all registered Mitigation Activities in order to audit whether they are implemented in accordance with the approved MADD, the terms and conditions of the initial approval, and the requirements of this Proclamation;

፲፬/ ጉድለቶች፣ ተገዢ አለመሆንና ከዕቅድ ውጪ የሆነ ትግበራዎች ከተገኙ፡-

14/ If defects, non-compliance, or deviations are identified:

ሀ) የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ጉድለቱን ለሀሳብ አመንጪው የሚገልጽ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

a) the DNA shall issue a written notice advising the Proponent of the defect;

ለ) የሀሳብ አመንጪው የተለዩትን ጉድለቶች የሚያስተካክልበትን ዕቅድ በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ያቀርባል እንዲሁም

b) the Proponent shall submit a plan within 30 days to correct the identified issues; and

ሐ) ባለሥልጣኑ የማስተካያ እርምጃዎቹ በተሳካ ሁኔታ መተግበራቸውን የሚያረጋግጥበትን ክትትል ያደርጋል፡፡

c) the DNA shall schedule follow-up tasks to verify that the corrective actions have been successfully implemented.

፲፭/ ከአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በመተባበር ወጥነት ያለውና የተጣጣመ ብሔራዊ የካርበን ገበያ እንዲኖር ማስቻል፤

15/ Cooperate with domestic and international regulatory bodies to facilitate a cohesive and aligned national Carbon Market;

፲፯/ ባለሥልጣኑ አግባብነት ካላቸው ዘርፎችና ተቋማት ጋር በመመካከር የካርበን ፕሮጀክት ዓይነቶችን የተፈቀዱ፣ በፈቃድ ሒደት ላይ ያሉ እና የማይፈቀዱ በሚል በአሠራር መመሪያ አማካኝነት ለይቶ ማስቀመጥ፤

፲፯/ የብቁነት መመዘኛዎች የቅነሳ ውጤቶች እንዲውሉ የታሰቡበትን ጥቅም መሠረት በማድረግ በልዩነት ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ፤

፲፰/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፰) ሥር የተዘረዘሩት የብቁነት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

16/ The DNA in consultation with relevant sectors and institutions shall set eligibility criteria for and maintain specific lists of carbon project types categorizing as white list, red list and grey list by a Guideline;

17/ Eligibility criteria may be applied differentially depending on the intended use of Mitigation Outcomes;

18/ The DNA shall ensure the fulfillment of an eligibility criteria stipulated under sub-Article (18) of this Article.

፳፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነቶች</u>

23. <u>Roles and Responsibilities of the Ministry of Finance</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር የካርበን ገበያ ፊስካል አስተዳደርን፣ የገቢ ክፍፍልንና የፋይናንስ ቁጥጥርን የሚመራ መንግስታዊ አካል ሲሆን፡-

The Ministry of Finance shall be the lead authority for the fiscal management, revenue distribution, and financial oversight of the Carbon Market. It shall:

፩/ ሁሉም የካርበን ክሬዲት ገቢዎች በብሔራዊ የመንግስት ፋይናንስ አያያዝ ሕጎች መሠረት መተዳደራቸውንና ሪፖርት መደረጋቸውን እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም የልማት አጀንዳዎች ለመደገፍ እንዲቻል በብሔራዊ በጀት ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ፤

1/ Ensure that all Carbon Credit revenues are managed and reported in accordance with national public financial management laws and are integrated into the national budget to support climate-resilient development priorities;

፪/ የረዥም ጊዜ ኢንቬስትመንትን ለመሳብ ለከፍተኛ የካርበን ማከማቸት ወይም ማስቀረት የቅነሳ ተግባራት የሚሆኑ ዋስትናዎችን ወይም የመድን ማዕቀፎችን ማቅረብን ጨምሮ የቅነሳ ተግባራትን የገበያ ስጋቶች የሚቀንሱ የፋይናንስ መሣሪያዎችን ማዘጋጀትና መተግበር፤

2/ Develop and implement financial instruments to mitigate market risks of Mitigation Activities, including providing guarantees or insurance frameworks for large-scale carbon sequestration or avoidance Mitigation Activities to attract long-term investment;

ሸ/ የጋራ የፋይናንስ አቅርቦት መንገዶችን፣ ድብልቅ የፋይናንስ አሠራሮችንና ውጤትን መሠረት ያደረጉ የክፍያ ሥርዓቶችን ማዋቀርን ጨምሮ ከካርበን ገበያ ተሳትፎ ጋር በተገናኘ የዓለም አቀፍ የአየር ንብረት የፋይናንስ ማሰባሰብን መምራት፤

ቀ/ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተላለፉ የቅነሳ ውጤቶችና ከሁለተኛ ደረጃ የካርበን ክሬዲት ግብይቶች ጋር የሚገናኙትን ጨምሮ ሁሉም የካርበን ክሬዲት የፋይናንስ ግብይቶች ለአገር ውስጥ የግብር ሕጎች፣ የውጭ ምንዛሬ ደንቦችና የመንግስት ፋይናንስ ስታንዳርዶች ተገዢ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

በ/ ከካርበን ጋር የሚገናኙ ፈንዶችንና የጥቅም መጋራት ክፍያዎችን የፋይናንስ ኦዲት በየወቅቱ በማከናወን ግልጽነትን ማረጋገጥና በኢትዮጵያ ወይም ከኢትዮጵያ ጋር በሚገናኝ የካርበን ገበያ ውስጥ ተገቢ ያልሆነ የፋይናንስ አስተዳደርን ወይም ሕገ-ወጥ የፋይናንስ ፍሰትን መከላከል፡፡

3/ Lead the mobilization of international climate finance linked to Carbon Market participation, including the design of co-financing structures, blended finance arrangements, and results-based payment systems;

4/ Ensure that all Carbon Credit financial transactions, including those related to Internationally Transferred Mitigation Outcomes (ITMOs) and the secondary trading of Carbon Credits, comply with national tax laws, foreign exchange regulations, and public finance standards;

5/ Conduct periodic financial audits of carbon-related funds and benefit-sharing payouts to ensure transparency and prevent financial mismanagement or illicit financial flows within the Carbon Market in and associated with Ethiopia.

፳፬. <u>የተሰየመው ባለሥልጣንና የገንዘብ ሚኒስቴር የጣምራ ተግባርና ኃላፊነቶች</u>

የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣንና የገንዘብ ሚኒስቴር በጋራ በመሆን፡-

ሀ/ የኢትዮጵያ መንግስትን በመወከል የሚፈጸሙ የልቀት ቅነሳ የግዢ ስምምነቶች ላይ ኦፊሴላዊ ተዋዋይ ወገን ሆነው ያገለግላሉ፤

24. <u>Joint Role and Responsibilities of DNA and Ministry of Finance</u>

The DNA and the Ministry of Finance shall jointly:

1/ Serve as the official contracting entity for Emission Reduction Purchase Agreements (ERPAs) entered into on behalf of the Government of Ethiopia;

፪/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው በደንብ መሰረት ደረጃውን የጠበቀ የጥቅም መጋራት ማዕቀፍ ዘርግተው ወደ ስራ እንዲገቡ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ማዕቀፍ፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስትና በክልል መንግስታት፤

ለ) በአልሚዎች እና ወይም ሀሳብ አመንጪዎች፤

ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ ተፈጻሚነት ካለው ፈቃድ በተሰጣቸው የካርበን ገበያ አሳላፊዎች እንዲሁም፤

መ) በአካባቢ ማኅበረሰቦች መካከል ከሚደረግ የካርበን ክሬዲት ግብይት የሚገኝ ትርፍ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉን ያረጋግጣል፡፡

2/ A standardized benefit-sharing framework shall be established and implemented in accordance with Regulations issued by the Council of Ministers. This framework shall ensure the equitable distribution of proceeds from Carbon Credits transacted among:

a) the Ethiopia Federal Government and Regional States;

b) developers and or Proponents;

c) licensed Carbon Market Intermediaries if applicable;

d) local communities.

፳፭. <u>የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባራት</u>

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ውስጥ ለካርበን ገበያ አከናዋኞች ፈቃድ የሚሰጥ አካል ሆኖ ተሰይሟል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

፩/ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸው ገምጋሚና አረጋጋጭ አካላት፣ የካርበን ገበያ አሳላፊዎች፣ የካርበን አሰባሳቢዎች እንዲሁም በካርበን ስታንዳርዶች፣ ዓለም አቀፍ ተቆጣጣሪ አካላትና ሌሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ባላቸው ተቋማት ከዚህ በፊት ፈቃድ የተሰጣቸው የካርበን ሀብት አስተዳዳሪዎች ፈቃዶች ትክክለኛና የጸኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲያከናውኑ ፈቃድ ይሰጣል፤

25. <u>Powers and Responsibilities of the Environmental Protection Authority (EPA)</u>

The EPA is hereby designated as the Licensing Authority for Carbon Market operators in Ethiopia. It shall:

1/ Verify the authenticity and validity of licenses of internationally accredited VVBs, Carbon Market Intermediaries, Carbon Aggregators, and carbon asset managers already licensed by Carbon Standards, international regulators, and other internationally recognized institutions, and grant a permit to operate in Ethiopia;

፪/ የአገር ውስጥ ገምጋሚና አረጋጋጭ አካላትን፣ የካርበን ገበያ አሳላፊዎችንና የካርበን አሰባሳቢዎችን የፈቃድ አሰጣጥ ይመራል፤

፫/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ፈቃድ ያላቸውን የካርበን አከናዋኞች ዐቅም የሚያሳድግና ብቁ የሚያደርግ ብሔራዊ ስትራቴጂን በመቅረጽና በመተግበር በካርበን ገበያ ውሰጥ የረዥም ጊዜ የአገር ሉዓላዊነትንና የቴክኒክ ብቃትን ያረጋግጣል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰውን ብሔራዊ ፈቃድ ያላቸው የካርበን አከናዋኞች መዝገብ አቋቁሞ የሚይዝ ሲሆን ይህም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የካርበን መዝገብ የተለየ ነው፡፡ ይህ መዝገብ አከናዋኞችን በየዘርፋቸው የሚለይና ለተሰየመው ባለሥልጣንና ለሕዝብ ክፍት ይሆናል፡፡

፭/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር የተጠቀሱትን አካላት የብቃት ማረጋገጫዎችና የሥራ ማከናወኛ ፈቃዶች ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤ ሁሉም የአገር ውስጥም ሆነ ዓለም አቀፍ አከናዋኞች በኢትዮጵያ የካርበን ገበያ ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚያስፈልጋቸው የቴክኒክ ችሎታ፣ የፋይናንስ መረጋጋትና የተግባራት የክንውን ነፃነትን ያረጋግጣል፤

፮/ ሞያዊ ታማኝነትንና የአካባቢ ደኅንነትን ለማረጋገጥ ሲባል የአከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፦

2/ Manage the full licensing of domestic VVBs, Carbon Market Intermediaries, and Carbon Aggregators;

3/ Develop and implement a national strategy to build capacity and certify licensed carbon entities operating in Ethiopia, ensuring long-term national sovereignty and technical expertise in the Carbon Market;

4/ Establish and maintain a National Register of Licensed Carbon Operators stipulated in Sub-Article (2) of this Article, distinct from the Ethiopia National Carbon Registry. This register shall categorize operators by their sectoral scopes and shall be accessible to the DNA and the public;

5/ Issue, renew, suspend, or revoke competency licenses and operating permits of entities stipulated under Sub-Article (2) of this article and ensure that all operators domestic or international possess the required technical expertise, financial stability, and operational independence required to function in the Ethiopian Carbon Market;

6/ For the purpose of maintaining professional and environmental integrity, the EPA shall:

ሀ) አግባብነት ባላቸው የዓለም አቀፍ የስታንዳርዶች ድርጅት ስታንዳርዶች ወይም የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት አስገዳጅ የሆኑትን ዕውቅናዎች ጨምሮ መነሻ የብቁነት መስፈርቶችን ያስቀምጣል፤

a) set minimum eligibility criteria for professional licensing, including mandatory accreditation under relevant ISO standards or UNFCCC requirements;

ለ) ፈቃድ የተሰጣቸው አከናዋኞች ዓለም አቀፍ የካርበን ሒሳብ አያያዝ ሥነ-ዘዴዎችን ያከበሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በየወቅቱ የአፈጻጸም ኦዲቶችንና ድንገተኛ ፍተሻዎችን ያከናውናል፤

b) perform periodic performance audits and spot checks of licensed operators to ensure they adhere to international carbon accounting methodologies;

ሐ) አካባቢያዊ ኦዲት በማከናወን የቅነሳ ተግባራት የአካባቢውን ሥነ-ሕይወታዊ ብዝኀነት አለመጉዳታቸውን፣ የኢትዮጵያ አካባቢያዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ምዘና አዋጅን አለመጣሳቸውን ወይም ከሌሎች አገራዊ የአካባቢያዊ ጥበቃ የሕግ ማዕቀፎች የማይጋጩ መሆናቸውንና ያረጋግጣል፤ ማንኛውንም ተገዢ ያለመሆን ግኝት ለተሰየመው ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል፤

c) undergo environmental audit for the Mitigation Activities specifically to ensure they do not harm local biodiversity, violate Environmental and Social Impact Assessment Proclamation of Ethiopia, or conflict with other national environmental legal frameworks, reporting any findings of non-compliance to the DNA;

፯/ በአንድ ፈቃድ የተሰጠው አከናዋኝ ላይ የሚቀርቡ የሞያዊ ሥነ-ምግባር ጉድለት ቅሬታዎችን ወይም ጥርጣሬዎችን ይመረምራል፡፡ የሞያዊ ሥነ-ምግባር ጥሰት መፈጸሙ ከተረጋገጠ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፦

7/ Investigate complaints or suspected professional misconduct by any licensed operator. Where a violation is established, the EPA may:

ሀ) መቀጮዎችን ሊጥል፣ የአገር ውስጥ ፈቃዶችን ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ የማከናወን ፈቃዶችን ሊሰርዝ፤

a) impose fines, cancel domestic licenses, or revoke Ethiopian operating permits;

ለ) የካርበን አከናዋኞች በድጋሚ ፈቃድ ለማግኘት እንዳያመለክቱ ወይም በብሔራዊ የካርበን ገበያው ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በአከናዋኝነት እንዳይሳተፉ ሊከለክል ይችላል፡፡

b) prohibit entities from re-applying for licenses or participating as operators in the national Carbon Market for a determined period.

፰/ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮ እና በሌሎች ብሔራዊና ዓለም አቀፍ የካርበን ክሬዲት ማድረጊያ ሥርዓቶች መሠረት ፈቃድ የተሰጣቸው ገምጋሚና አረጋጋጭ አካላት ከአልሚዎች፣ ከገዢዎችና ከደላሎች ገለልተኛ በሆነ መንገድ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ለማረጋገጥ ጥብቅ የሆኑ የጥቅም ግጭት ደንቦችን ያስፈጽማል፤

8/ The EPA shall enforce strict conflict-of-interest rules to ensure that licensed VVBs operate independently of Developers, buyers, and brokers, in compliance with Article 6 of the Paris Agreement and other national and international Carbon Crediting Mechanisms;

፱/ የአካባቢና የማኅበራዊ ተጽዕኖ ምዘና ሪፖርቶችን ገምግሞ ያጸድቃል፤

9/ Review and approve and environmental and social impact assessment reports;

፲/ ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣኑ የሚቀርቡ ፈቃድ ማግኘት፣ የዕድሳት ወይም የማስተላለፍ ማመልከቻዎች በሚቀመጠው ቅርጽና ከተገቢው የአስተዳደራዊ ክፍያ ጋር መቅረብ አለባቸው፤

10/ Applications for the issuance, renewal, or transfer of licenses shall be submitted to EPA in the prescribed form, accompanied by the required administrative fees;

፲፩/ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ሁሉንም የፈቃድ ማመልከቻዎች የያዘና ለሕዝብ ክፍት የሆነ መዝገብ መያዝና የአንድ የፕሮጀክት መጠን ወይም ዓይነት ከፍተኛ ግልጽነት እንዲኖር የሚጠይቅ በሚሆንበት ጊዜ የሕዝብ አስተያየት የሚሰባሰብበት ጊዜ እንዲኖር ማድረግ፤

11/ EPA shall maintain a public register of all license applications and may allow a period for public comment where a project's scale or nature warrants high-level transparency;

፲፪/ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የፕሮጀክት ዳታን በሚመለከቱ ጉዳዮች ከተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በማንኛውም ባለ ፈቃድ ላይ ድንገተኛ ፍተሻዎችንና ቴክኒካዊ ኦዲቶችን በማከናወን ለዚህ አዋጅ ተገዢ የመሆንን ቀጣይነት ያረጋግጣል፤

12/ EPA, in coordination with the DNA where project data is involved, may conduct unannounced inspections and technical audits of any licensee to ensure ongoing compliance with this Proclamation;

፲፫/ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አንድ ባለፈቃድ፡-

ሀ) የሚፈለውን የቴክኒክ ወይም የፋይናንስ ስታንዳርድ ይዞ መቆየት ካልቻለ ወይም የተሳሳተ መረጃ ካቀረበ፤

ለ) የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶችን ካላስተካከለ፤

ሐ) በፋይናንስ፣ በአካባቢ ጥበቃ ወይም ተያያዥ ወንጀሎች ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፤ ወይም

መ) የካርበን ገበያውን ታማኝነት የሚያጓድል የሞያዊ ገለልተኛነት ጥሰትን ከፈጸመ አንድን ፈቃድ ውድቅ ማመልከን ውድቅ ሊያደርግ ወይም የተሰጡ ፈቃዶችን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

13/ The Authority may refuse, suspend, or revoke a license if the holder:

a) fails to maintain the required technical or financial standards or provides fraudulent information;

b) fails to rectify identified non-conformities within a timeframe specified by the Authority;

c) is convicted a financial, environmental, or related criminal offense; or

d) commits a breach of professional independence that compromises Carbon Market integrity;

፲፬/ ማንኛውም አንድን ፈቃድ የማገድ ወይም የመሰረዝ ውሳኔ ተመጣጣኝ፣ በጽሑፍ የሚገለጽና ለውሳኔ መሠረት የሆኑ ምክንያቶችን የሚያካትት መሆን አለበት፤

14/ Any decision to suspend or revoke a license shall be proportionate, issued in writing, and include the specific grounds for the decision;

፲፭/ በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን በደንብ በሚወሰን የአስተዳደራዊ ቅሬታ ማቅረቢያ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

15/ A party dissatisfied with the Authority's licensing decision may lodge an appeal through the administrative grievance procedure as established by Regulation.

፳፮. <u>የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት ተግባርና ኃላፊነቶች</u>

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት በየራሳቸው የሥልጣን ወሰን ውስጥ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩዋቸዋል፡-

26. <u>Roles and Responsibilities of Ministries and Institutions</u>

Ministries and other relevant institutions shall, within their respective mandates, have the following powers and responsibilities:

፩/ በየዘርፋቸው ውስጥ ለካርበን ገበያው የሚሆን ዕምቅ ዐቅም ያላቸውን የቅነሳ ተግባራት በመለየትና ቅድሚያ በመስጠት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የመዋጮ መጠን ከሚኖራቸው የዘርፍ አስተዋጽዖ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

1/ Identify and prioritize Mitigation Activities with Carbon Market potential within their sectors ensuring alignment with sectoral contributions to Ethiopia's NDC targets;

፪/ ለካርበን ማከማቸትና ለልቀት ቅነሳ ተግባራት የሚሆኑ የዘርፍ መሪ ሰነዶችን፣ ቴክኒካዊ ስታንዳርዶችንና ሥነ-ዘዴዎችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁ የካርበን ስታንዳርዶችና ብሔራዊ የካርበን ገበያ ሥነ-ዘዴዎችና ስታንዳርዶች ጋር በተጣጣመ መልኩ መቅረጽና መተግበር፤

2/ Develop and implement sectoral guidelines, technical standards, and methodologies for carbon sequestration and emission reduction activities in alignment with recognized international Carbon Standards and national Carbon Market methodologies and standards;

፫/ የካርበን ፕሮጀክት ምክረ-ሀሳቦች በበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴው ወይም በሌላ መንገድ አማካኝነት ከዘርፍ ማስተር ፕላኖች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የቴክኒክ ምዘናና የማጽደቅ አገልግሎት መስጠት፤

3/ Provide technical assessment and endorsement for carbon project proposals to ensure they align with sectoral master plans either through Inter-Sectoral Carbon Market Committee or other ways;

፬/ የዘርፍ የመረጃ ቋቶችን መያዝና በየራሳቸው የዘርፍ ኀላፊነት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የካርበን ገበያ ትክክለኛ የልቀት መነሻዎችንና የፕሮጀክት አፈጻጸም መረጃዎችን ማቅረብ፤

4/ Maintain sectoral databases and provide the Ethiopia National Carbon Registry with accurate data on emission Baselines and project performance within their sectoral mandate;

፭/ ተገቢ ያልሆኑ ማበረታቻዎችን ለማስቀረት የዘርፍ ማበረታቻዎችን፣ የግብር እፎይታዎችን ወይም የድጋፍ ፕሮግራሞችን ከካርበን ገበያ ግቦች ጋር ማጣጣም፤

5/ Align sectoral subsidies, tax breaks, or support programs with Carbon Market goals to avoid perverse incentives;

፮/ የአልሚዎችን ቴክኒካዊ ገለጻዎች የሚፈትሹ የዘርፍ ባለሞያዎችን በማሰማራት ለክትትልና ማረጋገጥ ሒደቱ ድጋፍ መስጠት፤

6/ Support the monitoring and Verification process by deploying sectoral experts to audit the technical claims of Developers;

፲/ በየዘርፉ የሚመጡ አዲስ የካርበን ክሬዲት ዕድሎችን ማስተዋወቅ፤

፲፩/ ከየዘርፍ ኃላፊነቶቻቸው ጋር የሚገናኙ የቅነሳ ተግባራትን መቀየስ፡፡

7/ Promote new Carbon Credit opportunities within their respective field;

8/ Develop the Mitigation Activities with respect to their sectoral mandate.

፳፯. <u>የበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴ</u>

27. <u>Inter-Sectoral Carbon Market Committee</u>

፩/ ለተሰጠመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የቅነሳ ተግባራትን የማጽደቅና የመፍቀድ ውሳኔዎች ድጋፍ የሚሰጥ የበይነ-ዘርፍ የካርበን ገበያ ኮሚቴ (ከዚህ በታች "ኮሚቴው") በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፡፡

1/ The Inter-Sectoral Carbon Market Committee, hereinafter the "Committee", is hereby established under this Proclamation as a national body to support the DNA in approval and authorization decisions regarding Mitigation Activities.

፪/ ኮሚቴው፡-

ሀ) የቅነሳ ተግባራት በዓለም አቀፍ የካርበን ገበያዎች ውስጥ እንዲሳተፉ በሚፈቅዱ ውሳኔዎች ላይ የተሰየመውን ብሔራዊ ባለሥልጣን ያማክራል፤

ለ) የትብብር አሠራሮችንና ሌሎች የካርበን ክሬዲት አደራረግ አሠራሮችን በሚመለከት ለፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮ ተገዢነት መኖሩን ያረጋግጣል፤

ሐ) ለገምጋሚና አረጋጋጭ አካላት፣ ለካርበን ገበያ አሳላፊዎች፣ ለካርበን አሰባሳቢዎችና ለካርበን ገበያ የሀብት አስተዳዳሪዎች የሚሆኑ የፈቃድ አሰጣጥ ስታንዳርዶችን በምክረ-ሀሳብነት ያቀርባል፤ የዋጋ ትመና መንገዶችን፣ የጥቅም መጋራት አሠራሮችን ወይም ለተጋላጭ ማኅበረሰቦች የሚደረግ ከለላን በሚመለከት ምክር ይሰጣል፤

2/ The Committee shall:

a) advise the DNA on whether Mitigation Activities should be approved for participation in international Carbon Markets;

b) ensure compliance with Article 6 of the Paris Agreement regarding cooperative approaches and other Carbon Crediting Mechanisms;

c) recommend licensing standards for VVBs, Carbon Market Intermediaries, Carbon Aggregators, and carbon market asset managers; advise on pricing mechanisms, Benefit Sharing Arrangements, and safeguards for vulnerable communities;

መ) ለተሰየመው ባለሥልጣን የሚቀርቡ የቅነሳ ተግባር ምክረ-ሀሳቦችን ይመዝናል፤

ሠ) የቅነሳ ተግባር የመነሻ ሀሳብና የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ ከኢትዮጵያ የካርበን ገበያ ስትራቴጂ፣ በፈቃደኛነት ላይ ከተመሠረቱ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅዶች እንዲሁም ከሌሎች ብሔራዊ የአየር ንብረት ፖሊሲዎችና ከፓሪሱ ስምምነት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ረ) ቴክኒካዊ ትክክለኛነትን፣ አካባቢያዊ ደኅንነትንና ማኅበራዊ የጥበቃ ሥርዓቶችን አስመልክቶ በቀረበው የቅነሳ ተግባር ላይ ምክረ-ሀሳቦችን ያቀርባል፤

ሰ) የልቀት ቅነሳ የስሌት ሥነ-ዘዴዎችን ይገመግማል እንዲሁም፤

ሸ) አንድ የሀሳብ አመንጪ በተሰየመው ባለሥልጣን እንዲደጸቅ ላቀረባቸው የቅነሳ ተግባራት ረቂቅ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

d) assess Mitigation Activity proposals submitted to the DNA;

e) verify alignment of MAINs and MADDs with Ethiopia's Carbon Market Strategy, NDC, and other national climate policies and the Paris Agreement;

f) provide recommendations on technical soundness, environmental integrity, and social safeguards of proposed Mitigation Activities;

g) review methodologies for emissions reduction calculations;

h) recommend draft decisions on Mitigation Activities submitted by a Proponent for the consideration by the DNA.

፫/ ኮሚቴው ከ፯ የማያንሱና ከየዘርፉ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚውጣጡና አግባብነት ባላቸው ሞያዎች ከፍተኛ ዕውቀትና ልምድ ያላቸውን ባለሞያዎች ያቀፈ ይሆናል፤

3/ The Committee shall be composed of not less than 7 members constituting senior experts from state and non-state institutions with knowledge and experience in their respective specializations;

፬/ የኮሚቴው ተግባራዊ አኳኋን፣ አሠራርና ቢጋር የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

4/ The functional modalities and arrangements of the Committee and its Terms of Reference shall be decided by a Directive issued by the DNA;

፭/ ኮሚቴው በየወሩ ስብሰባ ያደርጋል። ሆኖም የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊጠራ ይችላል።

5/ The Committee shall meet on a monthly basis; however extraordinary meetings can be summoned by the DNA.

፳፰. <u>የክልል መንግስታትና የከተማ መስተዳደሮች ሥልጣንና ተግባራት</u>

የክልል መንግስታትና የከተማ መስተዳድሮች ሥልጣን ባላቸው የዘርፍ ቢሮዎቻቸው አማካኝነት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

፩/ የካርበን ገበያ ተግባራትን በክልል ወይም በከተማ መስተዳድር የልማት ዕቅዶችና የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂዎች ውስጥ ማካተት፤

፪/ የክልል ደኖችን፣ የውሃ አካላትንና የጋራ መሬቶችን ጨምሮ በክልሎች ሥልጣን ሥር ያሉ ሀብቶችን የሚመለከቱ የቅነሳ ተግባራትን ልየታና ንድፍ በበላይነት መምራት፤

፫/ የመሬት አጠቃቀም መብቶችንና ዘልማዳዊ ይዞታዎችን በማረጋገጥና ማረጋገጫ በመስጠት ለካርበን ማከማቻና ለልቀት ቅነሳ ሃብቶች ባለቤትነት ሕጋዊ እርግጠኛነትን ማጎናጸፍ፤

፬/ ለአካባቢው መንግስት መዋቅሮችና ባለ ድርሻዎች የቴክኒክ ዕገዛ፣ የዐቅም ግንባታና የግንዛቤ መስጫ ፕሮግራሞችን ለማቅረብ ክልላዊ የካርበን ገበያ አሃዶችን ማቋቋምና ዐቅም መገንባት፤

፭/ ክልላዊ መረጃዎች ከካርበን መዝገቡ ጋር የተቀናጁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ዳግም ቆጠራን ለመከላከል ከተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣንና አግባብነት ካላቸው ሌሎች አካላት ጋር መተባበር፤

28. <u>Powers and Responsibilities of Regional States and City Administrations</u>

Regional States and City Administrations, through their competent sectoral bureaus, shall have the following powers and responsibilities:

1/ Mainstream Carbon Market activities into regional or city administrations development plans, and climate-resilient green economy strategies;

2/ Oversee the identification and design of Mitigation Activities involving resources under regional jurisdiction, including state forests, water bodies, and communal lands;

3/ Validate and certify land-use rights and customary holdings to provide legal certainty for the ownership of carbon sequestration and emission reduction assets;

4/ Establish and capacitate dedicated regional Carbon Market units to provide technical assistance, capacity building, and awareness programs for local government structures and stakeholders;

5/ Coordinate with the DNA and other relevant bodies to ensure regional data is synchronized with the Carbon Registry for the prevention of double-counting;

፮/ በክልላቸው ውስጥ የሚከወኑ የቅነሳ ተግባራትን ትግበራ፣ ማኅበራዊ ተጽዕኖና አካባቢያዊ ደኅንነትን መከታተል የሚያስችሉ ክልላዊ የክትትልና ሪፖርት የማድረጊያ የቁጥጥር ማዕቀፎችን መዘርጋት፤

፯/ ፍትሐዊ፣ ግልጽና ጊዜውን የጠበቀ የካርበን ክሬዲት ትርፍ ክፍፍልን ለማረጋገጥ የጥቅም መጋራት ዕቅዶችን፣ ስምምነቶችንና ማዕቀፎችን ማስከበር፤

፰/ በክልሎቻቸው ውስጥ የቅነሳ ተግባራትን መቅረጽ፤ እና

፱/ በክልሎቻቸው ወይም በከተማ መስተዳድሮቻቸው ውስጥ ውጤታማ የቅነሳ ተግባራት አፈጻጸም እንዲኖር ድጋፍ ማድረግ።

6/ Establish regional monitoring and reporting oversight frameworks to track the implementation, social impacts, and environmental integrity of Mitigation Activities operating in their jurisdiction;

7/ Enforce Benefit-Sharing Plans, Agreements and frameworks to ensure the equitable, transparent, and timely distribution of Carbon Credit proceeds;

8/ Develop Mitigation Activities within their jurisdiction; and

9/ Support the effective implementation of Mitigation Activities in their region or city administration.

፳፱. <u>የአልሚው ተግባርና ኃላፊነቶች</u>

29. <u>Roles and Responsibilities of the Developer</u>

አልሚው፦

The Developer shall:

፩/ በጸደቁ የካርበን ሒሳብ አያያዝ ሥነ-ዘዴዎች በመጠቀም የቅነሳ ተግባሩን መንደፍና መተግበር፤

1/ Design and implement the Mitigation Activity using approved carbon accounting methodologies;

፪/ ሀብት ማሰባሰብና የቅነሳ ተግባሩን የየዕለት ክንውን በበላይነት መቆጣጠር፤

2/ Mobilize resources and oversee day-to-day Mitigation Activity operations;

፫/ የቅነሳ ተግባሩን ቴክኒካዊ የክትትል ሥርዓት መዘርጋትና ማስቀጠል፤

3/ Establish and maintain the Mitigation Activity's technical monitoring system;

፬/ ሁሉም የቅነሳ ተግባራት ለብሔራዊ የአካባቢና ማኅበራዊ ሕጎችን ተገዢ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

4/ Ensure all Mitigation Activities comply with national environmental and social laws;

፭/ ለተቆጣጣሪ አካላት ለሚቀርቡ ሪፖርቶች የሚያስፈልጉ ቴክኒካዊ መረጃዎችን በሙሉ ለሀሳብ አመንጪው ማቅረብ አለበት።

5/ Provide the Proponent with all technical data required for regulatory reporting.

፴. <u>የሀሳብ አመንጪው ተግባርና ኃላፊነቶች</u>

የሀሳብ አመንጪው፡-

፩/ ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የሚቀርቡ የቁጥጥር ሰነዶችንና ሕጋዊ ሒደቶችን በሚመለከት ይፋዊ ተወካይ ሆኖ የማገልገል፤

፪/ ስጋትን፣ ኃላፊነትን እና የጥቅም መጋራትን አስመልክቶ ከባለቤቶችና ኢንቬስተሮች ጋር አስገዳጅ የሆኑ ስምምነቶችን የመፈጸም፤

፫/ በብሔራዊ የካርበን መዝገቡ ውስጥ የሚገኘውን የቅነሳ ተግባሩን ባለቤት ሒሳብ ማስተዳደር፤

፬/ ሁሉም የክትትልና ሪፖርት የማድረግ ግዴታዎች፣ የገምጋሚና አረጋጋጭ አካል መሰየምን እንዲሁም ከማኅበረሰብ ጋር የሚደረጉ ምክክሮችን ጨምሮ የማኅበራዊ ጥበቃ ከለላዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፤ እና

፭/ ለቁጥጥር ተገዢ አለመሆንና ተጨባጭ ወይም ከፍተኛ ማጭበርበሮችን በሚመለከት ዋነኛ የሕግ ኃላፊነትን የመቀበል ቀዳሚ ሕጋዊ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

30. <u>Roles and Responsibilities of the Proponent</u>

The Proponent shall bear primary legal responsibility for:

1/ Serving as the official representative for all regulatory filings and proceedings with the DNA;

2/ Executing binding agreements with owners and investors regarding risk, liability, and Benefit Sharing;

3/ Managing the Mitigation Activity Owner's account in the National Carbon Registry;

4/ Ensuring the fulfillment of all monitoring and reporting obligations, retention of the VVB, and social safeguards, including community consultations; and

5/ Accepting primary liability for regulatory non-compliance or material misrepresentations.

፴፩. <u>የካርበን ክሬዲት ሻጮችና ገዢዎች ኃላፊነቶች</u>

፩/ ሻጭና ገዢው የካርበን ክሬዲት ማስተላለፎችን ወይም ግብይቶችን አግባብነት ባለው የካርበን መዝገብ ውስጥ መመዝገብ፣ የግብይት ዋጋዎችንና መጠኖችን ለተሰየመው ባለሥልጣን የማሳወቅና ለጸረ-ሙስና እና በወንጀል የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ለሚከላከሉ ሕጎች ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡

31. <u>Responsibilities of Carbon Credit Sellers and Buyers</u>

1/ The Seller and the Buyer shall record all transfers or dealing in Carbon Credits in the relevant Carbon Registry, disclose transaction prices and volumes to the DNA, and comply with anti-bribery and anti-money laundering requirements.

፪/ ሻጭ በክሬዲቶቹ ላይ ሊሎች የመብት ጥያቄ የማያነሱበትና ሕጋዊ የሆነ ባለቤትነት ያለው መሆኑን ማረጋጥና በሕግ የተቀመጡና ከአካባቢው ማኅበረሰብ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ፌደራልና የክልል መንግስታት ጋር የሚደረጉ የጥቅም መጋራት አሠራሮችን ማሟላት አለበት፡፡

2/ The Seller shall guarantee clear legal title to credits and fulfill all mandated Benefit-Sharing Arrangements with local communities, the Ethiopia federal and regional state governments.

፫/ ገዢ ዳግመኛ ጥቅም ላይ መዋልን ለመከላከልና በፈቃድ ደብዳቤ ወይም በአገር ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ ለሚውሉ የካርበን ክሬዲቶች ጥያቄዎች ደግሞ ከተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚሰጥ ተያያዥ ፈቃድ የተደገፉ መሆናቸውንና በማንኛውም የማካካሻ ወይም የመዋጮ ጥያቄ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የካርበን ክሬዲቶች በሙሉ የከሰሙ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3/ The Buyer shall ensure that all Carbon Credits used for any compensation or contribution claim are Retired to prevent reuse and that all claims are supported by either a Letter of Authorization, or a related approval from the DNA for domestic only Carbon Credits.

፴፪. <u>የካርበን አሰባሳቢዎችና የካርበን ገበያ አሳላጮች ኃላፊነቶች</u>

የካርበን አሰባሳቢዎችና የገበያ አሳላፊዎች፡-

32. <u>Responsibilities of Carbon Aggregators and Carbon Market Intermediaries</u>

Carbon Aggregators and Market Intermediaries shall:

፩/ ለኦዲት ዓላማ ሲባል አጠቃላይ የግብይትና የቅድመ-ማጣራት ማኅደሮችን ለ፲ (አስር) ዓመታት ይዞ መቆየት፤

1/ Maintain comprehensive transaction and due diligence records for 10 (Ten) years for audit purposes;

፪/ በግብይቱ ለተሳተፉ ወገኖች በሙሉ ሁሉንም ክፍያዎች፣ ኮሚሽኖችና የገንዘብ ጥቅሞች የሚያሳይ የጽሑፍ መግለጫ መስጠት፤

2/ Provide written disclosure of all fees, commissions, and financial interests to all parties involved in the transaction;

፫/ ገበያ ከማምታታት ወይም ስለካርበን ክሬዲቶች ሁኔታ ሀሰተኛ መረጃ ከማቅረብ መቆጠብ፤

3/ Refrain from market manipulation or misrepresenting the status of Carbon Credits;

፬/ አጠራጣሪ የፋይናንስ ተግባራትን ለኢትዮጵያ ፋይናንሻል ኢንተሊጀንስ አገልግሎት መጠቆም አለባቸው፡፡

4/ Report suspicious financial activities to the Ethiopia Financial Intelligence Service.

፴፫. የገምጋሚና አረጋጋጭ አካላት ተግባርና ኃላፊነቶች

ሁሉም ገምጋሚና አረጋጋጭ አካላት፡-

፩/ ይፋዊ ዕውቅናዎችን ማስቀጠልና የኦዲት ቡድኑ አስፈላጊው ቴክኒካዊና አካባቢያዊ ብቃት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

፪/ ከምዝገባ በፊት የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱን በገለልተኝነት መርምሮ ማረጋገጥ፤

፫/ የካርበን ስታንዳርዶችን ጨምሮ የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት ቅነሳና ቅልበሳ አሃዞችንና ተገዢነትን ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎችና መመዘኛዎች መሠረት ማረጋገጥና የካርበን መዝገቡ የካርበን ክሬዲቶችን ከማውጣቱ በፊት መደበኛ የማረጋገጫ ሪፖርት መስጠት፤

፬/ ከቅነሳ ተግባሩ፣ ከማንኛውም የቅነሳ ተግባር ባለቤት፣ ከኢትዮጵያ መንግስት፣ ከካርበን ክሬዲት ሽያጭ ወይም የጥቅም ግጭት ከሚፈጥሩ የማማከር አገልግሎቶች ጥብቅ ገለልተኝነት እንዲኖር ማድረግና ያንኑ ማስቀጠል፤

፭/ ለሞያዊ ቸልተኝነት ኃላፊ መሆንና ለተሰየመው ባለሥልጣን ቁጥጥር እንዲመች ለ፲ (አስር) ዓመታት የኦዲት ማስረጃዎችን መያዝ አለባቸው።

33. Roles and Responsibilities of VVBs

All VVBs shall:

1/ Maintain formal accreditation and ensure the audit team possesses necessary technical and local expertise;

2/ Independently validate the Mitigation Activity Design Document (MADD) prior to registration;

3/ Verify the quantification and compliance of GHG emissions Reductions and Reversals in accordance with applicable rules and requirements including Carbon Standards and issue a formal Verification Report before Carbon Credits may be issued by the Carbon Registry;

4/ Maintain strict independence from the Mitigation Activity, any Mitigation Activity Owners, the Government of Ethiopia, Carbon Credit sales, or conflicting consultancy services;

5/ Be liable for professional negligence and retain audit evidence for 10 (Ten) years for DNA oversight.

ክፍል ስድስት

ፈቃድ መስጠትና የባለ ፈቃዶች ግዴታዎች

፴፬. የባለ ፈቃዶች ጠቅላላ ግዴታዎች

ሁሉም ባለ ፈቃዶች፦

፩/ የአካባቢ ጥበቃ ሥርዓቶችን፣ የግብር ግዴታዎችንና የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ሕጎችን ጨምሮ ተፈጻሚነት ያላቸውን የኢትዮጵያ ሕጎች በሙሉ ማክበር፤

፪/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት ከሞያዊ ቸልተኛነት ወይም ስህተቶች ሊመነጩ የሚችሉ ኀላፊነቶችን የሚሸፍን የሞያዊ ካሳ የመድን ሽፋን መያዝ፤

፫/ በገለልተኛነትና በግልጽነት ሥራን ማከናወን፤ ማንኛውንም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭት ስለ ጥቅም ግጭቱ ባወቁ በ፯ (ሰባት) ቀናት ውስጥ ለተሰየመው ብሔረራዊ ባለሥልጣን ማሳወቅ፤

፬/ አጠቃላይ የፕሮጀክት፣ የቴክኒክና የግብይት ሰነዶችን ደኅንነቱ በተጠበቀ መንገድ ቢያንስ ለ፲ (አስር) ዓመታት ይዞ በመቆየት የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ለሚያደርገው ፍተሻ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

፭/ ባለ ፈቃዱ ወይም ተዛማጆቹ፤ የገንዘብ ጥቅም ባላቸው ወይም የማማከር አገልግሎት በሰጡባቸው የቅነሳ ተግባራት ላይ የግምገማና የማረጋገጥ አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ የጥቅም ግጭት ካለባቸው አገልግሎቶች መቆጠብ፤

PART SIX

LICENSING AND OBLIGATIONS OF LICENSE HOLDERS

34. General Obligations of Licensees

All license holders shall:

1/ Adhere to all applicable Ethiopian laws, including environmental safeguards, tax obligations, and labor Regulations;

2/ Maintain valid professional indemnity insurance to cover potential liabilities arising from professional negligence or errors, as determined by the Directive to be issued by the Ministry;

3/ Act with independence and transparency, disclosing any potential conflict of interest to the Authority within 7 (Seven) days of its identification;

4/ Maintain comprehensive project, technical, and transaction records in a secure format for a minimum of 10 (Ten) years, ensuring they are available for inspection by the DNA;

5/ Refrain from self-dealing including providing VVB services for Mitigation Activities in which the licensee or its affiliates have a financial interest or have provided consultancy services.

፴፭. <u>የግምጋሚና አረጋጋጭነት ፈቃድ</u>

፩/ ግምጋሚና አረጋጋጭ አካላት በተሰየመው ባለሥልጣን ዕውቅና የተሰጣቸውንና እንደ አግባብነቱ ከበይነ-መንግስታት የአየር ንብረት ፓኔል የአሠራር መመሪያዎች፣ ከካርበን ስታንዳርዶችና ከተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ የማዕቀፍ ስምምነት ስታንዳርዶች ጋር የተስማሙ የካርበን ሒሳብ አያያዝ ሥነ-ዘዴዎችን በጥብቅ በሥራ ላይ ማዋል አለባቸው፡፡

፪/ ፈቃድ ያላቸው ግምጋሚና አረጋጋጭ አካላት ባለፉት ፫ (ሦስት) ዓመታት ውስጥ የማማከር፣ የንድፍ ወይም የማስተዳደር አገልግሎት በሰጡባቸው የቅነሳ ተግባራት ላይ የማረጋገጥ አገልግሎት መስጠት አይፈቀድላቸውም፡፡ ሆኖም ግልጽ ለማድረግ ይህ ክልከላ፣ ግምጋሚና አረጋጋጭ አካላት ለአንድ የሀሳብ አመንጪ የማስተካከያ እርምጃ ጥያቄዎችን ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይሆንም፡፡

35. <u>VVB License</u>

1/ VVBs shall strictly apply carbon accounting methodologies recognized by the DNA and consistent with IPCC guidelines, Carbon Standards, and UNFCCC standards, as applicable.

2/ All licensed VVBs are prohibited from Verifying a Mitigation Activity for which it has provided consultancy, design, or management services within the preceding 3 (Three) years, but for clarity this obligation does not prevent the VVB from issuing corrective action requisitions to a Proponent.

፴፮. <u>የካርበን ገበያ አሳላጪ ፈቃድ</u>

፩/ የካርበን ገበያ አሳላጮች (ግብይቶችን ወይም የምክር አገልግሎቶችን የሚያመቻቹ) እና የካርበን ሀብት አስተዳዳሪዎች (የክሬዲት ፖርትፎሊዮዎችን የሚያስተዳድሩ) ጥብቅ የአመኔታና የቴክኒክ ስታንዳርዶችን ማሟላት አለባቸው፡፡

፪/ የካርበን ሀብት አስተዳዳሪዎች ሁሉም የሚያስተዳድሯቸው የካርበን ፖርትፎሊዮዎች የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የሚያስቀምጣቸውን ብሔራዊ የተጨማሪነትና የቋሚነት መስፈርቶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

36. <u>Carbon Market Intermediary Licenses</u>

1/ The Carbon Market Intermediaries (facilitating trades or advisory) and Carbon asset managers (managing credit portfolios) shall meet strict fiduciary and technical standards.

2/ Carbon asset managers shall ensure that all managed carbon portfolios comply with national Additionality and Permanence criteria as established by the DNA.

፫/ ማንኛውም ፈቃድ ባለው የገበያ አሳላፊው ውስጥ በተጠቃሚ ባለቤትነት ወይም ኩባንያዊ መዋቅር ላይ የሚኖር ለውጥ እንዲጸድቅ በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡

3/ Any change in beneficial ownership or corporate structure of a licensed Market Intermediary must be reported to the EPA for approval within Thirty (30) days.

ክፍል ሰባት

የካርበን ስምምነቶች

PART SEVEN

CARBON AGREEMENTS

፴፯. የተፈጻሚነት ወሰንና ተፈጻሚነት

37. Scope and Application

፩/ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚፈጸሙ ወይም በድንበር ተሻጋሪ ስምምነቶች አማካኝነት የቅነሳ ተግባሩ የሚከናወነው በኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ ኢትዮጵያን በሚመለከቱ የካርበን ገበያ ስምምነቶች ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

1/ The provisions of this Part shall apply to all Carbon Market contracts concluded within or involving Ethiopia including cross-border agreements where the Mitigation Activity is implemented within Ethiopia.

፪/ ሁሉም የካርበን ውሎች በጽሑፍ መደረግና ዓላማዎችን፣ የሚሳተፉ ወገኖችንና የእያንዳንቸውን ሚና እንዲሁም ሌሎች ዝርዝሮችን በግልጽ ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡

2/ All carbon contracts shall be made in writing, and shall, among others, clearly specify the objectives, the parties involved and their respective roles.

፫/ ሁሉም በተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የሚፈቀዱ ድንበር ተሻጋሪ የካርበን ክሬዲት ግብይቶች ዳግሞ ቆጠራን ለመከላከል እንዲቻል የተመጣጣኝ ማስተካከያዎችን አፈጻጸም በዝርዝር ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

3/ All carbon contracts involving cross-border transactions of Carbon Credits that are authorized by the DNA shall specify the application of Corresponding Adjustments to prevent double counting under the Paris Agreement.

፬/ አንድ የካርበን ውል፡-

4/ A carbon contract shall be of no effect where it:

ሀ) በሥራ ላይ ያለ የመንግስት ፖሊሲን ወይም የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ከተጻረረ፤

a) violates existing public policy or environmental laws;

ለ) በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሕገ-ወጥ ወይም ከሥነ-ምግባር ውጪ ከሆኑ የቅነሳ ተግባራት የሚመነጩ የካርበን ክሬዲቶችን የሚመለከት ከሆነ፤

b) involves Carbon Credits that originated from Mitigation Activities that are unlawful or immoral under Ethiopian law;

ሐ) ግብይቱ በተፈጸመ በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ በካርበን መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ካልተደረገ፤

መ) በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ማውጣት ሲኖርበት ፈቃድ ባላወጣ ወይም የምዝገባ መመዘኛዎችን ባላሟላ ወገን የተገባ ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦች፣ በፍትሐ ብሔር ሕግ፣ በንግድ ሕግና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ወይም በተዋዋይ ወገኖች የውል ስምምነት ውስጥ ተቃራኒው ካልተገለጸ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ በኢትዮጵያ የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የካርበን ክሬዲቶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕግ ሲሆን የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የሚሰጣቸው የተቃውሞ አለመኖር ደብዳቤዎች፣ የማጽደቅና የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤዎችና የፈቃድ ደብዳቤዎች በሙሉ ያለ ምንም ልዩነት የሚገዙት በኢትዮጵያ ሕግ ይሆናል፡፡

፮/ ዝርዝር ጉዳዮች ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ ሆነው በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

፴፰. <u>ከውል የሚመነጩ የመብት ጥያቄዎች</u>

፩/ ከውል ስምምነቶች የሚመነጩ የካርበን ክሬዲት ካሳ እና/ወይም የመዋጮ የመብት ጥያቄዎች ዕውቅና የሚያገኙት የካርበን ክሬዲቶቹና የመጠቀም መግለጫዎቹ በዚህ ውል መሠረት በካርበን መዝገቡ ውስጥ በአግባቡ የተመዘገቡና የተረጋገጡ ከሆኑ ብቻ ነው፡፡

c) fails to register with the Carbon Registry within Thirty (30) days of execution;

d) is entered into by a party required to hold a license under this Proclamation that fails to obtain such license or has not fulfilled registration requirements.

5/ Unless otherwise provided by this Proclamation, Regulations issued hereunder, the Civil Code, the Commercial Code and other relevant laws or contractual agreements between parties, Ethiopian law shall be the default law applying to Carbon Credits in or subject to the jurisdiction of Ethiopia, on the understanding that all Letters of No Objection, Approval and Registration, and Authorization issued by the DNA shall be governed by Ethiopian Law without exception.

6/ Particulars shall be determined by Regulation or Directive issued for the implementation of this Proclamation.

38. <u>Contractual Claims</u>

1/ Carbon Credit compensation and or contribution claims arising from contractual arrangements shall be recognized only when the Carbon Credits and claims of use are duly registered with the Carbon Registry and verified in accordance with this Proclamation.

፪/ ከካርበን ክሬዲቶች ጋር የሚገናኙ ከውል የሚመነጩ የመብት ጥያቄዎች ተዋዋይ ወገኖችን፣ የቅነሳ ውጤቶቹን ወሰን፣ የካርበን ክሬዲት ድልድልንና የክትትል፣ ሪፖርት የማድረግና የማረጋገጥ ኀላፊነቶችን በዝርዝር ማሳየት አለባቸው፡፡

2/ Contractual claims related to Carbon Credits shall specify the parties, the scope of Mitigation Outcomes, the allocation of Carbon Credits, and responsibilities for monitoring, reporting, and Verification.

፫/ ከካርበን ክሬዲቶች ጋር የሚገናኙ ከውል የሚነጩ የመብት ጥያቄዎች በሙሉ በቅደሚያ ፈቃድ ባላቸው ገምጋሚና አረጋጋጭ አካላት መረጋገጥ የሚኖርባቸው ሲሆን በዚህም ከዓለም አቀፍ የካርበን ስታንዳርዶችና ኢትዮጵያ ካለባት ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር የተጣጣሙ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

3/ All contractual claims related to Carbon Credits shall be subject to prior Verification of the Carbon Credits by licensed VVBs, ensuring consistency with international carbon standards and Ethiopia's international obligations.

፬/ የካርበን መዝገቡ ድልድሎችንና ማስተላለፎችን ጨምሮ ከውል የሚመነጩ የመብት ጥያቄዎችን መመዝገብና ወደፊት በሚወጡ ደንቦች የሚወሰኑ የምስጢር ጥበቃ ድንጋጌዎችን ታሳቢ በማድረግ እነዚህን መረጃዎች ለሕዝብ ክፍት ማድረግ አለባቸው፡፡

4/ The Carbon Registry shall record contractual claims, including allocations and transfers, and shall make such records publicly accessible, subject to confidentiality provisions prescribed by Regulation.

፭/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ለሌሎች ዓለም አቀፍ የቅነሳ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፈቃድ ከሰጠባቸው የካርበን ክሬዲቶች ጋር የሚገናኙ የካርበን መብት ጥያቄዎች ዕውቅና የሚያገኙት የካርበን ክሬዲቶቹ በካርበን መዝገቡ ውስጥ ከተመዘገቡ በኋላ ብቻ ነው፡፡ ሁሉም የመብት ጥያቄዎች ተመጣጣኝ ማስተካከያዎች እንዲደረጉ የሚያስችሉ ሰነዶችን እንደ አግባብነቱ ማካተት አለባቸው፡፡

5/ Carbon claims associated with Carbon Credits that have be authorized by the DNA for use for other international mitigation purposes shall only be recognized after the Carbon Credits are registered in the Carbon Registry. All claims shall include documentation enabling Corresponding Adjustments where applicable.

፮/ ከውል ከሚመነጩ የመብት ጥያቄዎች የሚነሱ አለመግባባቶች በፍትሐ-ብሔር ሕግ፣ በንግድ ሕግ ወይም ተፈጻሚነት ባላቸው ሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች ወይም ተፈጻሚነት ባለው ውል ውስጥ ስምምነት በተደረገባቸው ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ወይም የግጭት አፈታት ሥነ-ሥርዓቶች መሠረት የሚፈቱ ይሆናል፡፡

6/ Disputes arising from contractual claims shall be resolved under the Civil Code, the Commercial Code, or other applicable Ethiopian laws, or such international arbitration or dispute resolution procedures agreed to in the applicable contract.

፯/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ከዚህ አዋጅ ወይም ከአዋጁ የማስፈጸሚያ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ጋር የማይጣጣሙ ከውል የሚመነጩ የወደፊት የመብት ጥያቄዎችን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

7/ The DNA may suspend or cancel future contractual claims found inconsistent with this Proclamation or its implementing Regulations or Directives.

፴፱. ከገምጋሚና አረጋጋጭ አካላት ጋር የሚደረግ የአገልግሎት ስምምነት

39. VVB Services Agreement

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑ የግምገማና የአረጋጋጭ አካል አገልግሎቶች በሙሉ በገምጋሚውና አረጋጋጩ አካል አንዲሁም በሀሳብ አመንጪው መካከል በሚደረግ የጽሑፍ ስምምነት መሠረትና ፈቃድ በተሰጠው ገምጋሚና አረጋጋጭ አካል መከናወን አለባቸው፡፡

1/ All VVB services within Ethiopia shall be performed by a licensed VVB pursuant to a written agreement between the VVB and the Proponent.

፪/ ገምጋሚና አረጋጋጩ አካል በፍጹም ነፃነትና ገለልተኝነት ሥራውን ማከናወን አለበት፡፡ ማንኛውም ገምጋሚና አረጋጋጭ አካል ባለፉት ሦስት (፫) ዓመታት ውስጥ የማማከር ወይም የንድፍ አገልግሎት በሰጠበት የቅነሳ ተግባር ላይ የማረጋገጥ አገልግሎት መስጠት አይፈቀድለትም፡፡

2/ The VVB shall act with absolute independence and impartiality. No VVB may provide Verification services to a Mitigation Activity for which they have provided consultancy or design services within the preceding Three (3) years.

፫/ ሀሳብ አመንጪው ከገምጋሚና አረጋጋጩ አካል ጋር ስምምነት በፈጸመ በ፲ (አስር) ቀናት ውስጥ ገምጋሚና አረጋጋጭ መሰየሙን ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ The Proponent shall notify the Environmental Protection Authority of the appointment of a Verifier and the scope of the Verification within Ten (10) days of the agreement.

፬/ የማንኛውም የማረጋገጥ ሒደት ውጤቶች እንደ ካርበን ክሬዲት መሰጠት ቅድመ-ሁኔታ ለካርበን መዝገቡ መቅረብ አለባቸው።

4/ The results of any Verification shall be submitted to the Carbon Registry as a prerequisite for Carbon Credit issuance.

፵. የልቀት ቅነሳ የግዢ ስምምነት

40. Emission Reduction Purchase Agreement

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ የልቀት ቅነሳ የግዢ ስምምነቶች ሻጭ፡-

1/ Emission Reduction Purchase Agreements in Ethiopia should require that the seller:

ሀ) የካርበን ክሬዲት ባለቤትነት ማስረጃ እንዲያቀርብ፤

a) provide proof of Carbon Credit ownership;

ለ) በማስተላለፍ ወቅት የካርበን ክሬዲቶች ባለቤት ስለመሆኑና ክሬዲቶቹ የጸኑ ስለመሆናቸው ዋስትና እንዲሰጥ እንዲሁም፤

b) warrant title and validity of Carbon Credits at the time of transfer;

ሐ) አግባብነት ባለው የካርበን መዝገብ በኩል የካርበን ክሬዲቶቹን እንዲያስረክብ ማስገደድ አለባቸው።

c) deliver Carbon Credits through the relevant Carbon Registry; and

፪/ የልቀት ቅነሳ የግዢ ስምምነቶች የሚገዙባቸው ሥነ-ሥርዓቶች በደንብ ወይም በመመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

2/ Procedures governing Emission Reduction Purchase Agreements shall be prescribed by Regulation or Directive.

፵፩. የካርበን ጥቅም የመጋራት ስምምነት

41. Carbon Benefit Sharing Agreement

፩/ የካርበን መጋራት ስምምነት ማለት የሀሳብ አመንጪው የሚያቀርበው የተሰነደ፣ ሕጋዊ አስገዳጅነት ያለውና ከካርበን ክሬዲት ሽያጭ የሚገኙ ገንዘብ-ነክ እና ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ጥቅሞች አግባብነት ላላቸው አካላት፣ ማኅበረሰቦች ወይም የመሬት ባለይዞታዎች የሚከፋፈሉበትን መንገድ የሚዘረዝር የግዴታ ሰነድ ነው።

1/ A carbon benefit sharing agreement is a documented and legally binding commitment submitted by a Proponent outlining the distribution of monetary or non-monetary benefits from carbon credit sales to relevant bodies, communities, or landowners.

፪/ ጥቅሞቹ ሮያልቲዎችን፣ የርትዕ ተሳትፎዎችን ወይም እንደ መሠረተ-ልማት፣ አገልግሎቶች ወይም የዐቅም ግንባታ ያሉ የዓይነት መዋጮዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

2/ The benefits may include royalties, equity participation, or in-kind contributions such as infrastructure, services, or capacity-building.

፫/ ባለድርሻዎች ነፃ፣ አስቀድሞ የተሰጠ፣ መረጃን መሠረት ያደረገና እንደ አግባብነቱ በጽሑፍ የተገለጸ ፈቃዳቸውን ካልሰጡ በስተቀር አንድ የካርበን ጥቅም መጋራት ስምምነት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፬/ የሀሳብ አመንጪው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

ሀ) ስምምነቱ ከመደረጉ በፊት ከባለ ድርሻዎች ጋር ምክክር ማድረግ፤

ለ) የክሬዲት ሽያጭ ትርፎች በደረሱት በስልሳ (፷) ቀናት ውስጥ ጥቅሞቹን ማከፋፈል፤

ሐ) የጥቅም ፍሰቶች ቢያንስ በየሦስት (፫) ዓመቱ በገለልተኛ የካርበን አረጋጋጭ አዲት መደረጋቸውን ማረጋገጥ፡፡

፭/ ባለ ድርሻዎች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል፦

ሀ) የመሬት ተደራሽነትንና በፕሮጀክት ተግባራት መሳተፍን ጨምሮ የፕሮጀክት ትግበራን ማመቻቸት፤

ለ) ጥቅሞችን ለማኅበረሰብ ልማት፣ ለአካባቢያዊ ጥበቃ ወይም መተዳደሪያን ለማሻሻልና ለሌሎች ስምምነት ለተደረገባቸው ዓላማዎች ማዋል፡፡

፵፪. <u>የሁለትዮሽ የትብብር ስምምነቶች</u>

፩/ ኢትዮጵያ በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮.፪ መሠረት ከሌሎች አገራት ጋር የምትፈጽማቸው የካርበን ስምምነቶች በሚከተሉት መርሆች የሚገዙ ይሆናሉ፦

ሀ) የካርበን ዋጋ ትመና መንገዶችን ማስቀመጥ፤

3/ A carbon benefit sharing agreement shall be of no effect unless stakeholders provide free, prior, and informed consent documented in writing, where appropriate.

4/ The Proponent shall have the following duties:

a) conduct stakeholder consultations prior to execution of the agreement;

b) distribute benefits within Sixty (60) days of receipt of credit sale proceeds;

c) ensure benefit flows are audited at least once every Three (3) years by an independent carbon verifier.

5/ The Stakeholders shall have the following duties:

a) facilitate project implementation including land access and cooperation with project activities;

b) utilize benefits for agreed purposes, such as community development, environmental protection, or livelihood improvement.

42. <u>Bilateral Cooperative Agreements</u>

1/ Ethiopia's Carbon Agreements with other countries, pursuant to Article 6.2 of the Paris Agreement shall be governed by the following principles:

a) establishment of carbon pricing mechanisms;

ለ) የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚያስችል ኢንቬስትመንትን፣ የካርበን ፋይናንስንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማመቻቸት፤

b) facilitating climate investment, carbon finance and technology transfer;

ሐ) ኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅዶቿን እንድታሳካ ለማገዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚተላለፉ የቅነሳ ውጤቶች ድርሻ መያዝ፤

c) retention of a share of Internationally Transferred Mitigation Outcomes to assist Ethiopia in fulfilling its NDCs;

መ) የቅነሳ ውጤቶች በክፍያ ለሦስተኛ ወገኖች እንዲተላለፉ በመፍቀድ የአየር ንብረት ኢንቬስትመንትን ማመቻቸት፤ እና

d) facilitating climate investment by providing authorization of transfers of Mitigation Outcomes to third parties for consideration; and

ሠ) ለፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮.፪ ተገዢ መሆን፡፡

e) compliance with Article 6.2 of the Paris Agreement.

፪/ በአንድ የትብብር ስምምነት መሠረት የሚተላለፉ የቅነሳ ውጤቶች በሙሉ በካርበን መዝገቡ ውስጥ ተመዝግበው ክትትል የሚደረግባቸው ይሆናል፡፡

2/ All mitigation outcomes transferred under a cooperative agreement shall be recorded and tracked in the Carbon Registry.

፫/ የካርበን ክሬዲቶች ለአቪዬሽን ዘርፍ የቅነሳ ግዴታዎች ተገዢ ለመሆን የሚታሰቡ ከሆነ ስምምነቱ ለዓለም ዓቀፍ አቪዬሽን የካርበን ማካካሻ ሥርዓት ብቁ መሆንን በግልጽ የሚጠቅስ እንዲሁም የዚህን ሥርዓት ሪፖርት የማድረግና የማረጋገጥ ስታንዳርዶች የሚያከብር መሆን አለበት፡፡

3/ Where Carbon Credits are intended for aviation compliance, the agreement shall explicitly indicate CORSIA eligibility and adhere to CORSIA reporting and verification standards;

፬/ ሁሉም ስምምነቶች በጽሑፍ መደረግ አለባቸው፡፡

4/ All agreements shall be made in writing.

ክፍል ስምንት

የጥቅም መጋራት አሠራር

፵፫. የጥቅም መጋራት አሠራርና ዕቅድ

፩/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣንና የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጧቸው ደንቦች ወይም መመሪያዎች አማካኝነት ከቅነሳ ተግባራት፣ ከቅነሳ ውጤቶችና ከተያያዥ የካርበን ክሬዲቶች የሚመነጩ ገቢዎችን ድልድልና ክፍፍል የሚገዙ የትርፍ መጋራት ማዕቀፍና አሠራሮችን ይዘረጋሉ፡፡

፪/ በቅነሳ ተግባራት ላይ በመሰማራት ከካርበን ክሬዲቶች ወይም ከቅነሳ ውጤቶች የሚገኝ ገቢ አግባብነት ባላቸው የፕሮጀክት ተዋንያን መካከል ፍትሐዊ፣ ግልጽና ርቱዕ የሆነ የጥቅም ክፍፍልን ለማረጋገጥ ለሚነደፍ የጥቅም መጋራት አሠራር ተገዢ መሆን አለበት።

፫/ የሀሳብ አመንጪው የጥቅም መጋራት ዕቅዱን ከቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነዱ ጋር አብሮ ማቅረብ አለበት፡፡

፵፬. የጥቅም መጋራት አጠቃላይ ድንጋጌዎች

፩/ ከቅነሳ ተግባራት፣ ከቅነሳ ውጤቶችና ከተያያዥ የካርበን ክሬዲቶች የሚገኙ ጥቅሞች የሁሉንም ባለድርሻዎች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማረጋገጥና ለአገራዊ ድኅነት ቅነሳ አስተዋጽዖ ለማበርከት ርቱዕ፣ ግልጽና ዘላቂ በሆነ መንገድ መከፋፈል አለባቸው፡፡

PART EIGHT

BENEFIT SHARING MECHANISM

43. Benefit Sharing Arrangement and Plan

1/ The DNA and Ministry of Finance, through Regulation or Directive, shall establish a Benefit Sharing framework and mechanism governing the allocation and distribution of revenues generated from Mitigation Activities and the Mitigation Outcomes and the associated Carbon Credits.

2/ Revenue generated from the carbon credits or mitigation outcomes through engagement in Mitigation Activity shall be subject to a benefit-sharing arrangement designed to ensure fair, transparent, and equitable distribution of benefits among relevant carbon project actors.

3/ The Proponent shall submit the Benefit Sharing Plan accompanying the MADD.

44. General Rules on Benefit-Sharing

1/ The benefits accruing from Mitigation Activities and the Mitigation Outcomes and the associated Carbon Credits shall be shared in an equitable, transparent, and sustainable manner to ensure the meaningful participation of all stakeholders and contribute to national poverty reduction.

፪/ ሁሉም የጥቅም መጋራት አሠራሮች የግልጽነትን፣ የተጠያቂነትን መርሆች ማክበር እንዲሁም ተጽዕኖ ከደረሰባቸው የአካባቢ ማኅበረሰቦች ነፃ፣ ቀድሞ የተሰጠና መረጃን መሠረት ያደረገ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።

፫/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን እና ገንዘብ ሚኒስቴር በየወቅቱ የጥቅም መጋራት የቅነሳ ተግባራትን የሚዳስስ የተጠቃለሉ ሪፖርቶችን ያወጣል።

፬/ የአንድ አካል የጥቅም መጋራት አሠራር ግዴታዎችን መወጣት አለመቻል የቅነሳ ተግባርና የካርበን ክሬዲት ፈቃድ ዕገዳን ወይም ስረዛን ሊያስከትል ይችላል።

2/ All Benefit Sharing Arrangements shall respect the principles of transparency, accountability, and the free, prior, and informed consent of affected local communities.

3/ The DNA and the Ministry of Finance shall publish periodic aggregated reports on Benefit-Sharing Mitigation Outcomes.

4/ An entity's failure to comply with Benefit Sharing Arrangement obligations may constitute grounds for the suspension or revocation of Mitigation Activity and Carbon Credit authorization.

፵፭. <u>ተጠቃሚዎችን መለየት</u>

ከቅነሳ ተግባራት የሚገኙ የተጣሩ ጥቅሞች የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚከተሉት ባለ ድርሻዎች ይደለደላሉ፦

፩/ ለፌዴራል መንግስት አገራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳና የመቋቋሚያ ፕሮግሞችን፣ ምርምሮችንና ዐቅም ግንባትን ለመደገፍ፤

፪/ ለክልልና የአካባቢ መንግስታት እና የከተማ መስተዳድሮች በቅነሳ ተግባሩ ክልል ውስጥ የአገር ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ለሚያስችሉ ፕሮጀክቶችና ለማኅበረሰብ ልማት ተግባራት ገንዘብ ለማቅረብ፤

45. <u>Identification of Beneficiaries</u>

The net benefits derived from Mitigation Activities shall be allocated among the following stakeholders as prescribed by Directive to be issued by the DNA:

1/ The Federal Government to support national climate change mitigation and adaptation programs, research, and capacity building;

2/ Regional and local governments and City Administrations to finance localized climate resilience projects and community development initiatives within the project jurisdiction;

፫/ ለሀሳብ አመንጪዎች፣ የካርበን ገበያ አሳላፊዎችና እንዲሁም እንደ አግባብነቱ ለሌሎች ተዋንያን ላደረጉት ኢንቨስትመንት ፍትሐዊ ትርፍ ማግኘታቸውንና የሥራ ክንውን ወጪዎቻቸውን መሸፈናቸውን ለማረጋገጥ፤

፬/ አነስተኛ አርሶ አደሮችንና የደን ተጠቃሚ ቡድኖችን ጨምሮ በፕሮጀክት ተግባራት በቀጥታ ተጽዕኖ ለደረሰባቸው ወይም መዋጮ ለሚያበረክቱ የአካባቢ ማኅበረሰቦች፤

፭/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣንና የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የሚደረጉ ማስተካከያዎች ዝቅተኛውን የማኅበረሰብ ድርሻ ከ፭ በመቶ በላይ የማይቀንሱ እስከሆነ ድረስ በደንብ ወይም በመመሪያ አማካኝነት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን አገራዊ አጀንዳዎች፣ የፕሮጀክት መጠንንና የማኅበረሰብ ፍላጎቶችን በሚያሳይ መልኩ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ በተቀመጡት ጥቅሞች ድርሻ ላይ ማስተካከያ ሊያደርጉ ይችላሉ።

3/ Proponents, Carbon Market Intermediaries and other actors, as appropriate, to ensure a fair return on investment and cover operational costs;

4/ Local communities including smallholder farmers and forest user groups who are directly affected by or contributing to the project activities;

5/ The DNA and Ministry of Finance may, by Regulation or Directive, adjust the shares of the benefits stipulated under the Sub-Article (1) of this article to reflect national priorities, project scales, and community needs provided that any such adjustment shall not reduce the minimum community share by more than 5%.

ክፍል ዘጠኝ
የፋይናንስ ድንጋጌዎች

PART NINE
FINANCIAL PROVISIONS

፵፮. የክፍያዎች ዝርዝር

፩/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የቅነሳ ተግባራትን የምዝገባ፣ የክትትልና የፈቃድ ወጪዎች የሚሸፍኑ አስተዳደራዊ ክፍያዎችን ይሰበስባል።

፪/ የክፍያዎቹ ዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ) በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚተላለፉ የቅነሳ ውጤቶች የቅነሳ ውጤቶቹ ዋጋ ፪ በመቶ በእያንዳንዱ ማስተላለፍ ላይ ይጣላል፤

46. Fee Structure

1/ The DNA shall levy and collect administrative fees to cover the costs of Mitigation Activity registration, monitoring, and authorization;

2/ The fee structure will be payable as follows:

a) 2% of the value of Internationally Transferred Mitigation Outcomes shall be levied on each transfer;

ለ) ለኢትዮጵያዊያን የቅነሳ ተግባር የመነሻ ሀሳብ ሰነድ ፻ ዩኤስዲ፣

ሐ) ለውጭ ዜጎች የቅነሳ ተግባር የመነሻ ሰነድ ፻፶ ዩኤስዲ፣

መ) ለኢትዮጵያ ዜጎች የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ ፻፶ ዩኤስዲ፣

ሠ) ለውጭ ዜጎች የቅነሳ ተግባር የንድፍ ሰነድ ፪፻ ዩኤስዲ፣

ረ) የምዝገባ ወይም ፈቃድ (ምስክር ወረቀት) የመስጠት ክፍያ፣ ልዩ የመለያ ቁጥር ክፍያ፣ የተመጣጣኝ ማስተካከያ ክፍያ፣ የመያዣ ሒሳብ ክፍያ ወዘተ እና ለሌሎች አስተዳደራዊ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች የተሰየመው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

፫/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ የላቀ ማኅበራዊና የአካባቢ ጥበቃ ጥቅም ላስገኙ አነስተኛና ማኅበረሰብ-መር ለሆኑ የቅነሳ ተግባራት ክፍያዎችን ሊያስቀር ወይም ቅናሽ ሊያደርግ ይችላል።

፬/ ሁሉም ክፍያዎችና የመንግስት የካርበን ክሬዲት ገበያ ድርሻዎች በአንድ ብሔራዊ የግምጃ ሒሳብ ውስጥ ተቀምጠው ለምዝገባ ተግባራትና ለአገራዊ የአየር ንብረት ሥራዎች የገንዘብ ምንጭነት ይውላሉ።

፭/ ከካርበን ክሬዲቶች ከሚገኘው ትርፍ ፭ በመቶ ድርሻ በኢትዮጵያ መንግስት የግምጃ ሒሳብ ውስጥ ገቢ ይደረጋል፤ ለአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ እርምጃዎች ድጋፍ የሚሰጥ ይሆናል።

b) fee for MAIN for citizens of Ethiopia USD 100;

c) fee for MAIN for non-citizens of Ethiopia USD 150;

d) fee for MADD for citizens of Ethiopia USD 150;

e) fee for MADD for non-citizens of Ethiopia USD 200;

f) Fees for other administrative services such as, but not limited to, Listing or issuance Fee, Unique Identification Number Fee, Corresponding Adjustment Fee, Holding Account Fee, etc to be stipulated by Directive issued by the DNA.

3/ The DNA may, by Directive, grant fee waivers or reductions for small-scale, community-led Mitigation Activities that demonstrate exceptional social or environmental benefits.

4/ All fees and government shares of Carbon Credit revenue shall be deposited into a national treasury account to finance registry operations and national climate initiatives.

5/ A 5% share of proceeds generated from Carbon Credits shall be deposited in the Government of Ethiopia's treasury account to support adaptation actions.

፵፯. <u>የባንኮችና የሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ተሳትፎ እና ሚና</u>

፩/ ፈቃድ ያላቸው ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከናወኑ የቅነሳ ተግባራት የብድር ፋይናንስ፣ የኤክዊቲ ኢንቨስትመንትና የብድር ገጽታ ማሻሻያዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የበላይ ቁጥጥር ሥር የፋይናንስ ተቋማት ለካርበን ክሬዲቶች ግብይት፣ ዝውውርና ክፍያ እንደ አሳላፊዎች ወይም ባለ ዐደራዎች፣ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡ የካርበን ክሬዲቶች በብድር ዋስትናነት ወይም መያዣነት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ግዘፍነት የሌላቸው ሀብቶች ናቸው፡፡ የተሰየመው ባለሥልጣን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር በመተባበር በካርበን ክሬዲቶች ላይ ያሉ የመያዣነት ጥቅሞች ለሦስተኛ ወገኖች በመረጃነት የሚመዘገቡበትን መዝገብ ያቋቁማል፡፡

፬/ ባንኮች የካርበን ሀብት ፖርትፎሊዮዎችን ከአካባቢያዊና ከማኅበራዊ ስጋት አስተዳደር ማዕቀፎቻቸው ጋር እንዲያቀናጁ ይበረታታሉ፣ ከካርበን ክሬዲት ጋር የሚያያዙ ቦንዶችንና አረንጓዴ ዋስትናዎችን ጨምሮ ልዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ማቅረብ ይችላሉ፤

፭/ ባንኮች እንደየፍላጎታቸው በገዢነት፣ በሻጭነት፣ በግብይት አከናዋኝነት ወይም በአሰባሳቢነት ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

47. <u>Participation and Roles of Banks and other Financial Institutions</u>

1/ Licensed banks and financial institutions may provide debt financing, equity investment, and credit enhancement facilities for Mitigation Activities to be implemented in Ethiopia.

2/ Financial institutions may act as intermediaries, or custodians for the trading, transfer, and settlement of Carbon Credits, subject to the oversight of the National Bank of Ethiopia and the DNA.

3/ Carbon Credits issued under this Proclamation shall be recognized as intangible assets that may be used as collateral or security for credit facilities. The DNA shall collaborate with the National Bank of Ethiopia to establish a registry for the perfection of security interests in Carbon Credits.

4/ Banks are encouraged to integrate carbon asset portfolios into their Environmental and Social Risk Management frameworks and may develop specialized financial products, including sustainability or Carbon Credit linked bonds and green guarantees;

5/ Banks may participate as buyers, sellers, traders, or aggregators as per their discretion;

፮/ በካርበን ገበያ ውስጥ የሚሳተፉ የፋይናንስ ተቋማት ከካርበን ጋር የሚገናኙ ስጋቶቻቸውን ወይም ተጋላጭነቶቻቸውንና ግብይቶችን በብሔራዊ የልኬት፣ ሪፖርት የማድረግና የማረጋገጥ ሥርዓት መሠረት ለተሰየመው ባለሥልጣን ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

ክፍል ዘጠኝ

ተገዢነትና ሕግ ማስከበር

፵፰. ፍተሻ፣ ተገዢነትና አስተዳደራዊ እርምጃዎች

፩/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ተፈጻሚነት ላላቸው ሕጎች፣ ደንቦችና የፈቃድ ሁኔታዎች ተገዢነትን ለማረጋገጥ መደበኛ ወይም ድንገተኛ የቅነሳ ተግባር የሳይት ፍተሻዎችን በማድረግ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚተላለፉ የቅነሳ ውጤቶች ወይም የዓለም አቀፍ አቪዬሽን የካርበን ማካካሻ ሥርዓት ክሬዲቶችን አዲት በማድረግ ተገቢ ምዝገባን፣ መክሰምንና በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ ፮ ዕውቅና ለተሰጣቸው ሥነ-ዘዴዎች ተገዢ መሆንን የማረጋገጥ ሥልጣን አለው።

፪/ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በቅነሳ ተግባር ሳይቶች ላይ መደበኛ ወይም ድንገተኛ ፍተሻ በማድረግ የአካባቢና ማኅበራዊ የጥበቃ ሥርዓቶች በጸደቁ የአካባቢና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነዶችና አግባብነት ባላቸው ሌሎች የአካባቢ ጥበቃ የሕግ ማዕቀፎች መሠረት እየተተገበሩ መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን አለው።

6/ Financial institutions participating in the Carbon Market shall report their carbon related exposures and transactions to the DNA in accordance with the National Measuring, Reporting, and Verification system.

PART TEN

COMPLIANCE AND ENFORCEMENT

48. Inspection, Compliance, and Administrative Measures

1/ The DNA shall have the power to conduct regular or unannounced inspections of the sites of Mitigation Activities in order to verify compliance with applicable laws, regulations, and authorization conditions and audit of ITMO or CORSIA credits, ensuring proper registration, retirement, and compliance with methodologies recognized under Article 6 of the Paris Agreement and other Carbon Crediting Mechanisms.

2/ The EPA shall have the power to conduct regular or unannounced inspections of the sites of Mitigation Activities to audit Environment and Social Safeguards are being implemented against the approved Environmental and Social impact assessment documents and other relevant environmental legal frameworks.

፫/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ፍተሻዎችን፣ ክትትልንና የኦዲት ሥራዎችን የሚሠሩ ገለልተኛ የሦስተኛ ወገን ኦዲተሮችን ወይም ኤክስፐርቶችን ሊሰይም ይችላል፡፡ በይፋ ተቃውሞ ካልቀረበባቸው በስተቀር የሦስተኛ ወገን ኦዲተሮቹ ወይም የኤክስፐርቶቹ ግኝቶች አስገዳጅት ይኖራቸዋል፡፡

3/ The DNA may appoint independent third-party auditors or experts to carry out inspections, monitoring, or audit activities, and their findings shall be binding unless formally contested.

፬/ ሀሳብ አመንጪው በፍተሻ ወቅት አግባብነት ያሏቸውን ፋሲሊቲዎች፣ ማኅደሮችና ሠራተኞችን ሙሉ በሙሉ ክፍት ማድረግ አለበት፡፡

4/ Proponents shall provide full access to relevant facilities, records, and personnel during inspections.

፭/ በፍተሻ ሒደት ውስጥ አነስተኛ ጥሰቶች ወይም ጉድለቶች ከተገኙ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን ወይም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሥር በተቀመጡት ሥልጣንና ተግባሮቻቸው መሠረት የፕሮጀክቱ ሀሳብ አመንጪ በሚቀመጥለት የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዲወስድ የሚጠይቅ ማስጠንቀቂያ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

5/ Where inspections reveal minor non-compliance or deficiencies, the DNA or the EPA may issue a notice of corrective action, requiring the Project Proponent under their authorities stipulated under Sub-Articles (1) and (2) of this Article to remedy the issue within a specified time-frame.

፮/ አካባቢያዊ ደኅንነትን፣ የገበያ መረጋጋትን ወይም የሕዝብ ጥቅምን ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፈቃድ ደብዳቤዎች ተጨማሪ ሁኔታዎችን፣ ገደቦችን ወይም የክትትል መመዘኛዎችን እንዲያካትቱ ተደርገው ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡

6/ Authorizations may be modified to include additional conditions, restrictions, or monitoring requirements where necessary to safeguard environmental integrity, market stability, or public interest.

፯/ የቅነሳ ተግባራት የማጭበርበር አሠራሮችን ጨምሮ የክትትል ስታንዳርዶችን ማሟላት ካልቻሉ ወይም ለአካባቢያዊ ደኅንነት ወይም የገበያ ተአማኒነት ስጋት የሚፈጥሩ ከሆነ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የፈቃድ ማረጋገጫውን፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ደግሞ የሥራ ፈቃዱን ሊያግዱ ወይም ሊሰርዙ ይችላሉ፡፡

7/ Where Mitigation Activities fail to meet monitoring standards, include in fraudulent practices, or pose risks to environmental or market integrity, the DNA or the EPA may suspend or Revoke the authorization and license, respectively.

፰/ ዕገዳ ተፈጻሚ የሚሆነው የሀሳብ አመንጪው የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ ተገዢ መሆኑን አሳይቶ ዕገዳው እንዲነሳ እንዲያደርግ ነው።

8/ Suspension shall be imposed for a defined period, during which the Proponent must demonstrate compliance in order for any suspended authorization or license to be reinstated.

፱/ የቅነሳ ተግባራት የሚሰረዙት በተደጋጋሚ ጥሰት፣ ተጨባጭ በሆነ ማጭበርበር ወይም ሆነ ተብሎ በሚፈጸም የሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት ነው።

9/ Revocation of Mitigation Activity authorizations may in cases of persistent non-compliance, material misrepresentation, or deliberate misconduct.

፲/ የሀሳብ አመንጪው፣ አልሚው ወይም የካርበን ክሬዲት ፕሮጀክቱ ባለቤት የማጭበርበር ድርጊት ካልፈጸመ በስተቀር የተሰየመው ባለሥልጣን ከዚህ በፊት ፈቃድ የሰጠባቸውን የካርበን ክሬዲቶችን ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰርዝም።

10/ There shall be no retrospective revocation of Carbon Credits once authorized by the DNA absent fraud of the Proponent, Developer, or Carbon Credit Project Owner.

፵፱. <u>የቅሬታ አፈታትና የይግባኝ ሥነ-ሥርዓት</u>

49. <u>Grievance Redress and Appeal Procedures</u>

፩/ ማንኛውም በቅነሳ ተግባራት ምክንያት ተጨባጭና አሉታዊ ተጽዕኖ የደረሰበት ሰው በአንቀጽ ፳፪ ሥር የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በሚመለከት ለተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የበላይ ኀላፊ፣ በአንቀጽ ፳፭ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በሚመለከት ደግሞ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል።

1/ Any person who has been materially and negatively impacted by a Mitigation Activities may lodge a written complaint to the Head of the DNA for those issues prescribed under Article 22; or the EPA for those issues prescribed under Article 25 of this Proclamation.

፪/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የበላይ ኀላፊና የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የበላይ ኀላፊ የቅሬታ አፈታት ሥነ-ሥርዓቶችን በመዘርጋትና በሥነ-ሥርዓቱ መሠረት ቅሬታዎችን በመመርመር አቤቱታዎች በደረሷቸው በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ውሳኔ መስጠት አለባቸው።

2/ The Head of the DNA and Head of the EPA shall establish grievance procedures, review the grievance in accordance with such procedures, and provide a written decision within 30 days following the receipt of the grievance complaint.

፫/ የተሰየመው ባለሥልጣን ወይም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የቴክኒክ አለመግባባቶችን የሚመረምሩ ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

3/ The DNA or the EPA may establish an ad hoc or standing Grievance Committee to investigate technical disputes.

፬/ ማንኛውም የአንድ ግጭት ወገን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር በተደነገገው መሠረት የግጭቱን ዓይነት ታሳቢ በማድረግ በተሰየመው ባለሥልጣን ወይም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ አካል በ፴ ቀን ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ Any party to a dispute may appeal the decision of the reviewing DNA or EPA, as per the type of dispute as stipulated Sub-Article (1) of this article, may file an appeal to the Federal High Court within 30 days.

፭/ ከካርበን ገበያ ተግባራት በሚነሱና ይግባኝ በተባለባቸው ግጭቶች ግራ ቀኝ የሆኑ ወገኖች በግልግል ዳኝነትና የእርቅ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፯/፪ሺ፲፫ ወይም እንደ የተባበሩት መንግስታት የዓለም አቀፍ ንግድ ሕግ ኮሚሽን ዓለም አቀፍ ደንቦች ባለ ዓለም አቀፍ ደንቦች መሠረት አለመግባባቱን በአስማሚ ወይም በግልግል ዳኝነት በኩል ለመፍታት ስምምነት ማድረግ አለባቸው፡፡

5/ The parties to the appealed dispute arising from carbon market activities shall then agree to settle their dispute through mediation or arbitration. in accordance with the Arbitration and Conciliation Proclamation No. 1237/2021 or international rules such as the United Nations Commission on International Trade Law (UNCITRAL) Arbitration Rules.

፮/ የግልግል ዳኝነቱ የሚካሄድበት ቦታና የሥራ ቋንቋ ግራ ቀኙ በሚያደርጉት ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡

6/ The seat and language of the arbitration shall be determined by the agreement of the parties.

፯/ ማንኛውም የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የመጨረሻ እና በግራ ቀኙ ላይ አስገዳጅነት የሚኖረው ይሆናል፡፡

7/ Any arbitral award rendered shall be final and binding on the parties.

ክፍል አስር

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፶. የወንጀል ተጠያቂነት

ማንኛውም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ሰው ወይም አካል በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

፶፩. የፍትሐ ብሔር ኃላፊነቶች

፩/ የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና ድንጋጌዎችን በመጣስ በሌሎች ላይ ጉዳት ወይም ኪሳራ ያደረሰ ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት ላደረሰው ጉዳት ወይም ኪሳራ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተቀመጠው የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ውስጥ የተቀመጡትን የወንጀል ወይም አስተዳደራዊ ቅጣቶች አያስቀርም፡፡

፶፪. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን የኢትዮጵያ ብሔራዊ የካርበን መዝገብ በይፋ እስኪመሠረትና ወደ ሥራ እስኪገባ ድረስ ጊዜያዊ ዲጂታል የካርበን መመዝገቢያ ሥርዓት ያዘጋጃል፡፡

፪/ የተሰየመው ባለሥልጣን እየተከናወኑ ያሉ የቅነሳ ተግባራትን ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ቀን አንስቶ ባሉት ፺ (ዘጠና) ቀናት ውስጥ በብሔራዊ የካርበን መዝገብ ውስጥ ይመዘግባል፡፡

PART ELEVEN

MISCELLANEOUS PROVISIONS

50. Criminal Liability

Whosoever contravenes to this Proclamation shall be liable to conviction and punishment as prescribed by the Criminal Code of Ethiopia.

51. Civil Liabilities

1/ Any person who violates the provisions of this Proclamation or Regulations or Directives issued hereunder shall be held liable for any damage or loss caused to others in accordance with the relevant provisions of the Civil Code of Ethiopia.

2/ The civil liability under Sub-Article (1) of this Article shall be independent of any criminal or administrative sanctions provided for under this Proclamation.

52. Transitional Provisions

1/ The DNA shall maintain a temporary digital carbon recording system until such time as the Ethiopia National Carbon Registry is formally established and operational.

2/ The DNA shall register ongoing Mitigation Activities in the National Carbon Registry within 90 (Ninety) days from the date of coming to enforce of this Proclamation.

፫/ እየተከናወኑ ያሉ የቅነሳ ተግባራት ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ቀን አንስቶ ባሉት ፪ (ሁለት) ዓመታት ጊዜ ውስጥ በአዋጁ ውስጥ ተደንግገው ለሚገኙ ሁኔታዎች ተገዢ መሆን አለባቸው።

3/ Ongoing Mitigation Activities shall comply with the conditions of this Proclamation within 2 (Two) years from the date of its coming into effect.

፬/ አመልካቾቹ ትግበራዎችን ከዚህ አዋጅ መመዘኛዎች ጋር ለማጣጣም አስፈላጊ እርምጃዎችን እስከወሰዱ ድረስ ለቅነሳ ተግባራት፣ ለተያያዥ የቅነሳ ውጤቶችና የካርበን ክሬዲቶች የቀረቡና በመጣራት ሒደት ላይ ያሉ ማመልከቻዎች፣ ፈቃዶች ወይም ማጽደቆች ከ፪ (ሁለት) ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ የጸኑ ሆነው ይቆያሉ።

4/ Pending applications, authorizations, or approvals for Mitigation Activities and related Mitigation Outcomes and Carbon Credits shall remain valid for a period not exceeding 2 (Two) years, provided that applicants take necessary steps to align with the requirements of this Proclamation.

፭/ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት የተደረጉ የውል ስምምነቶች የጸኑ ይሆናሉ።

5/ Contractual arrangements entered into force before the coming into effect of this Proclamation shall be honored.

፮/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣን፣ ጊዜያዊ የግዴታዎች ቀሪ መሆንን፣ ሒደታዊ የተገዢነት የጊዜ ሰሌዳዎችንና የመሐል ጊዜ አመራርን ጨምሮ የተሳለጠ ሽግግር እንዲኖር ለማመቻቸት መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

6/ The DNA may issue Directives to facilitate the smooth transition, including temporary waivers, phased compliance schedules, or interim guidance.

፯/ በሽግግር ጊዜ ወቅት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ ከዚህ በፊት በነበሩ የሕግ ማዕቀፎች ሥር የተገኙ መብቶችን በማይነካ መልኩ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተቀመጡት የግጭት አፈታት መንገዶች የሚፈቱ ይሆናል።

7/ Disputes arising during the transitional period shall be resolved in accordance with the dispute resolution mechanisms established under this Proclamation, without prejudice to rights accrued under prior legal frameworks.

፰/ የካርበን መዝገቡ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ሲገባና እየተናወኑ የነበሩ የቅነሳ ተግባራት ከዚህ አዋጅ ጋር ሲጣጣሙ በዚህ አንቀጽ ሥር የሚገኙት የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያበቃል።

8/ Transitional provisions under this Article shall lapse upon the full operationalization of the Carbon Registry and the alignment of existing Mitigation Activities with this Proclamation.

፶፫. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ማንኛውም ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

53. Inapplicable Laws

No Law, Regulation, Directive, or Customary Practice in contravention of this Proclamation may be applicable to matters provided therein.

፶፬. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ የተሰየመው ብሔራዊ ባለሥልጣንና የገንዘብ ሚኒስቴር ለዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚወጡ ደንቦች አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

፫/ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የብቃት መመዘኛዎችንና ልዩ የፈቃድ መመዘኛዎችንና ፈቃድ የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች የሚመለከቱ የአሠራር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተሰየመው ባለሥልጣን መደበኛ ደንቦች ወይም መመሪያዎች እስከሚወጡበት ጊዜ ድረስ ከዚህ አዋጅ መንፈስና ዓላማዎች ጋር የሚጣጣሙ ጊዜያዊ የአሠራር መመሪያዎችን ወይም ትእዛዞችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

54. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue Regulation for the implementation of this Proclamation.

2/ The DNA and Ministry of Finance may issue Directives for the implementation of this Proclamation and Regulation under this Proclamation.

3/ The Environmental Protection Authority may issue guidelines concerning the competence requirements and specific licensing requirements and conditions to obtain license.

4/ The DNA may, where necessary, issue temporary guidelines or instructions to address urgent matters pending the issuance of formal Regulations or Directives, provided such measures are consistent with the spirit and objectives of this Proclamation.

፶፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

55. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, On this 3rd day of September, 2026

TAYE ATSKESELASSIE
PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA